# ያልተቋጨ ጉዞ

አመልማል ደምሰው አንዳርጌ

አዲስ አበባ

2008 ዓ.ም

ያልተቋጨ ጉዞ

አመልማል ደምሰው እንዳርጌ

2008 ዓ.ም.

የመጀመሪያ ዕትም- ሰኔ 2008 ዓ.ም.

የፀሐፊዋ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

©አመልማል ደምሰው እንዳርጌ፣ 2008

ለአስተያየትዎ:- amelmald@gmail.com

የዚህ መፅሐፍ ገቢ 10% በድርቅ ለተጎዱ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ ይሁንልኝ::





## ምስጋና

«ሁሉ በእሱ ሆነ!»

ውድ አባቴ! አቶ ደምሰው እንዳርጌ—ዘመንህን ተሻግረህ የመማርን ጥቅም አሳውቀህኛል:: አምላክ አፅምህን ያለምልመው::

ው .. እናቴ! እማዎይ ያምሮት ሰንደቅ---«ጥሩ ሰው ማለት ከከፉ ጋር መኖር የቻለ ነው» ትይን ነበር:: ከአንቺ ተቻችሎ መኖርን፣ ደግነትንና ቸር መሆንን ተምረናል:: ነብሰሽን ከአብርሃምና ከይስሀቅ ጎን ያኑርልን::

ደራሲ ቆንጂት ብርሃን--- የራስሽ እጣዳፊ ሰራ እያለብሽ የመጽሐፉን ረቂቅ አንብበሽ የሰጠሽኝ ገንቢ አስተያየት በእጅጉ ረድቶኛል:: የአንቺ ያላሰለሰ ማበረታቻ ባይኖር ኖሮ ይህ መጽሐፍ ከቶም መጽሐፍ ሆኖ ለሕዝብ ባልቀረበም ነበር:: ቀናነትሽን ሳደንቅ ከአንቺ ጋር የተዋወኩባትን ቀን እየመረቁ ነው:: ያደረግሽልኝ ሁሉ ከምስጋና በላይ ነው::

ተሰፋዬ ወልደዮሐንስ--- የማመሰግንህ ርህራሄ ከሌለው የሰላው የጽሁፍ መቀስህ ጋር ነው:: የአንተ ድጋፍ ባይታከልበት ኖሮ ምናልባት ይህ መጽሀፍ ሳጥን ውስጥ ተቀምጦ ዓመታትን ባስቆጠረ ነበር::

ታጠቅ ሰለሞን የሰጠኸኝ ትችት ያላየኋቸውን ጉድለቶች ደግሜ እንዳይ በእጅጉ ረድቶኛል::

ተካልኝ በንቲ፣ እሰቴር ኃይለመለኮት ምን ቃላት አግኝቼ ላመስግናችሁ? ረቂቁን አንብባችሁ ስትጨርሱ ገጽታችሁ ላይ የነበረው ደስታ ከእኔ ከባለቤቷ ላይ እንኳ አልታየም:: ተከሽ የሰጠህኝ አስተያየት ደፍሬ መጽሐፉን መጽሐፍ እንዳደርገው ጉልበት ሆኖኛል:: እናንተን የመሰለ ጽኑ ወዳጅና ጓደኛ ስላለኝ ሁሌም ሙሉነት ይሰማኛል::

መሰፍን መሰለ ሳትሰለች ለሰጠኸኝ ሙያዊ ድጋፍ ሁሉ እግዜር ይሰጥልኝ ብልህ ያለንን ቅርርብ ያርቅብኝ ይሆን? ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አሰፋው ካለብህን የስራ ጫና ጋር ረቂቁን አንብበህ ለሰጠህኝ አተያየት ከልብ አመሰግናለሁ::

የምስራች ደሳለኝ-- የማመሰግንሽ ረቂቁን አንብበሽ አስተያየት ስለሰጠሽን ብቻ አይደለም:: የነበርሽበትን የጊዜ አጣብቂኝ አውቅ ስለነበር እንጂ ሲቲና በሻህ-- የገነባሽው ሞራሌ አንድ እርምጃ ወደፊት እንድሄድ ረድቶኛልና ምስጋናዬ ይድረስሽ::

ወርቁ፣ ኃይሌ፣ ብርቱካን፣ ሰብለ-- ፎዚ ወንድም እህቶቼ! ታደርጉልኝ ለነበረው ድጋፍና ማበረታቻ ምስጋናዬ የላቀ ነው::

ገረመው በቀለ መፅሐፉ መፅሐፍ ስለሆነ ደስ ይበልህ:: ለመድሃኒት፣ ለየወጌ፣ ለሰለሞን፣ ለህፃን ቅዱስና በፀሎት ለትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ::

ልጆቼ! ሳምሶን ሙሉ (ዶ/ር)፤ ዲያቆን ዮናስ ሙሉ፤ ማሕሌት ሙሉ፤ ሰብለ ገረመውና ሚካኤል ስለሺ ይህ መጽሀፍ-- መጽሀፍ ሆኖ እንዲወጣ የነበራችሁን ጉጉት ሳስብ እንኳን ደስ አላችሁ ብላችሁ ይሻል ይሆን አልኩ!





መታሰቢያነቱ

- ለኢትዮጵያ በጎ አሰበው፤ በጎ አልመው፤ ለእድገቷና ለብልጽግናዋ ሲታገሉ ለተሰው ሁሉ::
- ለአቶ ሙሉ አምባው ፈረደ-- ዲሞክራሲን፤ ፍትህንና ነፃነትን ፍለጋ ወጥተህ ለቀረኸው::
- ለአልማዝ ደምሰው አንዳርጌ-- ልጅነትሽን ገና ሳትጨርሽ በሰው አገር በረ-ጅሙ አስበሽ በአጭር ለቀረሽው::

አሳረኛ አገር ውስጥ እትብቷ በመቀበሩ አጥብቃ አዘነች:: ያ የነበራት እንደ ጧፍ የሚንቀለቀል የአገር ፍቅር ስሜት!--- ያ እንደ መንጠር እሳት የነደደ አገራዊ ወኔዋና ኩራቷ ከውስጧ ሊመክን ምንም ያህል አልቀረውም::

«ከምንም በላይ በምወዳትና በምኮራባት አገሬ እንዲህ ጭን--ቅ! ያለ ነገር ገጥሞኝ---- ያላሰብኩት ዱብዳ! ወርዶብኝ አቤቱታዬን በጽሞና አዳምጦ የሚቀበል የመንግሥት ሠራተኛ እንዴት አጣለሁ!? ችግሬን አዳምጦ በአግባቡ ሊረዳኝ የሚችል የመንግሥት ተቋም እንዴት አገሬ ላይ አይኖርም!?» አለች እጅግ ተከፍታ!

«ትሰሚያለሽ?» አለ ያው ነገር ነገር የሚለው ወታደር::

«አዎ! እያዳመጥኩ ነው» አለች ተስፋ በሌለው ስሜት::

«ሃያ አራት ሰዓት እስኪሞላው መጠበቅ ይኖርብሻል--- ገባሽ!»

«ኧረ ሃያ አራት ሰዓትስ ሞልቶታል:: ትናንት የወጣ ይኸው እስካሁን .....»

«ቢቃ!--- ቢቃ! እሺ ገቡቶኛል:: ለምጠይቅሽን ጥያቄ ብቻ በአጭር በአጭሩ መልስ ስጪ» አላት:: ለሦስተኛ ጊዜ ሀሳቧን የመጨረስ እድል እንኳ አላገኘችም። እሰሳልሳ ለመናገርም--- - ለመናደድም---- ለማዘንም ፋታ ሊሰጣት አልቻለም::ጥድፊያውና ቁጣው ቆሌ ይገፋል::

«እሺ» አለች ለንግግሯ እየተጠነቀቀች።

«መቼ ይሆን ጉዳያችንና አቤቱታችን በአግባቡ ተቀብሎ የሚያስተናግድ ሕዝብ አገልጋይ መንግሥትና መልካም አስተዳደር የምናገኘው?» ሰራሷ አንሾካሾከች:: እድሜዋን ሙሉ ስትመኘውና ስትታገልለት የኖረችው መልካም አስተዳደር እንደ ሰማይ ራቃት:: ሕዝብ ይሁነኝ ብሎ የመረጠው— ሕዝብን አክብሮ በአግባቡ የሚያገለግል መንግሥት በእጅጉ ናፈቃት:: የሰውየው ያልተገራ ንግግርና ማን አለብኝነት ካጋጠማት ያልታሰበ ችግር ይበልጥ አናደዳት:: ውስጥ አንጀቷ በቁጭት ተርመጠመጠ:: እንዲህም ሆና በተጠየቀችው መሰረት ተጠንቅቃ የመኖሪያ አድራሻ ሰጠች። ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ስልክና የመኖርያ ቤት ቁጥር የሚሰራበትን መስሪያ ቤት ሁሉ ሳይቀር አስመዘገበች።

«ሀሎ! አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ነው?» እንደ ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያው ያለ ቁጣ ቁጣ የሚለው የእለት ሁኔታ ተቀባይ ወታደር እንዳይገጥማት በልቧ ጸለየች። የወዲያኛው መስመር ስልክ ሊነሳ ልቧ ከውስጥ ተንደፋደፈች::

«አዎ! ምን እንርዳዎት?» አለ በወዲያው መስመር ያለው ሰው ረጋ ብሎ:: ትንፋሿን እንደ ምንም ዋጥ አድርጋ





«አባከዎ ከቤቱ ወጥቶ ያልተመለሰ ሰው ሁኔታ ለማስመዝገብ ነበር» አለች ተሰሳልሳ::

«ከቤቱ ወጥቶ ካልተመለሰ ሃያ አራት ሰዓት ሞልቶታል?» ሲል አሁንም በተረጋጋ መንፈስ ጠየቃት::

«አዎ!---ትናንት የወጣ--- ይኸው እስካሁን አልተመለሰም» አለች:: ይኸኛው ቃል ተቀባይ ወታደር ረጋ ያለ ሰለመሰላት በጭንቀት የተንጠለጠለች ልቧን በረጅሙ ተንፍሳ መለስ አደረገቻት:: ረጅም ትንፋሿ በወዲያኛው የስልክ መስመር እዳይሰማ የስልኩን መነጋገሪያ ጫፍ በእጇ እፍን አድርጋ ይዛ::

«ምናልባት ዘመድ ወይ ጓደኛ ቤት ሄዶ አድሮ እንዳይሆን እጠያይቃችኋል? ከልምድ እንደምናውቀው እንዳንዴ ወዳጅ ዘመድ ቤት ተሂዶ ጨዋታ ይያዝና ሰዓቱ ሲገፋ በዚያው ይታደራል» አለ ወታደሩ:: ለማጽናናት እየሞከረ::

«ኧረ የምናውቃቸውን ሰዎች በሙሉ አጠያይቄያለሁ:: ከማንም ሰው ቤት እንዳልሄደ አረጋግጫለሁ። በጣም ሲጨንቀኝና መጨረሻ ላይ ፖሊስ ጣቢያ ማሳወቅና ማስመዝገብ ግድ ሊሆንብኝ ነው የምደውለው» አለች እየተጨነቀች።

ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ፤ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ፣ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ..... በአጠቃላይ አዲስ አበባ ለሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ ክፍተኞች፣ ቀበሌዎች..... ምን ቀርቷት? ይመለከታቸዋል ብላ ላመነችባቸውና ለገመተቻቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ሁሉ አመለከተች። ድንገት ቢረዳኝ ብላ ለእንዳንድ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችም አስታወቀች:: በአካል ቀርባ እያነባች ሁኔታውን አስረዳች። በየሆስፒታሉ ባዘነች። የምኒልክ ሆስፒታልን ሁኔታ አንቀጠቀጣት።

እንዲህ ጭንቅ ያለ ነገር ሲገጥማት ወድያውኑ ፈጥና ከጎኗ የተገኘችው ታናሽ እህቷ ራሔል ነበረች።

«ምንድነው ነገሩ ምን ተፈጠረ?» አለች ራሔል ከፉኛ ደንግጣ::

ትሩፋት ባለቤቷ ትናንትና ቀን ላይ የወጣ እስካሁን ድረስ እንዳልተመለሰ ስትነግራት አንቅልፍና ድንጋጤ ሁለመናዋን ድከም አድርጎት ነበር::

«ተጣልታችሁ--- ማለቴ ከፉ ነገር ተነጋግራችሁ ነበር?» ጠየቀች ራሔል ግራ ግብት ብሏታል::

«እንደሱ ቢሆንማ ምን ያስጨንቀኝ ነበር ራሔል? ግፋ ቢል በሽማግሌ እንታረቅ አልነበር::»

«ሲወጣ ገንዘብ ይዞ ነበር? ምናልባት ለገንዘቡ ሲል ማጅራት መቺ....» ራሔል ልትናገረው የነበረውን እንጠልጥላ ተወችው::

«ከትራንስፖርት ውጭ ኸረ ይህን ያህል የረባ ገንዘብ አልያዘም» አለች ትሩፋት::

አብረው በኖሩበት ዘመን ሁሉ የሚሄድበትን ጉዳይና ቦታ ሳይነግራት የቀረበት ጊዜ ትዝ አይላትም:: እንዲህ በወጣበት የማደር አጉል ጸባይ ፈጽሞ አይታበት አታውቅም:: ምን አልባት ድንገት በተፈጠረ ጠብ ታስሮ እንደሆን ብለው ሳይቀር አስበዋል:: በየትኛውም የአዲስ አበባ የታወቁ ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ ግን አልነበረም:: እንደው ቢጨንቃቸው ነው እንጂ አምባጓሮ ውስጥ የማይገኝ ሰው መሆኑን ሁለቱም አሳምረው ያውቃሉ:: ሁለት ሆነው በየቦታው በፍለጋ ተንከራተቱ---ባዘኑ:: ያን የመጨረሻ ክፉ ነገር ማሰብ ባይፈልጉም ግድ ሲሆን ነበር ምኒልክ ሆስፒታል ለመሄድ የተነሱት::

ሬሳ ከፍል ተፈቅዶላቸው ሲገቡ ከሙታን ከተማ የገቡ ነበር የመሰላቸው። የከፍሉ ወለል በቁመታቸው ልክ በጀርባቸው ኗ ብለው በተዘረጉ ነፍስ አልባ ፍጡራን ተሞልቷል። ሌላ ጊዜ ፈሪና ደንጋጣ የነበረችው ራሔል ለዚያን ቀን ድፍረት ከየት እንዳመጣች እግዜር ይወቅ:: ክፍሉ ውስጥ እንደ ገባች አስከሬኖቹ የተሸፈኑበትን ላስቲክ እየገለጠች መፈተሹን የተያያዘችው ወድያው ነበር:: ስው ሁሉ የሚያውቀው ከራሔል ይልቅ የተሻለች ደፋርና ጠንካራ ትሩፋት እንደሆነች ነበር:: አባታቸው እንኳን

«ትሩፋት በአካልም ሆነ በመንፈስ ጠንካራ ናት:: እንደ ወንድ በሬ ጠምዳ አርሳ ትበላ ይመስለኛል:: ራሔል ግን እግዚአብሔር ሲፈጥራት ለስላሳና ልማልም አድርጎ ነው:: ክፉ ቀን ቢመጣ ችግር ትቋቋም አይመስለኝም» ይሉ ነበር:: የሁለቱን እህትማማቾች የመንፈስ ጽናትና የአካል ጥንካሬ እየተመለከቱ:: ያን ቀን ትሩፋት ምን እንደ ነካት አይታወቅም ገና አንደኛው አስከሬን የተሸፈነበትን ላስቲክ ገለጥ ከማድረጓ አቅለሸለሻት:: የልቧ ምት ጨመረ:: ሰማይ ምድሩ ዞረባት:: ፈጥና ከፍሉን ለቃ ወጣች:: የበላችው ነገር ባይኖርም ጥቁር ሀሞት እስከትተፋ ድረስ ልቧን ደግፋ አስመለሰች። ትሩፋት እንዲህ ስትሆን ራሔል ከሬሳ ክፍሉ ገና አልወጣችም ነበር:: እነዚያን ላስቲክ ለብሰው የተዘረጉ አስከሬኖች እየገለጠች ፍለጋዋንም አላቋረጠችም::

«ተመስገን ባይሆን የሞት አደጋ አልደረሰበትም ማለት ነው::» አለች ራሔል የሆስፒታሉን ግቢ ለቀው ሲወጡ::

«ግን እርግጠኛ ነሽ ራሔል ሁሉንም በሚገባ ፈትሸሻል?» አለች ትሩፋት አስከሬን ብሎ ለመጥራት እንኳን እየከበዳት::





«እንግዲያው ያንቺ ጀግንነትማ ታየልሽ እኮ! ገና ከመጀመርሽ ከከፍሉ በረሽ መውጣትሽ--- ግን ምን ነክቶሽ ነው ትሩፊ?» ለጥያቄዋ መልስ ሳትሰጣት ነበር የጠየቀቻት:: ጤንነቷ አጠራጥሯት ቆም ብላ እየተመለከተቻት::

«እንጃ ራሔል! እኔም የሆንኩትን አላውቅም:: ምናልባት እንቅልፍ ሳልተኛ ስላደርኩ ይሆናል» አለች ትሩፋት አሷም ቆም ብላ:: መላ አካሏ መዛሉና መድከሟ እያስታወቀባት::

«አይ! የእንቅልፍ ማጣት ብቻ አልመሰለኝም:: አሞሻል ትሩፊ:: በጤናሽማ እንዲህ ልትሆኚ አትችይም:: ሐኪም ሊያይሽ ይገባል» አለች ራሔል ስጋት ገብቷት::

«ራሔል ደግሞ! አሁን በዛሬው ቀን የኔ ጤንነት ያሳስብሻል በእናትሽ!? ጭንቅ! ከብድ! ያለ ነገር ገጥሞን ግራ በገባን በዚህ ሰዓት! እንዲህ በዋዛ ቤቱን ጥሎ በወጣበት እንደማይቀር የምታውቂውን ሰው እኮ ነው በመፈለግ ላይ ያለነው! ያ ለቤተሰቡ ከፍተኛ አክብሮትና ፍቅር የሚሰጠውን ሰው ሞት--ሽረት ለማወቅ እኮ ነው በመባዘን ላይ ያለነው!! የወደቀበትን እንኳ ሳናውቅ ደብዛው ጠፍቶ ሲቀር እያየሽ እንዴት ነው ሐኪም እንዲያየን የምትመክሪኝ!?» ደርሶ ከፍት አላት ትሩፋት:: ራሔል ምንም አላለችም:: ብትከፋም አልፈረደችባትም:: እውነትም ያ ለቤተሰቡ ትልቅ ኃላፊነት የሚሰማው--- ያ ለቤተሰቡ ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት የሚሰጥ ሰው ነው ድንገት ከቤቱ ወጥቶ የት እንደ ገባ ያልታወቀው::

«እሺ በቃ ተይው! ብቻ አንቺን አይመምሽ ደህና ሁኚ እንጂ ግድ የለም» ብላ ዝም አለች ራሔል::

«ይልቅ እርግጠኛ ነሽ? እያንዳንዱን ላስቲክ እየገለጥሽ በደንብ አስተውለሽ አይተሻል?» አለች ትሩፋት ራሔልን በመጠራጠርና እርግጠኛ ባለመሆን::

«አትጠራጠሪ ትሩፋት:: ሁሉንም አስከሬን እያስተዋልኩ በደንብ ፈትሼ አይቻለሁ:: ራስሽ እንዳየሽው ልትቆጥሪው ይገባል» አለች ራሔል በእርግጠኝነት::

«ነገሮች ሁሉ እንዲህ የተገላቢጦሽ ሲሆኑ አባታችን ከመቃብር ቀና ብሎ ማየት ቢችል ኖሮ ምን ይል ነበር ይሆን?» አለች ትሩፋት በውስጧ:: እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ እውነት--- እውነት አልመስልሽ ብሏት:: «ምነው ሁሉም ነገር በሕልሜ በሆነ» ስትል ተመኘች::

የአዲስ አበባ የመንደር ጉራንጉር ሁሉ አንድ አልቀራቸውም። ፍለጋቸው ሰው ያውም ራሱን በሚገባ የሚያውቅ ትልቅ ሰው ሳይሆን እቃ እንደ ጠፋው ነበር:: በአዲስ አበባ ምድር ግን አላገኙትም:: የትሩፋትን ባለቤት--- የልጆቿን አባት የበላው ጅብም አልጮኸም......

******

ትሩፋት ብዙ አለበች:: ብዙ ተጨነቀች:: ማድረግ የሚገባትን ሁሉ ያላደረገች እየመሰላት ብዙ ባዘነች:: ደከመች:: ሕዝብ ያያቸዋል ብላ ባለበቻቸው ቦታዎች ሁሉ አጥር ግንብ፣ ኤሌትሪከና ለልከ ምሰሶዎች ላይ ሁሉ ሳይቀር ፎቶውን አባዝታ ለጠፈች:: የገባበትን ወይም የወደቀበትን የሚያውቅ ወይም የሰማ ሰው ቢኖር ለጠቆማት ሁሉ ወሮታውን እንደምትከፍል አስታወቀች:: ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ «የአፋልጉኝ» ጥሪዋን በሬዲዮ አስተላለፈች። በግልና በመንግሥት ጋዜጦች ሁሉ የድረሱልኝ ጥሪዋን አዳረሰች:: ያገኘችው ተስፋ ግን አልነበረም....

ሦስት ቀን ሙሉ ከሥራ ገበታዋ ላይ አልተገኘችም:: ከዚህ በላይ መቅረት ደግሞ ያስጠይቃታል:: ከሥራ እስከ መፈናቀል የሚያደርስ ችግር ሊያጋጥማት ሁሉ ይችላል:: የሥራ ቦታዋ ደግሞ የምኒልኩን የሬሳ ክፍል ያህል ቀፈፋት:: ለምን እንደ ቀፈፋትም አላጣችውም:: ሁሉም ሰው ሊጠይቃት የሚችለውን ጥያቄ ገና ከወዲሁ ስታሰበው አስጠላት::

«ቤተሰቡ ያለ አንድ ሁነኛ ሰብሳቢ በአንድ ጀንበር መበተን የለበትም:: ሥራዬን መጀመር ግድ ነው» አለች ውስጧን ለማሳመን እየጣረች::

የሚያዚያዋ ፀሐይ እናት መብሳት የጀመረችው ገና በጧቱ ነው:: ትሩፋት ቅፍፍ እያላት ተነስታ ወደ ትምህርት ቤት ለትሄድ መንገዱን ሁሉ ራስ ምታት ለቆባት ነበር:: ቢሮ ገብታ መምጣቷን ለትምህርት ቤቱ ወጣት ዳይሬክተር ለአቶ ኃይለእብ ስታስታውቅ ሰላምታውን አስቀድሞ

«ለመሆኑ የት ገባ ይባላል?» አላት አይታውን ከእሷ ላይ ሳይነቅል::

«የገባበትን ባውቅማ ኖሮ እኔስ ሙች በየቦታው የአፋልጉኝ ጥሪ አቀርብ ነበር» አለችው ኮስተር ብላ:: ልጅ እግሩ ዳይሬክተር ከዚህ በላይ ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ አላቀረበላትም:: የእሷ ኮስተር ማለትና ሁኔታዋ ለሌላ ጥያቄ አይጋብዝም:: ከሰዓት መፈረሚያው ላይ ፊርማዋን አኑራ ስትሄድ ሁሉ ከኋላዋ በአግራሞት እየተመለከታት ነበር:: ሁሉም የትምህርት ቤቱ መምህራን አንድም ወሬ ፍለጋ--- የምርም ከልባቸው በማዘን ሲያጽናኗት ጠይቀዋታል:: እሷ ግን በዚህ ጊዜ የማንንም ማጽናኛም ሆነ ከንፈር መጠጣ አልፈለገችም:: ብትችል ኖሮ እቤቷ ብቻዋን መሆንን ነበር የምትመርጠው:: የምርጫዋን ማድረግ ባለመቻሏ ግን ቀኑን ሙሉ ከሚያስጨንቃት ሐሳብ ጋር ስትታገልና የሰውን ፊት ለትሸሽ ዋለች:: እንደ ሁልጊዜው ሥራዋን በትጋትና በጥንካሬ መስራት አልቻለችም:: እንደ ምንም ታግላ ሐሳቧን ሰብስብ አድርጋ ሥራዋ ላይ ብቻ ለማድረግ ብትጥርም





አልሆነላትም:: ፍዝዝ---- ድንግዝ ስትል ነበር የዋለችው:: አንድ ከፉ ነገር እንደ ገጠማትና ሀሳብ እንደ ገባት ተማሪዎቿ ሳይቀር አውቀውባታል::

«ቲቸርዬ ዛሬ አሞዎታል አይደል? ቲቸርዬ ዛሬ የደከመዎት ይመስላሉ:: ቲቸርዬ እቤትዎት ሄደው ቢያርፉ ይሻላል....» እያሉ የጠየቋትና ሐሳብ ያቀረቡላት ተማሪዎች ብዙ ነበሩ:: ቀኑን ሙሉ እንዲሁ በድን አካሏ ሲወዛወዝ ዋለ::

******

ቀኑ እየሄደ ነው:: ትሩፋትም ቀን በሄደ መጠን ተስፋዋ እየተሟጠጠ:: ሆኖም ባገኘችው አጋጣሚና ጊዜ ሁሉ ማጠያየቋና ማፈላለጓ አልቀረም:: ከራሔል ጋር እየተፈራረቁ በየፖሊስ ጣቢያው ይባከናሉ:: ሰንቅ እየያዙ ስሙን ያስጠራሉ:: «አለ» ብሎ ሰንቁን የተቀበላቸው ፖሊስ ጣቢያ ግን አልነበረም::

ለሞኑን እንደሚያደርጉት ሁሉ አንድ እሁድ ቀን በየፖሊስ ጣቢያው ሲንከራተቱ ውለው እቤት ከመግባታቸው ስልኩ ጮኸ:: ትሩፋት ልቧ በካራ እንደ ተከፈለ ዱባ ከሁለት ትርክክ ያለ መሰላት። አንዳች ወሬ ለመስማት የምትጓጓውን ያህል መስማት ደግሞ አትፈልግም:: ትፈራለች:: የሚመጣውን ወሬ ሁሉ ባትሰማው ይሻላት ይመስላታል:: እንደገና ደግሞ እዚህ ቦታ ወይ ደግሞ እዚህ ፖሊስ ጣቢያ እንደው የትም ይሁን የት--- ብቻ ከሆነ ቦታ--- እንዲህ ሆኖ--እንዲያ ሆኖ የሚል በሕይወት የመኖሩን ወሬ ማግኘት አጥብቃ ትመኛለች፤ እናም የሆነ ወሬ መስማት የምትፈራውንና የምትጠላውን ያህል በዚያው መጠን ደግሞ ለመስማት ትጓጓለች:: መላው ጠፍቷታል:: ግራ ግብት ያለ ነገር ገጥሟታል:: ስልኩ ላይ አፈጠጠች። ለሞኑን ስልክ በጮኸ ቁጥር እንዲሁ ነው ስትሆን የሰነበተችው። ሆኖም አልቀረላትም የስልኩን እጀታ አነሳች::

«ሀሎ!» አለች:: ድምጿ ሲንቀጠቀጥ ታወቃት።

«ሀሎ! እንደ ምን ዋላችሁ?» አለ በወዲያኛው መስመር ያለው ሰው::

«እግዚአብሔር ይመስገን:: ማን ልበል?» አለች ትሩፋት በተረበሸ ድምጽ::

«እኔን እንኳን አያውቁኝም:: ወይዘሮ ትሩፋትን ፈልጌ ነበር» አለ ያው ሰው:: ሰም መንገሩን ቸል ብሎ::

«እኔ ራሴ ነኝ» አለች ቀልጠፍ ብላ:: ለጆሮ ደስ የሚል ወፈር ብሎ ረጋ ያለ ድምጽ ነው። ትሩፋት ግን እንደ መርዶ ነጋሪ ፈራችው። ልቧ ደረቷን ሰንጥቃ እንዳትወጣ የፈራች ይመስል ስልክ ባልጨበጠ እጇ ጫን አድርጋ ደረቷን ያዘች ::

«በየቦታው የለጠፉትን ፎቶግራፍ አይቻለሁ። እ--- ምናልባት ይረዳዎት ከሆነ እ---- እ---- » ሰውየው ንግግሩን ለትንሽ ጊዜ አቋርጦ ጸጥ አለ። የእሷም ትንፋሽ አብሮ ቀጥ ሲል ደረሰ። ረጋ ጎተት ያለው ንግግሩ ዓመት የወሰደ መሰላት።

«እርብ ሚያዚያ ሃያ እራት ቀን ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ---- ካዛንችስን ያውቁታል ብዬ እገምታለሁ---- ያውቁታል አይደል?»

«አዎ አውቀዋለሁ» አለች በዚያው በሚንቀጠቀጥ ድምጿ። «እህ! አሁን ምን አለበት የሆነውን ነግሮ ቢገላግለኝ!» አማረረች በውስጧ። ሰውየው ተናግሮ ሳይጨርስ ምቷን ልታቆም የደረሰች ልቧን አያዳመጠች።

«ከስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ወረድ ብላ ባለችው ቀጨን አስፋልት መንገድ ቁልቁለቷ ላይ እ---» ትንፋሽ ለመውሰድ ድምጹ ለሰከንድ ጸጥ ብሎ በጠፋ ቁጥር የምዕተ-ዓመት ያህል አየረዘመባት ተጨነቀች። የልቧ ምት በእጥፍ የጨመረ መሰላት። ከለበሰችው ቢጫ ከነቴራ በላይ እስኪታይ ድረስ ተንደፋደፈች። ከሰከንዶች ከቆይታ በኋላ

«ጠፋ የሚሉት ሰው ረዘም ደልደል ያለ ቁመና ያለው ነው አይደል?» ይባስ ብሎ ሌላ ጥያቄ ጨመረላት

«አ--ዎ ትክክል ነዎት» አለች የሞት ሞቷን።

«የቀይ ዳማ?» እንደ ገና ሌላ ጥያቄ « ልክ ነው፤ ትክክል ነዎት» አለች ደግማ። ጨሂ--ጨሂ የሚል ስሜት እየተናነቃት።

«እንግዲያው ቅድም በገለጽኩልዎት ቀንና ሰዓት ቁመቱ ረዘም---አካሉ ደግሞ ደልደል ያለ የቀይ ዳማ ሰው--- በታጠቁ ለዎች ታርጋ ቁጥር በሌላት ነጭ ቶዮታ መኪና በግዳጅ ተገፈታትሮ ታፍኖ ሲወሰድ አይቻለሁ። ከለጠፉት ፎቶግራፍ ጋር ሳገናዝበው መልኩ እርሰዎ የሚሉት ሰው ለመሆኑ አያጠራጥርም። እስቲ በየፖሊስ ጣቢያው ያፈላልጉ። አግዜር ይርዳዎት።»

አመሰግናለሁ ለማለት እንኳ ጊዜ ሳይሰጣት ስልኩ ተዘጋ። ተቋርጦ መስሏት ደጋግማ ሀሎ አለች። መልስ የለም። ዐይኗን ከስልኩ እጀታ ላይ ተክላ በተቀመጠችበት ፍዝዝ--ድንዝዝ እንዳለች ቀረች። ሁሉም ነገር ዞረባት። ሀሳቧ ሁሉ ከውስጧ ብን ብሎ ጠፍቶ ጭንቅላቷ ባዶ ቅል የሆነ መሰላት። እጇን ሶፋዉ መደገፊያ ላይ አነባብራ በግንባሯ ደፋ አለች። ዐይኗን ጨፍና ወደ ውስጧ ተመለከተች። ማለቂያ የሌለው ሐሳብ ጓዙን ጠቅልሎ ቀ--ሰስስ እያለ ሁለንተናዋን መቆጣጠር ጀመረ።





«ምንድን ነው የስልኩ መልእክት? ነገሩ ምንድን ነው ተባለ?» ጥያቄዋን አከታተለች ራሔል የሆነውን ለመስማት ጓጉታ።

«'በታጠቁ ኃይሎች ታፍኖ ተወስዷል' ነው የሚለው» አለች ትሩፋት በአጭሩ። በግንባሯ ከተደፋችበት የሶፋ መደገፊያ ላይ ቀና ብላ ራሔልን እየተመለከተች።

«ም--ን!? ማን ነው እሱ? ከየት ነው የደወለው? ምን ማለት ነው ታፍኖ ተወስዷል ማለት? እነማን ናቸው ያፈኑት?.... » ራሔል የጥያቄ መዓት ደረደረች ድንጋጤ መላ አካሏን አርዶት እየተርበተበተች።

«ማን እንደ ሆነ አላውቅም ራሔል። ስሙንም አልተናገርም። ብቻ ካዛንችዝ አካባቢ ታርጋ ቁጥር በሌላት ነጭ ቶዮታ መኪና በታጠቁ ኃይሎች በግድ ታፍኖ መወሰዱን ነግሮኛል» አለች ትሩፋት ተስፋዋ ከውስጧ በኖ እየጠፋ። ራሔል የምትለው ነገር አልነበራትም። እሷም ፍዝዝ ብላ ሄዳ ሶፋው ላይ በቁሟ ዘፍ አለች።

«ሀሎ! ወይዘሮ ትሩፋትን ነበር...» ብዙ የስልክ ጥሪዎች ደረሷት። መልዕክቱ ግን አንድ ነበር---! «በታጠቁ ኃይሎች ታፍኖ ተወስዷል።» በቃ ይኸው ብቻ!......

«የታጠቁ ኃይሎች እነማን ናቸው? አፋኞቹ እነማን ይሆኑ? አፍነው የት ይሆን የወሰዱት? እስካሁን ምን አድርሰውበት ይሆን? ወደ የት ይሆን የሚሄደው? ማን ይሆን የሚጠየቀው? ከእንግዲህ ሕይወት በብቸኝነት እንዴት ይሆን የምትገፋው....?» መልሰ ያላገኘችላቸው ብዙ--ብዙ ጥያቄዎች ተግተልትለው አዕምሮዋን አስጨነቁት።

"ግበድ እንዴት ይሆን የሚያደርገው?» ሌላ አስፈሪ ጥያቄ ጨመረች ለራሷ። ያም ሆኖ ሙብሰልሰሏን አላቋረጠችም። በታጠቁ ኃይሎች አፍኖ እስከ መውሰድ የሚያደርስ የግል ጠላት እንደ ሌላቸው መቶ በመቶ እርግጠኛ ናት። የአዲስ አበባ ማጅራት መቺዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ ደግሞ ሳይታለም የተፈታ ነው። ታርጋ ቁጥር የሌለው መኪና ሊይዙ የሚችሉና የጦር መሳሪያ የታጠቁ ማጅራት መቺዎች በአዲስ አበባ ምድር መኖራቸው እስከ ዛሬ ተሰምቶ አይታወቅም። ዛሬ ለእሱ ለአንድ ሰው ሲባል በአንድ ሌሊት ተፈጥረው አያድሩም። መሳሪያ የታጠቁ ኃይሎች ደግሞ እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ስታስብ ሰጋቷና ፍርሀቷ ጨመረ። የአምባገነኑ የደርግ መንግሥት የአፈናና የወከባ ጊዜ በዐይነ-ሕሊናዋ መጣ።

እጹ ኃይለሥላሴ ለስልጣናቸው ያሰጋሉ የሚሏቸውን ሰዎች በግፍ ሰቅለዋል--- አግዘዋል-አስረዋል እንዲሁም አሳፍነው ሰውረዋል። ወታደራዊው የደርግ መንግሥት በስልጣኑ የመጣ የመሰለውን ሁሉ አይቀጡ ቅጣት ቀጥቷል። አስራ ሰባት ዓመት ሙሉ ሕዝብ አስለቅሷል። ትሩፋት ባሳለፈቻቸው የግማሽ ምዕተ ዓመት እድሜዋ ውስጥ ያየቻቸው ሦስት መንግሥታት ለስልጣናቸው ያሰጋሉ ብለው የሚጠረጥሯቸውን ሰዎች ሕግ ፊት

ማቅረብ ሲችሉ የቤተሰብን ስቃይ ለማብዛት እፍነው ይለውራሉ:: በዚህ አሰራራቸው አንደኛው ከሌላው ተሽለው አላገኘቻቸውም:: እንደውም መንግሥት በተቀያየረ ቁጥር በደልና ግፍ እየከፋና እየባሰ ዜጋን እያስጨነቀ መሄዱን ነው ያስተዋለችው:: ያውም ጥፋተኛንና ወንጀለኛን የሚቀጡ ፍትሃ ብሔርና ወንጀለኛ መቅጫ የተባሉ የሕግ መጻሕፍት በተረቀቁባት፣ የሕግ ተቋማት አሉት እየተባለ በሚነገርባትና በሚፎከርባት አገር-- ኢትዮጵያ::

«ሰው አገሩ ላይ በሰላም ወጥቶ በሰላም የመግባትና የመኖር ዋስትና ከሌለው እንዴት ነው መኖር የሚቻለው? ከዚህ የበለጠ ነጻነት ማጣትስ በዓለም ላይ ይኖር ይሆን? የዚች አገር ጉዞ ወደ የት እያመራ ይሆን?» የደርግ የአፈናና የግድያ ጊዜ ለሁለተኛ ጊዜ በዐይኗ ስር ድቅን አለ:: እነኛ ያሳለፈቻቸው የብቸኝነት ዓመታት ታለቧት:: በትግልና በጥንካሬ አልፋቸው ዛሬ ላይ ደርሳለች:: አሁን ግን ልጆቻቸው አድገው ጎጇቸው በሞቀበት በዚህ ወቅት እንዲህ ከቁጥጥሯ ውጭ በሆነ ድንገተኛ ዱብዳ «ትዳሬ ይፈርሳል» ብላ አልጠበቀችም:: በዚህ ሰዓትና ጊዜ እሷም ያለ ትዳር አጋሯ--- ልጆቿም ያለ አባት የመሆናቸውን አጋጣሚ አምኖ የመቀበል አቅም አጣች:: ለእንዲህ ዓይነቱ ድንገተኛ ዱብዳ ዝግጁ አይደለችም---በፍጹም! እንደ ደርግ ዘመነ መንግሥት ጠንካራ ሞራልና ጠንካራ የመንፈስ ብቃት የላትም::

«ዛሬስ በጥንካሬ መቋቋም የምችል አይመስለኝም:: ሰው ዘመኑን ሁሉ ሲታገል መኖር ይሰለቸዋል---!ይመረዋል--! ያንገፈግፈዋል----! ለዚያውም ላልተገኘ ድል--- ላልመጣ ዲሞክራሲ--- ላልተገኘ ፍትሕ-ርትህ---ላላደገችና ላልተለወጠች አገር» አለች በቁጭት:: ውስጧን ፈተሸች:: ብርታት እንደ ሌላት ተሰማት:: መንፈሷ እንደ ብርጭቆ ከሽከሽ ብሎ የተሰባበረ መሰላት፤ አካሏ ጭምር ድቅቅቅ ያለ--- ያ የነበራት ብርቱ ወኔ በውስጧ የለም:: ደከማል! ታከቷታል! ለመጀመሪያ ጊዜ ከእድሜዋ በላይ ያረጀች መሰላት::

ለወትሮው «እርጅና ቁጥር አይደለም:: እርጅና ማለት ያለ ሞራልና ያለ ምክንያት መኖር የጀመሩ እለት ነው» ትል ነበር ከጓደኞቿ ጋር ስለ እድሜ ሲጨዋወቱ::

«ያለምክንያት ረጅም እድሜ ከመኖር ምክንያት ያለው አጭር እድሜ ሺህ ጊዜ ይበልጣል:: መኖር-- እየበሉና እየጠጡ መተኛትና መነሳት ብቻ ከሆነ ምክንያታዊ አይደለም:: ያለ ምክንያት መኖር ማርጀት ብቻ ሳይሆን ወደ እንስሳነትም መውረድ ነው:: ለመኖር ቢቻል ለሰው ዘር በሙሉ---ከዚያ ዝቅ ሲል ደግሞ ለአገርና ለወገን የሚፈጽሙት አንድ በጎ ዓላማ ሊኖር ይገባል» የሚል ፍልስፍና ነበራት:: አሁን ግን በተለይ በዚች አገር ላይ ለመኖር ምክንያት አጣችለት:: መንፈሷም አካሏም ከዘመኗ በላይ ውድቅድቅ--እርጅትጅት ያሉባት መሰላት:: መኖር አስጠላት::





«ሞት ምን ይመስል ይሆን?» ደግማ ሌላ አስፈሪ ጥያቄ ራሷን ጠየቀች:: ከእንዲህ ዓይነቱ ኑሮ ሞት ግልግል እንደሚሆን አልተጠራጠረችም:: ግን ብዙ ኃላፊነት አለባት:: ሌላው ቢቀር ቤተሰቡ የእሷ የመኖር ምክንያት ነው:: ልጆቿ አባታቸውን አጥተው እናታቸውንም ማጣት የለባቸውም:: እሷ ባትፈልግም መኖሯን የሚሹ ብዙ ነፍሶች አሉ:: መኖር ግድ ሆነባት::

******

ተስፋዬ አብሮ አደጓ ነው:: የጎንደር ከፍለሀገር የፖለቲካ ሁኔታ አላኖር ሲላቸው ለፈ ከተማ ይሻላል በማለት ሁለቱም ዝውውር ጠይቀው አዲስ አበባ የገቡት አብረው ነው:: ዛሬ ጓደኝነቱ ቤተሰባዊ ሆኗል:: በደግ በከፉ ይገኛኛሉ:: በአድካሚው የሕይወት ጉዞዋ ውስጥ እስከ መጨረሻው ያልተለያት ሰው ቢኖር ተስፋዬ ነው::

«ተስፋዬ ችግሬን ለመጋራት የምታደርገው ጥረት ሁሉ ሰው ጨርሼ እንዳልጠላና ሰው እንዳልሸሽ ረድቶኛል:: አብረውኝ የበሉ--አብረውኝ የጠጡ-- በደህናው ቀን አብረውኝ ቸበር ቻቻ ያሉ ወዳጆቼ ዛሬ አጠገቤ የሉም:: ብቻ 'ሰው ጥሩ ሰው ከፉ' ትል ነበር እናታለም የምላት እንደ እናቴ የምወዳት አክስቴ:: የለማይ ቤቷን ያብጅላት፤ ፍቅር አዋቂ መልካም ሰው ነበረች-- ተረጩ ታምራት::» ብላ ትካዝ አለች ትሩፋት::

«የሰውን አመጣጥ ታሪክ እንደ ተማርነው ሰው ብቻውን መኖር የማይችል ማኅበራዊ እንስሳ ነው:: ግን ደግሞ ሰው ራሱን ከምንም በላይ ስለሚወድ በመሰሉ ላይ ሲጨክንና በወገኑ ላይ ሲከፋ ልክ የለውም:: ያም ሆኖ ሰው ያለሰው መኖር አይችልም:: ሰው ያለሰው ጉልበት አያገኝም:: ያለጉልበት ደግሞ እድገትና ብልጽግና አይመጣም» አለና ወድያው

«እ--ው!! ይቅርታ ትሩፌ--- የኔ ነገር ዲሞ ትዝ አለችኝ መሰል:: እንደ ዱሮው ውይይት ውስጥ ላስገባሽ ነበር:: የመጣሁበትን ትልቅ ቁም ነገር ትቼ» አለ ተስፋዬ:: «ምን ዓይነት የፖለቲካ ልክፍት ይሆን እያዞረ---- እያዞረ እዚያው አዙሪት ውስጥ መልሶ-- መላልሶ የሚከት?» እያለ ራሱን እየታዘበ ነበር በውስጡ::

«እውነት ብለሀል ተስፋዬ ሰው አንደ ኮሶ እያንገሸገሸውም ቢሆን ያለሰው ብቻውን መኖር የማይችል ደካማ ፍጡር ነው:: እግዜሩም ይህንን ድክመቱን ተገንዝቦ ሳይሆን አይቀርም ለአዳም ሔዋንን የፈጠረለት:: ይህንን ስንነጋገር ምን ትዝ እንዳለኝ ታውቃለህ?» አለች ትሩፋት ውስጧ ባይለቅም ፈገግ ለማለት እየሞከረች::

«ከበደ ሚካኤል በውብ ብዕራቸው የጻፉት 'ሰውና ዝንጀሮ' የሚለው ግጥም ነው አይደል? ያ ከሰው ተለይቶ ሄዶ የዝንጀሮ ጓደኛ አበጅቶ ሲኖር ስለ ምተው ሰው መሆን አለበት ያስታወሰሽው» አላት ተስፋዬ::

«በእውነት! እሱ ነበር ትዝ ያለኝ፡፡ ግን እንዴት አወቅህ?» አለች ትሩፋት የሐሳባቸው አንድ መሆን እየገረማት፡፡

«የዚያ ትውልድ አባልና ከአንድ ወንዝ የተቀዳን መሆናችን ተዘነጋሽ እንዴ ትሩፋት? በይ ወደ መጣሁበት ጉዳይ እንግባ፡፡ ወደ ዚያ ወንዝ ከወረድን መመለሻ የለንም» አለ ተስፋዬ፡፡

«ትክክል ብለሀል ተሰፋዬ ባሕሩ ውሰጥ ከመግባታችን በፊት ድንበሩ ላይ ባሕሩ ውሰጥ ከገባን መውጫ የለንም፡፡ እዚያው ገብተን ሰንበጫረቅ መዋላችን ነው፡፡»

«ከተለከፍንበት የፖለቲካ ልከፍት ማርከሻ ጸበል ካላገኘን መቼም ቢሆን መዳኛ የለንም፡፡ ንኮች ነን--ንኮች! ያ ባይሆን ኖሮ ታድያ አሁን በዚህ ጭንቅ ሰዓት መነሳት የሌለበትን ነገር እኮ ነው የምንነጋገርበት፡፡ በጣም እናሳዝናለን! በይ ትሩፌ ከፖሊሱ ጋር ምን ማድረግ እንደሚኖርብን እንነጋገር» አለ ተሰፋዬ፡፡

«ንኮች ለለ ሆን መስሎህ ነው ተሰፍሽ? ንኮችና የፖለቲካ ሀራራ ኖሮብን አይመስለኝም፡፡ ተነስተንለት የነበረው በጎ ዓላማ ግቡን ሳይመታና ሳይቋጭ በመቅረቱ ይመስለኛል እኔስ፡፡ በል ወደ ተነሳንበት ጉዳይ እንግባ፡፡ ይኸ ፖሊስ ነው የምትለውን ሰው እምኙ መቀበል ከብዶኛል፡፡ እንዴት መደራደር እንዳለብኝም አላውቅም፡፡ አንተን ከመሰለህና ካመንከበት ግን እሺ ይሁን» አለችው ተሰፋዬን እንዳይከፋው፡፡

«ገንዘቡ አሳሰበሽ ከሆነ አታስቢ ትሩፌ-- እንተጋገዛለን፡፡ ለዚህ ጊዜ ያልሆንኩሽ ለመቼ ልሆንሽ ነው? ደግሞም እኮ የአንቺ ጉዳይ የኔ---ችግርሽ ችግሬ መሆኑንም አትርሺ» አለ ተሰፋዬ፡፡ በሁሉም ነገር ከጎኗ እንደሚቆም እያረጋገጠላት፡፡

«ለገንዘቡ ሳይሆን ጥሎብኝ ወታደር ብዙ አላምንም፡፡ ሁለት ነገር ነው ይዞብህ የሚመጣው፡፡ አንድም ከእፍህ ነገር ለመልቀምና መረጃ ለመሰብሰብ ወይ ደግሞ ከልቡም ሊሆን ይችላል፡፡ ብቻ እንጃ! ወታደር እፈራለሁ፡፡ የድሮው መጥፎ ትዝታ ገና ከውስጤ አልወጣም መሰል፡፡ እነዚህ ደግሞ የዋዛ እንዳይመስሉህ፡፡ ልባቸው የማይገኝ--- ነገረ ስራቸው የማይታወቅ ምስጦች ናቸው፡፡ ለማንኛውም አንተ ካመንከበት እንግዲህ ይሁን» አለች ትሩፋት ውስጧን ቅር እያለው፡፡

«ግድ የለሽም ትሩፋት ይሞከር፡፡ የምናገኘው ሁለታችን ብቻ ነን፡፡ ምን እንዳያመጣ ነው? እሱው ከሳሽ---እሱው ምስከር-- ራሱ ዳኛ ሆኖ መቼም አይወነጅለንም፡፡ የምንነጋገረው ደግሞ ገንዘብን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ የሚያስፈራሽ ነገር የለም፡፡ ከሆነ ይሆናል ካልሆነም ይቀራል፡፡ የምናገኘው ነገር ከሌለ የምናጣው ነገርም አይኖርም» አለ ተስፋዬ እያበረታታት፡፡





በዚህ የጭንቅ ጊዜ እንዲህ ያለ ሰው አጠገቧ በመኖሩ ተሰፋ በሌለበት ውሰጧ ተስፋ ዘራ፤ እና ፈገግ ለማለት እየሞከረች «አመሰግናለሁ ብልህ ያን የመተሳሰብ ዘመን ፍቅር ይቀንሰው ይሆናል ብዬ ሰጋሁ» አለችው ዐይን ዓይኑን እያየች፡፡

«ለምን ታመሰግኝኛለሽ ትሩፌ? ያንች ጉዳይ የእኔም ጉዳይ ነው አልኩሽ አይደል» አላት እሱም በተራው ዐይን ዐይኗን እየተመለከተ፡፡ ሁለቱም በውሰጣቸው ተናበቡ፡፡ የሁለቱም ልቦች ዓመታትን ወደ ኋላ ሄደው አንድ መሰመር ላይ ተገናኙ፡፡«የትግሉ ነው ሕይወቴ!» የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ፡፡

ተሰፋዬ ከሰውዬው ጋር እሱም በተገኘበት ለመነጋገር ቀጠሮ ተቀበለ፡፡

******

ግንቦት 15 ቀን 1989 ዓ.ም

ቱሪስት ሆቴል--ሰዓት 10፡30

ትሩፋት ወታደሩን ገና ስታየው ነበር ቀልቧ ያልወደደው፡፡ የሆነ ቀትረ ቀላል ሆኖ ታያት፡፡ ይልቁንስ ሌላ ችግር ውስጥ እንዳትገባ ፈራች፡፡ ከውስጧ ሐሳብ ጋር እየተብሰለሰለች እያለ ሽቁጥቁጡ የቱሪስት ሆቴል አስተናጋጅ መጥቶ «ምን ልታዘዝ» አለ እጁን የኋሊት አጣምሮ ከወገቡ ሰገድ እያለ፡፡ ከሐሳቧ ብንን ብላ ቅድሚያ ወታደሩ እንዲያዝ ጋበዘችው፡፡ ቢራ አዘዘ፡፡ ትሩፋት ለስላሳ አዘዘች፡፡ ተስፋዬ «ለእኔም ለስላሳ ይሁንልኝ» ሲል

«እንዴ! ተስፋዬ አንተማ ቢራ ያዝ እንጂ እኔ እንኳን አሁን ናላዬ ዞሮ ድሮም መጠጥ ላይ ብዙ እንደማልታማ ታውቃለህ፡፡»

«ዋይ! እኔንም ለብቻዬን ቢራ ስጠጣ ታሳፉሩኛላቹሀ፡፡ ባይሆን አንቴ ለእኔን ሙሰል» አለ ወታደሩ፡፡ ተስፋዬ ባይፈልግም ስውየውን ለመምሰል ቢራ አዘዘ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ዝም ዝም ከተባባሉ በኋላ ተስፋዬ

«ትሩፋት ያው አንግዲህ እንደ ነገርኩሽ ያልኩሽ ሰው እሱ ነው፡፡ ኮንስታብል ካህሳይ ይባላል፡፡ ጉዳዩን አሳውቄዋለሁ ወደ ዋናው ቁም ነገር በመግባት መወያየት ይቻላል» አለ ተስፋዬ ሁለቱንም ለውይይት እየጋበዘ፡፡

«አዎ ይሻላል፡፡ ለፍሬ ነገሩን እኑነጋገር፡፡ እኔም አንዲ አንደ ናንቴ ሽግር ከገጠማቸ ሰዎችን ጋር አንድ ሌላ ቀጦሮ አለኝ፡፡ ፎጠንን ፎጠን አድርገን ቶሎ አንጨርሽ» አለ ኮንስታብል ካህሳይ፡፡ ቸኩሏል፡፡

«መልካም፡፡ መወያየት እንችላለን» አለች ትሩፋት፡፡

«እንግዴ ለእሱን ለጓኛዬን ከነገረኝም በተጨማሪ በየቦታውን የሎጠፉሻቸውን የአፈሉጉኝ ጡሪሽንና ለፎቶግራፉን አይቻሎህ፡፡ ለጉዳዩን በሚገባ እጡንቻሎህ» አለና የቢራ ብርጭቆውን ብድግ አድርጎ ወደ አፉ ሲወስድ ትሩፋትን በዐይኑ ሥር ተመለከታት፡፡ ሁኔታዋን ለማጥናት የፈለገ ይመስላል፡፡ ከፊቷ ላይ ግን ምንም ነገር ማንበብ ባለመቻሉ ብርጭቆውን ወደ ጠረጴዛው መልሶ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

«ለዚ ተሰወረ ለምቱይውን ሰውስ እኔ በሙሠራቤት በሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ እንደሚገኝ አረጋግጥልሻሎህ፡፡ ግን ለቤተሰቡን ሆነ ለሌላ ሰውን እንዳያገኝ ቶኮልከሎ ለብቻውን ነው የታሰረ፡፡ ለጉዳዩስ በከፉተኛ ሙሥጢር ቶይዞዋል፡፡ በከባድ የፖለቲካ ወንጀል ተጦርጥሮ ነው ቶይዞ ያለው...»





«እሱስ ይሁን እሺ-- ቤተሰብ እንዳያየውና እንዳይጠይቀው አፍኖ መሰወር ተገቢ ነው!? ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ እንኳ ሕግ ፊት አቅርቦ ማስቀጣት አይቻልም ነበር!? አንድ ትልቅ አገርና ትልቅ ሕዝብ ከሚያስተዳድር መንግሥት ይህ ይጠበቃል!? ሕጻናት ልጆቼና እኔ ባልሠራነው ወንጀል እንድንሳቀቅና አንድንቀጣ የተፈረደብንስ ምን ስላጠፋን ነው!?» ንግግሩን አቋርጣ አከታትላ ጠየቀችው፡፡ ስሜቷን መቆጣጠር አቅቷት በንዴት ነበር የምትጠይቀው፡፡ ተስፋዬ ደጋግሞ በዐይኑ ጠቀስ እያደረገ ዝም አንድትል ምልክት ቢያሳያትም መታገስ አልቻለችም፡፡ የማያስፈልግ ነጥብ ውስጥ የገባች መሆኗን የተገነዘበችው በኋላ ነው፡፡

«ዋይ! ለዚህን ጉዳይስ እኔ ማሱረዳት አይጦበቅብኝም፡፡ ለዚ ጉዳይ ለእኔን አይሞለከተኝም፡፡ ለእኔና እናንቴ የቶገናኘንበት አግባብ ሌላ ነው» አለ አሁንም ብርጭቆውን እያነሳ፡፡

«ልከ ነህ ኮንስታብል ካህሳይ፡፡ ወደ መጣንበት ነጥብ እንግባ፡፡ አንተ ልትረዳን የምትችለው በምን ሁኔታ እንደ ሆነ ልታብራራልን ትችላለህ?» አለ ተስፋዬ» አለሳልሶ፡፡ የትሩፋት የስሜት መለዋወጥ አስግቶት፡፡

«እኔ ልረዳቹህ የምችሎ በሕይዎቱን ለሞኖሩን እንድታውቁ ማድረግ ብቻ ነዎ» አለና ወደ ትሩፋት ተመለከተ፡፡ ተስፋዬ ዝም ብላ በትዕግስት እንድታዳምጠው ደጋግሞ በዐይኑ ምልከት አሳያት፡፡ እደብ ገዝታ ንግግሩን እንዲቀጥል ጠበቀችው፡፡

«በሕይዎት ለሞኖሩን እንዲረዳሽ ሲታሰር ይዟቸውን ከነበሩ ነገሮችን ለአንዱን ላመጣልሽ እችላሎህ፡፡ ለዚ የማደርጎ ዶሞ በሕይዎቴ ቆርጬ ነዎ፡፡ የሰውን ጭቆት ስለሚገባኝ እንጂ ለገንዘቡን ብቻ ብዬ እንዳልሆነ ልቱረጅልይ ይገባል፡፡ ብዙ ከፉያም አሉጦይቅም» ብሎ ዝም አለ፡፡ ትሩፋትና ተስፋዬም በጸጥታ ጠበቁት፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ንግግሩን ራሱ ቀጠለ፡፡

«ለመጀመርያውን ሁለት ሺህ አምስት ሞቶ ብር ቀብዲ እወስዳሎህ፡፡ ፖሊስ ጣቢያው ውስጥ ለመኖሩ አርጉጠኛ እንድትሆኚ በቂ መረጃ ስሶጥሽን ዶሞ ቀሪውን ሁለት ሺህ እምስ ሞቶ ብር ትከፉይኛለሽ፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡» ሲናገር ፈጠን ፈጠን ይላል፡፡ ቀጭን መጣጣ ጠይም ፊቱ ላይ ምንም ዓይነት ነገር ለማንበብ ይቸግራል፡፡ ስለገንዘቡ ሲናገር እንኳ ሕገወጥ ሥራ እየሰራ መሆኑ ያሳሰበው አይመስልም፡፡ ትሩፋትና ተስፋዬ ድፍረቱ ደንቋቸዋል፡፡

«በአጠቃላይ አምስት ሺህ ብር መሆኑ ነው አይደል?» ጠየቀች ትሩፋት፡፡

«እዎ!! በሁለት ጊዜ ከፉያ የሚጦቃሰል ማለት ነው» አለ ኮንስታብል ካህሳይ ቀሰል እያርጎ፡፡

«መልካም፡፡ ግን ግልጽ ሆኖ ያልገባኝ ነገር አለ...» ልትናገር የነበረውን ሳትጨርስ አቋረጣት፡፡

«እሺ ምኑ ላይ ነዎ ያሉገባሽ? ለከፋያውን በቶምለከተ ከሆነ ግልጽ ነው፡፡ መቼም እንደ ጉሊት ሽንኩርቲ ገበያ ከርከር ውሰጥ እንደማቁገቢ እሩግጠኛ ነኝ» አለ፡፡ እጁን ጭምር «አይሆንም» በሚል ዓይነት እያወናጨፈ፡፡

«ለመከራከር ሳይሆን እንደው በግልጽ ተነጋግሮ ለመተማመን ያህል ነው» አለች ለመለሳለስ እየሞከረች፡፡ የቅድሙ ሁኔታዋ ትክክል እንዳልነበር ገብቷታል፡፡

«እዎ ሁቅሂ!-- እውነት አለሽ፡፡ ሞተማመን ከሌለስ ሥራ ለመሰራትን እሽጋሪ ነው፡፡»

«እንደዛ ከሆነ መጀመርያ ለምሰጥሀ ሁለት ሽህ አምሰት መቶ ብር ምን ዋሰትና ይኖረኛል? ማለቴ በሕይወት ለመኖሩ እርግጠኛ እንድሆን የምታመጣልኝ መተማመኛ የእሱ ባይሆን? ወይ ደግሞ ለማግኘት ብትቸገርና ሳይሳካልህ ቢቀር የሚቀጥለው እርምጃ ሊሆን የሚችለው ምንድን ነው? ገንዘቡን ማግኘት የምችለ...» አሁንም ሀሳቧን ሳትጨርስ አቋረጣት፡፡

«ሰሚኢሞ ለባለጉዳዩዋለ አንች ነሽ፡፡ ልታሙኝኝ ካልቻልሽ መቅረት ይችላል፡፡ ለማኑኛም ግን በሁለታችን መካከል ያው እሱ ወንድሜ አሎ» አለ፡፡ ወደ ተሰፋዬ በእጁ እያመለከተ፡፡ ቀጠል አደረገና «ቀደም አንቺ እንደ ተናገርሽው ለዋናውን ነርሰ መቶሟሙኑ ነው፡፡ ካልተሟመንከለ ሰራ መሰራት አይቻልም ዶሞ በሕይዎት ለሞኖሩ ቶሎ ማወቅ ከፈለግሽ ግዜው ማጡፋት ያለብሽ አይመሰለኝም፡፡»

«እውነት ነው መፍጠን አለብኝ፡፡ ስለዚህ እንዲህ ብናደርግለ ነገ አንተን በተመቸህ ጊዜና ቦታ እንቀጣጠርና እንገናኝ፡፡ እኔም ሙሉን አምሰት ሺህ ብር ይዤ እመጣለሁ፡፡ በአንተ በኩል ደግሞ ለመኖሩ እርግጠኛ እንድሆን ጣቱ ላይ ያለውን የቃልኪዳን ቀለበቱን ልታመጣልኝ ትችላለህ?» አለችው፡፡ በጥርጣሬ ዐይን እያየችው፡፡

«ዋእ! ለዚማ ሊሆን አይችልም፡፡ አንችስ ቡታሱቢው እንዴት የቃልኪዳን ቆሎበት ያህል ነገርሰ አሙኖ ይለጦኛል!?»

«ከአንተ እኔ ባላውቅ» አለችው ትሩፋት ተረጋግታ «ካንተ እኔ ባላውቅ እንደምሰማውና እስከ አሁን እንደሚሰራበት ከሆነ ማንኛውም ሰው ወደ ማረሚያ ቤት ሲወሰድ የያዘውን ገንዘብም ሆነ ንብረት በሙሉ አስመዝግቦ ለፖሊስ ጣቢያው ንብረት ክፍል ያስረክባል፡፡ ስለዚህ የጣት ቀለበቱ በፖሊስ ጣቢያው ንብረት ክፍል ውስጥ ይገኛል ማለት...» ለሶስተኛ ጊዜ ንግግሯን ሳትጨርስ አቋረጣት፡፡





«እኛ እንደ ደርግ ኢሰፓስ የሶውን ወርቅ አናወልቅም፡፡ ያውም ለጋብቻ ቆሎበትን ያህል ከባድ ነገር!» አለ ኮንስታብል ካህሳይ ቆጣ ብሎ፡፡ ትሩፋትና ተሰፋዬ «... እንደ ደርግ ኢሰፓ...» ብሎ በመመጻደቁ እርስ በእርስ ተያይተው የትዝብት ፈገግታ ተለዋወጡ፡፡

«የቃልኪዳን ቀለበቱ እጁ ላይ ካለ እንደውም ለስራህ የበለጠ እመቺ ሆነልህ ማለት ነው፡፡ እኔና እሱ ብቻ የምንግባባበት ምልክት ወይም ኮድ እኔ እለጥሃለሁ፡፡ ኮዱን ስትነግረው እርግጠኛ ነኝ ቀለበቱን አምኖ ይሰ ...»ንዴቱ ጣራ ከመድረሱ የተነሳ ለአራተኛ ጊዜ ንግግሯን ሲያቋርጣት እንኳ አልታወቀውም፡፡

«ዋይ! እንቺ ለቆሎበቱ ብቻ ነው እዴ ቱኩረትሽ!? የሙትፈልጊው ለሶውየውን መሰሎኝ! ሰቆሎበቱ ነው እንዴ ለካስ ጭኑቀትሽ!» ከተገቢው በላይ መጮሁን እንኳ ልብ አላለውም፡፡

«ቆይ ታገስ ኮንስታብል፡፡ ተረጋግታችሁ ለመግባባት ሞከሩ፡፡ እሷ በትክከል ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ታሰሮ በሕይወት መኖሩን በእርግጠኝነት ማወቅ ትፈልጋለች፡፡ በሕይወት ለመኖሩ መቶ በመቶ እርግጠኛ እንድትሆን ትክከለኛ ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርባታል፡፡ ለዚህ ደግሞ እንተ መተማመኛውን በቀላሉ ማግኘት እንድትችል ዘዴዎችን እያመቻቸችልህ ነው፡፡ ሥራህ እንዲቀልህ እየረዳችህ እኮ ነው!» አለው ተሰፋዬ ነገሩን ግልጽ ለማድረግና ሰማግባባት እየሞከረ፡፡

«ዋይ! እንተስ ወንድሜ ብትሆን እሰቲ አስቦ፡፡ አሁን ለሱ ለጣትህ ላይ ያለው የቃልኪዳን ቆሎበትህ አውልቀህ ሱጦይ ብልህ ትሶጠኛሎህ እንዴ! ማወቅ የፈሎጋችሁት ለሰውዬውን በሕይወት መኖር መሱሎኝ ነበር! ለካ እናንተ ለንቡረቱ ኑሩዋል ዋና ጭንቀታቹህ!» አለ የተገረመ መሰሎ፡፡

«ግድ የለም ኮንስታብል ካህሳይ እትቆጣ! እንዳልከው የምፈልገው ቀለበቱን ሳይሆን የሰውየውን በሕይወት መኖር ነው፡፡ እንዳልከው እሱም ቢሆን የቃልኪዳን ቀለበቱን አሃምኖ ሊሰጥህ ይቸገር ይሆናል፡፡ ለማንኛውም ሌላ ቀላል ዘዴ መጠቀሙ ይሻላል፡፡ ፈርማውን ወረቀት ላይ ፈርሞ ቢልከልኝ ይበቃኛል፡፡ እኔም ለዚህ ሁሉ ድካምህ አምሰት ሺህውን ብር በሙሉ ልከፍልህ ይኸው በጓደኛዬ ፊት ቃል እገባልሃለሁ» ስትለው ፊቱ ቅጭኑም ሲል እየችው፡፡

«እስ፤ ሰሚኢሞ እህቴ! ለኔለ ሳታሙኝኝ ሳንቺስ እንዴት እድርጌ ልሞንሽ? ለሰንት ሡሉዋትነት ከፉዬ እኮ ነው ይህን ሥራ የሙሰራው፡፡ ለፊርማውን ካመጣሁልሽ በኋላ እዩተሽ የሱ ፊርማ አይደለም ቡትይኝ ሙን ለማረግ እችላሎህ? ለዚ ነው የመጀመርያ ክፉያ የሚያሰፈልገው፡፡ ዋይ! ቤት እከራዮች እንኳን ቀብዲ ይቀበሉ የለ እንዴ!» አለ አሁንም የተገረመ መሰሎ፡፡

«ልክ ነው፡፡ አንተም ቢሆን ይህንን ሥራ ችግር ውስጥ ገብተህ እንደምትሰራው ይገባኛል፡፡ እንዳልከው በሁለታችን መካከል ተስፋዬ አለ፡፡ ፈርማው የእሱ ለመሆኑ እንዲያስተማምነን ደግሞ ስሙ ተጽፎባቸውና ፈርማው ያረፈባቸው የተሰያዩ ደብዳቤዎችንና ሰነዶችን ይዤ እመጣለሁ፡፡ ፊርሞ ከሚሰጥህ ጋር አስተያይተን መተማመን እንችላለን-- አሁንስ ኮንስታብል ካህሳይ?»

«እንዲህ እንደ እንቺ አይነት ኬዝ የገጠማቸ የቡዙ ሰዎችን ጉዳይ ሰርቻሎህ፡፡ ሰሁሉም የሰራሁት ቅድሚያ ከፉያ ተቀብዬ ነው፡፡ እንደ እንቺስ ተጦራጣሪና አስሸጋሪ ሰው እስካሁን አላጋጠመኝም፡፡ ለእንቺን ዛሬ ሌላ አዲስ አሰራር አሉከተልም፡፡ምኖሩ ማረጋገጥ ከፈሰግሽ የሙሰራው በዚሁ መንገድ ነው፡፡ ካልሆነ በጊዜ ብንለያይ ይሻላል፡፡ ሌላ ሀተታ አያሰፈልግም» አለ በሰጨት ብሎ፡፡

«ነገርኩህ እኮ ኮንስታብል ካህሳይ የመጣሁት ድንገት ነው፡፡ ገንዘቡ ሰዛሬ የሚፈሰግ አልመሰለኝም፡፡ ሙሉውን ገንዘብም ሰማግኘት ከወዳጅ ዘመድ ማፈላለግ ይኖርብኛል፡፡ አንዲት ተራ አስተማሪ ይህን ያህል ገንዘብ በአንዴ ከየት አመጣለሁ? አንተም ይገባሃል ብዬ አሰባለሁ» አለችው ውሰጡን ለማጥናት እየሞከረች፡፡

«ቢቃ ሰገንዘቡን በሞላልሽ ጊዜ እንገናኝ!» ብሎ በተቀመጡበት ሳይሰናበታቸው እየተቆናጠረ ሄደ፡፡ አዳራሹን ለቆ እስኪ ወጣ ድረስ ሁለቱም ተገርመው በዐይናቸው ተከተሉት፡፡

«ገና ሳየው ነበር ነገሩ እንደማይሳካ የገባኝ፡፡ ችግሩ መሰንበቱ በጀኝ፡፡ ሰው ምንም ያህል ከባድ ችግር ቢገጥመው እየዋለ እያደረ ሲሄድ መረጋጋቱ አይቀርም፡፡ ጭንቀቱንና ችግሩን እየተለማመደው ይሄዳል መሰል ቀለል ማድረግ ይጀምራል፡፡ ይህን ሰው የእለቱ እለት አግኝቸው ቢሆን ኖሮ እንኳን አምስት ሺህ ብር ከዚያም በላይ ቢጠይቀኝ ያችኑ ደሳሳ ጎጆዬን በእራጣ አሰይዤ ታበድሬም ቢሆን መስጠቴ አይቀርም ነበር፡፡ ደግነቱ ማሰብና ማመዛዘን በቻልኩበት ደረጃ ላይ ሆኜ ነው ያገኘኝ» አሰች ትሩፋት ዐይን እውጣነቱ እየገረማት፡፡ ከዚያ በኋላ ኮንስታብል ካህሳይን ዳግም ላለማግኘት ወሰነች ፡፡

«ምን እንደሚያሳዝነኝ ታውቂያለሽ ትሩፊ? እንዲህ አንዳንቺ ልጁ-- ባሰቤቱ--ወንድም እህቱ-- አባት እናቱ---ወዳጅ ዘመዱ.... ድንገት ከቤቱ ወጥቶ የተሰወረበት የተጨነቀ ምስኪን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ገንዘቡን በከንቱ ተበልቷል ማሰት እኮ ነው፡፡ በእውነቱ በጣም ያሳዝናል፡፡ ከበደል ላይ በደል! ግፍ ነው የግፍ ግፍ! የአንዱ ሀዘን የሌላው ደስታ--- የአንዱ ጥፋት የሌላው ልማት---የአንዱ ውድቀት የሌላው እድገት» አሰ ተስፋዬ አዝን ብሎ፡፡

«እነዚህ አዙሮ የሚያይ እንገት የሚሉት ነገር ያልፈጠረባቸው ሽንኮች--- ግፍ ይፈራሉ ብለህ ታስባለህ ተስፋዬ፡፡ ይህን ሕዝብ ስጋው አልቆ አጥንቱ እስኪፋቅ ድረስ





ሲቦጠቡጡት ጭካኔያቸው በቀለኝነት ያሰባቸው ነው የሚመሰለው፡፡ እንግዲህ አሰበው እንደ እኔ ዓይነት ችግር ከገጠማቸው የተጨነቁ የዋህ ሰዎች ላይ ፊርማና ውል የሌለው ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብሩን ላጥ አድርጎ ይጠፋል፡፡ ለማን አቤት ይባላል?» አለች ትሩፋት በጣም ተከፍታ፡፡

«እኔማ ወታደርና የዘመኑ ሰው መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የእውነት የሚረዳሽና የሚሰራው መሰሎኝ ነበር እዚህ ጣጣ ውስጥ ልከትሽ የቻልኩት» አለ ተስፋዬ ጥፋተኝነት እየተሰማው፡፡

«ተስፋዬ ብዙ ወዳጆቼ ምንም መረጃ ሳይኖራቸው ገና ለገና 'ባለቤቷ በመንግሥት ታፍኖ ተወሰዷል፤ የመንግሥት ተቃዋሚ ሳይሆን አይቀርም' በሚል አጉል ፍርሀት ተውጠው ከወዲሁ ሸሽተውኛል፡፡ አንተ ግን በዚህ የጭንቅ ሰዓት ጊዜህን ሰውተህ የችግሬ ተካፋይ በመሆን ከጎኔ ቆመሃል፡፡ አመሰግናለሁ አልልህም፡፡ ተለምዷዊ ቃል በመሆኑ ያንሰሃል፡፡ ትልቅ ውለታ እንደ ዋልከልኝ ግን አልደብቅህም፡፡ ዳግም ሰው እንድወድና በቀሪው እድሜዬ ሰው የሚባል ፍጡር ጠልቼ ከሰው እየሸሸሁ እንዳልኖር ረድተኸኛል» አለችው፡፡

«ምን አደረኩልሽ ትሩፋት? ምነው በታደልኩና ላደርግልሽ የምፈልገውን ያህል ሁሉ ማድረግ በቻልኩ!» አላት፡፡ ማህላቸው ካለው ጠረጴዛ ላይ አቆላልፋ የተደገፈቻቸውን ሁለት እጆቿን ሰቦ ጭብጥ አድርጎ ያዛቸው፡፡

«ሰው ሆኖ----ሰው ጠልቶ----ከሰው እየሸሹ መኖር እንዳልኖሩ ይቆጠራል፡፡ ይህ ትልቅ እዳ እንዳይደርስብኝ ተከላከለህልኛል፡፡ በጥላቻ ሰማየ ሰማያት የወጣች ነፍሴን በፍቅር ወደ ምድር አውርደህልኛል ተስፋዬ፡፡ በገንዘብ የማይተመን ውድ የጓደኝነት በረከት ነው፡፡» አለችው አሷም የተጨባበጡ እጆቻቸውን እያጠበቀች፡፡ ከልቧ ነበር፡፡

እሷ የትዳር አጋሯንና የልጆቿን አባት ሳጣች ብዙ ወዳጆቿ ያላዩ ያልሰሙ መሰሰው ፊታቸውን አዙረውባታል፡፡ ባጉል ፍርሀት ተውጠው ብዙ የምታቀርባቸው ሰዎች ርቀዋታል፡፡ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ከጎኗ የተገኘው ተስፋዬ ብቻ ነው፡፡ ብታማሰግነው የሚበዛበት አይሆንም፡፡ የያዙትን መጠጥ ጨርሰው ቱሪስት ሆቴልን ለቀው ሲወጡ ፀሐይ ጠልቃ ተራውን ለምሽቱ መልቀቋ ነበር፡፡ አራት ኪሎ ታክሲ ተሻምቶ ለመያዝ ላይ ታች በሚራወጡ ሰዎች ተሞልታ መርካቶ ገበያን መስላሰች፡፡

********

የጥዋቷን ፀሀይ የሐምሌ ጥቁር ደመና እንደ ብርድ ልብስ አፍን አድርጎ ይዟታል። በመኝታ ቤቱ መስኮት ይገባ የነበረው ብርሃን ባለመኖሩ ክፍሉ ጨለምሰም ብሏል። ትሩፋት አልጋዋ ውስጥ እንዳለች ሐሳብ ይወዘውዛታል። ሐሳቧ ደግሞ ውሉ እንደ ጠፋበት ልቃቂት በየቦታው እየተበጣጠሰ የምትይዘውንና የምትጨብጠውን አሳጥቷታል፡፡ ጭንቀት

ሁለመናዋን ተቆጣጥሮ ያባዝናታል፡፡ ጭንቀቷ ይቀልላት ይመስል አቃስታ በረጅሙ ተነፈሰች።

«ምን ጉድጓድ ዋጠው? ምን አውሬ በላው? ሞተ ወይ አለ የሚል ምንም ፍንጭ ሳልሰማ ይኸው ድፍን አራት ወር፡፡ እንዴት የወደቀበትንና ያለበትን ሁኔታ ማወቅ ያቅተኛል? ሞቶም ከሆን አስከሬኑን፤ ታስሮም ከሆን የታሰረበትን ቦታ ማግኘት እንዴት ተራራ የመግፋትን ያህል ከበደኝ? ብዙ አልደከምኩለትም ማለት ነው ይሆን? የትም ታፍኖ ተወስዶ ደብዛው ጠፍቶ እንዲቀርና እንዲረሳ ፈርጄበታለሁ ይሆን? አዎ የእኔ ስንፍና ነው፡፡ ያለጥርጥር ጥንካሬ ጎሎኛል ማለት ነው፡፡» ራሷን ወቅሳ አታበቃም፡፡ የሆነውን ነገር እንዲኑን አለማወቋ የእሷ ድክመት ይመስላታል፡፡ ግን እያደረገች ካለችው በላይ ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ይገባታል፡፡ ቀን በሄደ ቁጥር ደግሞ ጭንቀቷ እየባሰባት ተቸግራለች፡፡ አሁን አሁንስ አዕምሮዋ በሐሳብ ብዛት ተወጣጥሮ እንዳይፈነዳ ትፈራ ጀምራለች፡፡ ከሁሉም በላይ ግን አንድ ድምጽ ምንጊዜም ሳትሰማው ውላ አታድርም፡፡ ሁሌም በጆሮዋ ያስተጋባል፡፡ ከሁሉም ድምጾች ልቆ እያስገመገመ ይሰማታል፡፡ ወፈር ብሎ የሚወርድ ረጋ ያለ ድምጽ፡፡

«...በታጠቁ ኃይሎች በግድ ተገፈታትሮ ታርጋ ቁጥር በሌላት ነጭ ቶዮታ መኪና ታፍኖ ሲወሰድ አይቻለሁ...» መስማት ባትፈልግም ማስቆም አትችልም፡፡ ብትሸሸውም አይለቃትም፡፡ ዛሬም አልጋዋ ውስጥ ሆና ምናልባት ከአስር ጊዜ በላይ ተደጋግሞ ተሰምቷታል፡፡ እነዚህ የታጠቁ ኃይሎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ እሷ ብቻ ሳትሆን ድፍን አገር ምድሩ ያውቃል፡፡ ቤት ለቤት ተዞሮ ሙልጭ ተደርጎ ተመንጥሮና ተፈትሾ መሳርያ ሁሉ በአንድ ተቋም እጅ ውስጥ መግባቱ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው፡፡ «የገጠመኝ መጋፋት የማልችለው ችግር ነው፡፡» አለች ትሩፋት፡፡

የዛሬ ቀጠሮዋን አሰበች ሆኖም ያን ያህል አስተማማኝ ውጤት ያመጣል የሚል ሙሉ እምነት የላትም፡፡ ኢሰመጉ (የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ) እንዲህ እንደ እሷ ድንገት ከቤታቸዉ ወጥተው ሳይመለሱ የቀሩ ሰዎችን ስም ዝርዝር በግል ጋዜጦች ላይ ወይም በራሱ መጽሔትና በመሳሰሉት ላይ ከመጻፍ ወይም ስም ዝርዝር ከማሳወቅ የዘለለ ሥራ ሰርቶ አላየችም፡፡ እንዲህ እንደ እሷ በገዛ አገራቸው በመንግሥት ታጣቂዎች ታፍነው ተወስደው ደብዛቸው የጠፉ ሰዎችን አሰገኝ ወይም በግፍ ያለፍርድ የታሰሩ ሰዎችን አስፈታ ሲባል ሰምታ አታውቅም፡፡ ኢሰመጉ የራሱ ህልውና ኢህአዴግ መንግሥት እጅ እንዳይጠፋ እየታገለ ያለ ድርጅት እንደ ሆነ አድርጋ ነው የምትወሰደው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት በበጎ ዓይን ከማያያቸው ድርጅቶች ውስጥ እንደ አንዱ ትቆጥረዋለች፡፡ ይሁን እንጂ ዛሬ ምን አልባት በሚል ስሜት ለማመልከቻዋ የሚሰጧትን መልስ ለመስማት ለመሄድ ወሰናለች፡፡





ከባለቤቷ ጋር አብረው በኖሩበት ዘመን ስታውቀው ቤተሰቡን ጥሎ እንዲህ እንደ ዋዛ በወጣበት የሚቀር ዓይነት ሰው አይደለም፡፡ ራሷን የምታውቀውን ያህል ታውቀዋለች። ራሷን የምታምነውን ያህል ታምነዋለች። «እዚህ ሄድኩ» ሳይላት ድንገት በወጣበት የውሃ ሽታ ሆኖ ይቀራል ብላ ማመን ቸገራት፡፡ የዛሬ አራት ወር በዚያች ጭንቅ ጥቁር ሌሊት ለአፍታም ቢሆን ያልሆነ ጥርጣሬ ውስጥ መግባቷ አልቀረም ነበር፡፡ «ምን ይታወቃል ድንገት በሌላ ሴት...» የመጣባትን ይህን ክፉ ሀሳብ አልጨረሰችውም፡፡ «አይሆንም!— አይደረግም!-- ፈጽሞ አያደርገውም!» ስትል ነበር ጮክ ብላ ለራሷ የነገረችው፡፡ እንዲህ በማሰቧ እንኳን «ሰው መሆን እንዴት ከፉ ነው!» ስትል ያኔም በዚያች ጥቁር ሌሊት ጊዜ ራሷን ወቅሳለች፡፡ ከዚህ ሁሉ ከተወሳሰበው ሀሳቧ መሀል እንደ ቁርጥራጭ ፊልም ቀስ እያለ በዐይነ ህሊናዋ የመጣው ትዕይንት ግን ሁሉ ነገሯን አነቃቅቶ ወደ ቤት ፍተሻ አስገባት፡፡

አሰፋ ከእድገት በኅብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻ ጀምሮ የሚተዋወቁ የቆየ የባለቤቷ ጓደኛ ነው፡፡ እቤትም በተደጋጋሚ ሲመጣ ታውቀዋለች፡፡ በመጣ ጊዜ ቤት ያፈራውን ቀማምሰው ተሳስቀውና ተቀላልደው ይለያዩ ነበር፡፡ የአንድ ቀን ሁኔታቸው ግን ለእሷም ለየት ብሎባት ነበር፡፡ አንድ ዶከመንት ነገር ይዘው አፍ ለአፍ ገጥመው በጽሞና ይነጋገራሉ፡፡ አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ በጊዜው የሥራ ጉዳይ ይሆናል ብላ በመገመት ብዙም ትኩረት አልሰጠችውም ነበር፡፡ ሻይና መክሰስ ለማቀራረብ ከሰራተኛዋ ጋር ጉድ ጉድ ማለቷን ቀጠለች፡፡ በሁለት ጓደኛሞች የግል ጨዋታ ላለመግባት ጭምር፡፡

ባለቤቷ ወጥቶ በቀረባት በዚያች የቀን ከፉ ጥቁር ሌሊት ጊዜ ግን ሁኔታቸውን እንደ ገና በዐይነ ህሊናዋ አመጣችው፡፡ ጥብቅ ሚሥጢራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ይነጋሩ እንደ ነበር ሠሰል ብሎ ታያት፡፡ ሳታሰበው እግሯ ወደ መኝታ ቤት መራት፡፡ ወደ ቁምሳጥኑ፡፡ እጇ ያገኘውን ነገር ሁሉ እያወጣ ፈለጋዋን ቀጠለች፡፡ መሳቢያዎችን፣ ሻንጣዎችን ሁሉ ዝርግፍግፋቸውን አውጥታ ተመለከተች፡፡ ያገኘችው ነገር አልነበረም፡፡ የእጅ ቦርሳው ትዝ ያላት መጨረሻ ላይ ነበር፡፡ ከተቀመጠበት ሄዳ በፍጥነት ብድግ አደረገችው፡፡ ሚሥጥራዊ የመክፈቻ ቁጥሩን ባለማወቋ መክፈት አልቻለችም ነበር፡፡ በግምት እየነካካች ሞከረችው አልሆን ሲላት ወደ ሳሎን ተመለሰች፡፡ የብረውን መሳቢያ ከፈተችና ቢላዋ አወጣች፡፡ ከብዙ ልፋትና ሙከራ በኋላ መጨረሻ ላይ ነበር የተሰካላትና ከፈተችው፡፡ ውስጡ ያሉትን ዶክሜንቶች በሙሉ እያወጣች ተመለከተች፡፡ መጨረሻ ላይ እጇ የገባውን ዶክሜንት ስትመለከት ግን ድንጋጤ መላ አካሏን ወረረው፡፡ በሚሥጢራዊ ኮድ የተጻፈ ነበር፡፡ ባለቤቷ በምን ምክንያት ሊታፈን እንደሚችል ፍንጭ ሳይሰጣት አልቀረም፡፡ ለዚች አገር የሕዝብ ልዕልና ዛሬም እንደ ገና ግማሽ ምዕተ-ዓመት በዘለለው አድሜው ለመታገል ያልደከመው አሱነቱ ልቧን አደማው፡፡ ከዚያች አስከፊ ጥቁር ሌሊት ጋር ተፋጣ በሐዘን የተዉጋ ልቧን እንደ ያዘች የማይቀር የተፈጥሮ ሕግ ሆነና ጨለማው ለንጋት እጁን ሰጠ፡፡

የምታከብረው፣ የምታምነውና የምትወደው ባለቤቷ እንደ ዋዛ ከቤት ወጥቶ ከቀረ አነሆ ወራት አስቆጠረ:: ትሩፋት አልጋዋ ውስጥ እንዳለች የሀሳብ ድር ታደራለች:: በዐይነ ህሊናዋ የሚታያት ነገር ሁሉ ደግሞ እጅግ ከፉ ከፉ ነገሩ ሆነባት:: በትንሽ ጠባብ ጨለማ ከፍል ውስጥ ብቻውን ተጥሎ --- በልተው በጠገቡ ሦስት አራት ወጠምሻ ወታደሮች ትብብር ፋታ በማይሰጥ ቅብብል ተደብድቦ--- ሁለመናውን የደም አባሳ አልብሶት---ዓይኑ ማየት እስኪሳነው ድረስ አባብጦ--- አነዚያ የምትወድለት ትናንሽ አንቁ መሳይ ጥርሶቹ ረግፈው---በአፍ በአፍንጫው ደም አንደ ጅረት ሲንጀረጀር—ዝግባ የመሰለው ረጅም ቁመናው አይሆኑ ሆኖ ዝሎና ተንሳቁሎ----ሲወጣ የለበሳት ስስ ነጭ የበጋ ሸሚዙ በደም ተነከራ-- አይን ቢወጉ በማይታይ ድቅድቅ ጨለማ ከፍል ውስጥ እንደኛው ጥግ ላይ ሬሳ መስሎ ተጥሎ ታያት:: ዝግንን አደረጋት:: ይህን ከፉ የቀን ቅዠት ሳለማየት ዐይኗን ጨፈነች:: የባሰውን በጨፈነችው ዐይኗ ውስጥ በጥይት ግንባሩ ተበርቅሶ---በጨቤ ልቡ ሳይ ተወግቶ---ሬሳው በደም ተነከሮ አየችው:: « እ--አ--- እህ!!» አለች:: ልቧን ውጋት ቅ--ስፍ አድርጎ ያዛት። ደረቷን በእጇ ተጭና ጥብቅ አድርጋ ያዘች:: ዐይኗን ደጋግማ ከፈት ዘጋ---ከፈት ዘጋ አደረገች። ትዕይንቱ ዐይኗ ስር አልጠፋልሽ ሲላት አልጋዋ ላይ ተፈናጥራ ወረደች።

የለሊት ልብሷን አውልቃ አልጋው ጥግ ወረወረችው። በመስኮቱ የገባው ብርድ ጀርባዋ ሳይ ፍስስ ሲል ቅዝቃዜ ተሰማት:: አስነጠሳት። ሄዳ ከመልበሻ መስታወቱ ፊት ለፊት ቆመች። ሙሉ እርቃን ምስሏን አቀረበላት። ሸበት ጣል-ጣል ያለበት ረጅም ጸጉሯ በየቦታው ተበታትኗል። ሰብሰብ አድርጋ አርስ በእርሱ አያያዘችው። ሦስት ልጆች ብትወልድም ዛሬም ሸንቃጣ ናት። ጡቶቿ እንደ ወይፈን ቀንድ ቆመው ልዋጋ ባይሉም ሞላ--ሞላ እንዳሉ ነው በመጠኑ ዘንበል ያሉት። እንደ አጥቢያ ኮከብ ብርሃን የሚተፉት ትላልቅ ዐይኖቿ ቁም መስታወቱ ላይ አፍጠዋል። እንደ እንግዳ ሰው እስተውሳ ራሷን ተመለከተችው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ዐይኗን ወግታ የምትመለከተው እርቃን ምስሏን ሳይሆን ከመስታውቱ ባሻገር-- ከካፒቴን ግቢ ከፍ ብላ ባለችው ቀጭን የእግር መንገድ ውስጥ ውስጡን ተሂዶ ከምትገኘዋ ቤቷ ባሻገር --- ከቀበና ዜሮ ሁለት ቀበሌ ባሻገር --- ከአዲስ አበባ ሰማይ ባሻገር---- ከአድማስ ወዲ--ያ ማ--ዶ ---! ከዘመንም ባሻገር ጭልጥ ብላ ር----ቃ ሄዳለች..... የሕይወቷን ልቃቂት ወደ ቀኝ ሳይሆን ወደ ግራ--ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ መልሳ እያሾረች እያጠነጠነች ጉዞዋን ተያያዘችው:: ጉዞዋ አንደ ዥዋዥዌ ከወዲያ ወዲህ እያላተመ እያላጋት ይዟት አልም አለ::





## ልጅነትና አዲስ ዘመን

«የከተማነት ወግ ማዕረግ ሳይደርሳት ይኸው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በሳይ አስቆጠረች::-ዙሪያዋን ከብብ አድርገው እንደ መልካም እናት እቅፋቸው ውስጥ ያስገቧት ተራሮች የቱሪስት መስህብ ሆነው አልጠቀሟት! ወይ ደግሞ የሆነ ማዕድን በከርሰ ሆዳቸው ውስጥ ኖሮ አላበለፀጓት! ያገጠጠ የድንጋይ ቁልል ብቻ! እነቋላ ዮሀንስን የመሳሰሉ ውብ ተራሮቿ የእሞራ ኩስ መጣያ ሆነው ቀርተዋል:: ቢያድላትማ የነዋሻ እንድርያስ፣ የነዘዝ እምባ... ታሪካዊ ዋሻ ባለቤትስ አልነበረች። ተጎብኝና ይለፍልሽ ቢላት ኖሮ!» አለች ትሩፋት በሐሳቧ ነጉዳ ሄዳ አዲስ ዘመን ከተማን በዐይነ ሕሊናዋ እያየቻት::

ትሩፋት ያደገችባት አዲስ ዘመን ከተማ ከሸኒ ወንዝ ማዶ ወደ ጣራ ገዳም መውጫ ዳገቱ ላይ ሆኖ ለተመለከታት ትልቅ ጎድጓዳ የእግዜር ገበታ ትመስላለች:: የሸኒ ወንዝን የሚያቋርጠው ብቸኛውን ድልድይ ተከትሎ አንድ የጠጠር መንገድ ከተማዋን ጫፍ አስከ ጫፍ ለሁለት ከፍሏት ወደ ምሥራቅ ይዘልቃል:: ከተራራው ግርጌ ሲደርስ ይቆማል። ወደ ተራራው እናት ቀና ሲሉ ሀና ማርያም ቤተክርስቲያን በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ መርገፏ እሸብርቃ እላዩ ላይ በኩራት ጉብ ብላ ትታያለች። ከተማዋን ቁልቁል እያስተዋለች «ያስኔ ማን ጠባቂ አለሽ አንች ምስኪን ከተማ?» የምትል ትመስላለች።

ያንኑ አንድ የጠጠር መንገድ ግራና ቀኝ ጠርዝ ተከትለው የተሰሩት ቤቶች አብዛኞቹ በተናጠል ለመቆም የፈሩ ይመስል በግድግዳ-- በግድግዳ ተገናኝተው አርስ በእርስ ተደጋግፈው ቁመዋል። እሮጌ ቆርቆሯቸው አቧራ የለበስ ቡትቶ ይመስላል። ንፋስ እንዳያነሳው አልፎ አልፎ የተጫነው ድንጋይ ከብዶት ጣራው ሁሉ ቁልቁል ጎብጧል::

እፈር ፈጭተው --- ውሃ ተራጭተው ---- የቅጠል እንጀራ ጋግረው ---- የውሸት ጠሳ ጠምቀው --- የውሸት ተጋብተው--- የውሸት ወልደው ከብደው ---- የውሸት ተጎራብተው ---- የውሸት ቡና ጠጥተው..... እቃቃ እየተጫወቱ ያደጉባት የልጅነት መንደር ፍቅር መተኪያ የለውም። ትዝታው ከደም ጋር ተዋህዶ በስራ አከላት ሲፈስ ዝንተ ዓለም ይኖራል። ጎስቋላዋ አዲስ ዘመን ከተማ አንዲያ ናት ለትሩፋት---- ዘወትር በዐይኗ ሳይ የምትሄድ---በደም ስሯ የምትዘዋወር::

በጋ ከከረምት ዋኝታ ሳደገችባት ሸኒ ወንዝ ደግሞ ልዩ ትዝታ አላት። በጧት ውሃ ልትቀዳ እንስራዋን አዝላ ስትሄድ መንገዱ ላይ እፍሰውት የሚሄዱት የጠላ አተላ፣ የአረቄ ብሬንጥና የጠጅ አንቡላ ሽታ አፍንጫዋን ተንፍጎት እያውቅም። እንደ ጥሩ ማዓዛ ተላምዳዋለች። የእመዱና የቤት ጥራጊው ፍሳሽ ባዶ እግሯን ስስ ቡላ ካልሲ ያጠለቀች ሲያስመስላት እንኳ ተጠይፋው አታውቀም። ሁሌም ቢሆን የማትለምደውና የምትጠላው ነገር ቢኖር ግን እንደ ጉልቻ አልፎ አልፎ ጉች ጉች ያለውን የሰው አይነ ምድር ነበር። እየተጠየፈች በፍጥነት የመዝለል ያህል ተራምዳው ታልፋለች። ከዚህ ሁሉ ይልቅ በናፍቆት የሚታያት ቶሎ

እንስራዋን አውርዳ---ቶሎ ልብሷን አውልቃ ሰፋ ካለው የወንዙ ክፍል ዘላ ጥልቅ ብላ የምትዋኘው ነው:: የመንፈስ እርካታዋ ከፏፏቴው ጋር አብራ እየተፍለቀለቀች የምትባቻው ነው:: ከዚህ የተፈጥሮ ደስታ ተቋድሳ የማትጠግበውን የሸኒን ወንዝ ሌላ ዙር ዋና ዳግም እያሰበች ውሃዋን ቀድታ እንስራዋን አዝላ ወደ ቤቷ ትመለሳለች::

ለአዲስ ዘመን ከተማ መቆርቆር መሰረቷ የሸኒ ወንዝ መኖር እንደ ሆነ ኗሪዎቿ ይስማማሉ። ለቤት ውስጥ ሥራ፣ ለመጠጥና ለልብስ ማጠቢያነት የሚያውሉት ይህንኑ የሸኒ ወንዝን ነው። አለቶቹ ለልብስ ማጠቢያ እንዲሆኑ ተፈጥሮ ሆን ብላ ያዘጋጀቻቸው ይመስላሉ። ሳፋ ለምኔ ያሰኛሉ። ትሩፋት ቅዳሜ ቅዳሜ የተሻለውን መርጣ ስትይዝ ወፍ አትቀድማትም።

ትሩፋት ያደገችው በተለይ ጭቃ መንደር በምትባለዋ ሰፈር ነው:: ጭቃ መንደር ልክ እንደ ኗሪዎቿ የደቀቀች ምስኪን ሰፈር ብትሆንም ለትሩፋት ግን ዝናዋን በርቀት በወሬ ብቻ የምትሰማትን የፓሪስ ከተማን ያህል ውብ ናት::

«አባባ መሳይ ሰፈራችን ለምን ጭቃ መንደር ተባለች ግን ካልታጣ ስም?» በመቆርቆር ትጠይቃለች ትሩፋት:: አባባ መሳይ የአባቷ ጓደኛና ጎረቤት ናቸው:: እንደ አባቷ ታያቸዋለች::

«አረገኝ!--ኧረገኝ! ትሩፋቴ ከረምቱ ሲወጣ ግዜ ጭቃው ከምን ግዜው ተረሳሽ ልጄ? መንገዱ ሁሉ አረንቋ ሁኖ መስሎኝ የከረመ:: ተዚች ተኔ ቤት እስተናንተ ቤት እንኳን መተላለፊያ መንገድ አሳጥቶነ መስሎኝ የባጀ» ይሏታል አባባ መሰይ በጊዜው ጸጉሯን እያሻሹ:: በእነዚያ ትላልቅ ዐይኖቿ ቀና ብላ እይታቸው ዝም ትላለች:: እንዳልተቀበለቻቸው ሲያውቁ አባባ መሳይ ደግሞ ማስረዳታቸውን ይቀጥላሉ::

«አንችንስ ቢሆን ጭቃው እስከ ቅልጥምሽ መስሎኝ ሲውጥሽ የከረመ። እግርሽን ቅርጭጭት ቆርጦ ሊጥለውስ አልነበር:: ጫጋቱስ ቢሆን ሙች ቀርቶልሽ! የእግሮችሽን እጣቶች ሁሉ ቀርድዶ ቀርድዶ ያቆሰለው የበካው ጭቃ እንጂ ነው:: የልጅ ነገር! በጋው ሲመጣ ግዜ ተመቼው ተረሳሽ ትሩፋቴ? ለዚህ ነዋ! ጭቃ መንደር የተባለችው» ይሏታል በፍቅር ዐይን እያዩዋት::

«በክረምት የኛ ብቻ አይደለችም ሁሉም መንደር አይደል ጭቃ በጭቃ የሚሆነው» አለች ትሩፋት በአባባ መሳይ ሀሳብ ባለመስማማት።

«ዛድያ እንደኛው መንደር አይሆንማ! ወርቅ ሜዳ ብትኸጂ---አራዳ ገበያ ብትኸጂ--- ሮብ ገበያ ብትኸጂ---ጌሾ መንደር ብትኸጂ---ዘንቦ ውዲያው ነው ጠፈፍ የሚለው። እንደ ጭቃ መንደር እስከ ቅልጥም የሚውጥ አረቋ ጭቃ አታገኝም::»





ትሩፋት ነገሩ ባይዋጥላትም ዝም ትላለች። አባባ መሳይን ሳለማስቀየም ጭምር። ትወዳቸዋለች። የእሳቸውን ያህል አባቷን እንኳ ዘና ብላ አታናግራቸውም። እሷ ብቻ ሳትሆን የሰፈሩ ልጆች በሙሉ ይቀርቧቸዋል:: ተረት ተረት የሚያወሩላቸው እሳቸው ናቸው። የሰፈሩ ሴት ልጆች በጉትቻ የሚያጌጡት ጆሮዋቸውን በርጥብ ኢጋም እሾህ አባባ መሳይ በስተውላቸው ነው። ትሩፋት ብቻ ነበረች ያመኛል ብላ ያልተበሳችው። ደምና ቁስል ትፈራለች። ሰው ላይ እንኳ ስታየው የሰራ አከላቷን ከውስጧ ሰቅጥጥ የሚያደርግ ስሜት ይሰማታል::

«ትሩፋቴ አንች ከነወርቄ፣ ከነብርቱካን፣ ከነሸዋርካብሽ፣ ከነአልማዝ፣ ከነአስራቴ፣ ከነሳባ፣ ከነማርታ.... በምን ታንሻለሽ? ካላንች በስተቀር ጉትቻ ያላደረገች ኩታራ በጭቃ መንደር እስቲ ፈልገሽ ንገሪኝ» ይሏታል አባባ መሳይ:: እሷ ብቻ ለምን ይቅርባት ከሚል አባታዊ ፍቅር:: ጆሮዋ ተበስቶ በጉትቻ እንድታጌጥ ሁልጊዜ ያነሳሏታል:: እውነትም ከትሩፋት በስተቀር ሁሉም እኩዮቿ ጉትቻ አድርገዋል::

«ያመኛል አባባ መሳይ:: ደም ደም ሳይ እኔ እንጃ! ዝግንን ያደርገኛል» አለች ሰውነቷ ሰቅቅ እያለ::

«ኧረ ወዲያ ጅል! ደም የሚወድ ማንን አይተሻል? የግዳስ የኔን የአባትሽን ምክር ስሚ:: ደፍረሽ ከተበሳሽ በኋላ ህመሙም ቁስሉም ለጊዜው ነው እንጂ ጥቂት ቆይቶ ይሽርልሻል:: እሾሁን በእጅሽ ቶሎ ቶሎ ታልነካካሽው ደሞ ፈጥኖ ይድንልሻል:: ጥቂት ቆይተሽ ደሞ እሾሁ ይወጣና ሰበዝ ጫፍና ጫፉ በእሳት ተተርኩሶ ይደረግልሻል:: እንደ ዚያ ተሆነ ሲዱን እፍታ አይቆይም» አሏት እያባበሏት::

«ጉትቻ ባይኖረኝና ቢቀር ምን እሆናለሁ ግን አባባ መሳይ?»

«ጅሎ! ወንድ ነዋ የምትመስይው! ደምስ ሁሏም ልጅ ጉትቻ ሲኖራት አንቺ ብቻ ለምን ያቀርብሻል?» ትሩፋት ጆሮዋን በመበሳትና ባለመበሳት መሀከል ሆና ስታወላውል ተመለከቷት:: እሳቸውም ማበረታታቱን ቀጠሉበት::

«ትሩፋቴ ይልቅስ ሸኒ ማዶ ሮጠሽ ኸደሽ እርጥብ ኢጋም እሾህ ቆርጠሽ አሁኑኑ ይዘሽ ነዪ። ዛሬ ከተበሳሽ ነገ ቀኑ ቅዳሜም አይደል? እዎ ቅዳሜ ነው:: እኔ ጉትቻ አገዛልሻለሁ። ሳንቲሙን እሰጥሽና አንችው አራስሽ ገበያ ወርደሽ የወደድሽውን መርጠሽ ትገዢለሽ::» አሏት በጉትቻ መግዣ ሳንቲም እያባበሏት::

ትሩፋት የዚያኑ እለት ጆሮዋ ተበሳ:: እንደ ፈራችው ብዙ ቀን ቆስሎ አሰቃያት። ቢሆንም አባባ መሳይ በገዙላት የአስር ሳንቲም ጉትቻ እንደ ጓደኞቿ አጌጠች። ደስ አላት። ራሷን ከቻለች በኋላ ገዝታ የምታደርጋቸው የወርቅና የብር ጉትቻዎቿ ሁሉ እንደ ዚያች የሣምሰማር ራስ የመሰለች የአስር ሳንቲም ጉትቻ ብርቅ ድንቅ አይሆኑባትም::

ዛሬ ዛሬ ራሷን በመስታወት ስታየው ሁለቱ ጆሮቿ እኩል አልተበሱም። አንደኛው ከፍ ሌላኛው ዝቅ ያለ ነው። ያመኛል ብላ ፈርታ ከወድያ ወዲህ እየተቁነጠነጠች እስቸግራቸው ነበር። ሆኖም አስተውሎ ሰተመለከተው ነው እንጂ ያን ያህል ልዩነቱ ጎልቶ አያስታውቅም፡፡ አፈሩን ገለባ ያድርግላቸው የማይጠፋ የዘለዓለም መታሰቢያቸው አድርጋ ትቆጥርላቸዋለች።

አባባ መሳይ የሰፈሩን ልጆች ሁሉ ያቀርባሉ። «ልጅ ቢናገሩት— ቢቆጡት ቂም አይዝም--- ተናግሮ አያስቀይምም» የሚል እምነት ነበራቸው። በተለይ ደግሞ ከሰፈሩ ልጆች ሁሉ ትሩፋትን ይበልጥ ያቀርባሉ። ቀልባቸው ይወዳታል። ለመልዕከትም ሆነ ለትእዛዝ የእሷን ስም መጥራት አፋቸው ላይ ይቀናቸዋል። እሷም ብትሆን እቤት ስንት ስራ እየጠበቃት-- የእንጀራ እናቷ ቁጣ እያሳቀቃት ትዕዛዛቸውን ከመፈጸመም ወደ ኋላ ያለችበት ጊዜ የለም። ከሁሉም ትዕዛዛቸው የማይረሳት ደግሞ ከቤታቸው ታዛ ካለው ትልቅ ድንጋይ ላይ ይቀመጡና--

«ትሩፋቴ ያችን ዱካ መቀመጫ ይዘሽ ነይና እዚህ አጠገቤ ተቀመጭ። መጣፍ ቅዱሰ ታንቢልኛለሽ» ይሏታል። የማያነቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች እያገላበጡ። ትንሿን ዱካ ይዛ ትመጣና አጠገባቸው ትቀመጣለች። እየሰለቻትም ቢሆን ፈቃዳቸውን ትሞላለች። የሚፈልጉትን ምዕራፍና ርእስ እየነገሯት ታነብላቸዋለች። እድሜ ለየኔታ አካለወልድ የግእዝ ቁጥር አላምራ ታውቃለች። ቁንጥጫቸውና አለንጋቸው ከፉ ነበር እንጂ የመጀመርያ መምህሯ የኔታ አካለወልድ ጠንካራ የቄስ ትምህርት መምህሯ ነበሩ፡፡ ጭቃ መንደር ተወልዶ--- የጭቃ መንደር ልጅ ሆኖ እሳቸው ዘንድ ያልተማረ የለም፡፡ የእሳቸውን የጆሮ ቁንጥጫና እለንጋ ያልቀመሰ የጭቃ መንደር ልጅ በውርርድ አይገኝም፡፡ «ጣፋጭ› ይሏታል እለንጋቸውን፡፡ የኔታ አካለወልድ ትሩፋትን ዳዊት ሊያስድግሟት ሲሉ ነው አባቷ

«ዘመን እመጣሹ የአስኳላ ትምህርት ይሻላል» ብለው መንግሥት ትምህርት ቤት ያስገቧት፤ ወዲህ በነፃ ነው። እንደ የኔታ በወር አንድ ሽልንግ አያስከፍልም።

አባባ መሳይ አንዳንድ ጊዜ ያበዙታል። ልጅ ናት ይሰለቻታል አይሉም። ያልገባቸውን ምዕራፍ ደጋግማ እንድታነብላቸው ያዟታል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ከመጽሐፉ የተነበበውን በማጣቀስ ማብራሪያ ይሰጧታል።

«ትሩፋቴ ይህ የምታነቢልኝ መጣፍ ቅዱስ ይባላል፡፡ እናንተ ከተማሪ ቤት እንደሚሰጣችሁ የሳይንስ፣ የሒሳብ ምናምን እንደምትሉት ዝም ብሎ ተራ መጣፍ አይደለም፡፡ በሙሉ የግዚሀር ቃል ነው የተጣፈበት። እድሜሽ ረጅም እንዲሆንና ሀብትና ጤና እንዲሰጥሽ ቃሉን ማከበር አለብሽ» ይሏታል ዐይን ዐይኗን እያዩ፡፡ የሚሉት ብዙም ባይገባትም





«እሺ አባባ መሳይ» ትላለች ቀና ብላ እያየቻቸው፡፡

«ትሩፋቴ እናት አባታችሁን አከብሩ ይላል የናትና ያባትሽን ትዛዝ ፈጣሚ ሁኚ ልጄ! አትስረቂ ብሏል እንዳትሰርቂ! አትዋሽ ብሎ ያዛል እንዳትዋሽ! ይኸንን የምታነቢልኝን የመጣፍ ቅዱሱን ቃል ሁሉ ጠብቂ፡፡ በተለይ በተለይ እሰርቱ ትዛዛት የሚባሉትን በደንብ አጥንተሽ ቢቃልሽ ያዣቸው፡፡ እድሜሽን ሙሉ ይጠቅሙሻል ልጄ። በይ ለዛሬ ይበቃል። እግዜር ይባርከሽ፤ በሰላም ያዋለን አምላክ በሰላም ያሳድረን፡፡ ነገ ደሞ ሌላ ምዕራፍ እነግርሽና ታነቢልኛለሽ፡፡ እደጊልኝ! ትምህርትሽን ይግለጥልሽ!» ይሉና መርቀው ግንባሯን ስመው ያሰናብቷታል፡፡ ለነገ ደግሞ ሌላ ቀጠሮ እየሰጧት፡፡ ሳታውቀው ለመጽሐፍ ቅዱስ ክብር ሰጠች። ውስጧ ተቀበረ።

አባባ መሳይ መቼም ነገረ ስራቸው ሁሉ ከትላላቅ ሰዎች ይልቅ የልጅ ጓደኛ የሚመርጡ ነው የሚያስመስላቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በኋላ ኮስተር ብለው ቁምነገር ያወሯታል፡፡

«ትሩፋቴ እኔ አባትሽ እኮ የጥሊያን አፍ እችላለሁ» ይሏታል፡፡

«ማን አስተምሮዎት አባባ መሳይ?» ትጠይቃለች ለመልሱ እየጓጓች፡፡

«የጥሊያን አሽከር ነበርኩ» ይሏታል እየፈገጉ። ተሰተካከለው የበቀሉት ጥርሶቻቸው ሸር ቢመስሉም እንደ ሽምግልናቸው ያን ያክል አልወየቡም። ከፈገግታቸው ሳይወጡ አንዳንድ ጣሊያንኛ ቃላት ይነግሯታል።

«ከፈለግሽ አንችንም አስተምርሻለሁ» ይሏታል፡፡ እሺም እንቢም አትላቸውም። ጎረቤቶቻቸው ቡና ተርቲም ላይ አቶ መሳይ በጊዜው በሊሉበት ጥንብ እርኩሳቸውን ለምን እንደሚያወጡት የገባት ቆይቶ ነው። ትምህርት ቤት ስለ ጣሊያን የግፍ ወረራ ሲተረክ፡፡

«ይኸ ከርሳም ባንዳ! ለሆዱ ያደረ! ቀን አይወጣም መስሎት ወገኑን ያሰፈጀ! አገሩን የከዳ! ላላወቀው ልብስ ለባሶ ከሰው ጋር ሲውል ሲያዩት ሰው ይመስላል። ለምድረ ጥሊያን አንቁላል ሲሸከም ኑሮ ይኸው ዛሬም አላለፈለት፡፡» ሲል አንዱ

«አንዳንዱ ባንዳ እኮ ብልጥ ነው፡፡ አገሩንና ወገኑን ቢከዳም ራሱን ጠቅሟል፡፡ ጠገራ ብር ሰብስቧል። ልብ ያለው ጀግና ደግሞ የውስጥ አርበኛ ሆኖ ጫካ ከሚዋጉትም የበለጠ ጀብዱ ሰርቷል፡፡ የጠላትን ሚሥጥር ሁሉ ለአርበኞች እያቀበለ ወገኑንና አገሩን ጠቅሟል፡፡ ይኸ እኮ ወይ ለአገሩ አልሆነ ወይ ለራሱ አላወቀበት። በሆዱ ብቻ ሲገዛ የኖረ ከርሳም! ይኸው በሰተርጅና ከስል ሲያከሰል ይውላል፡፡» ይላል ሌላው ቡና ተርቲመኛ ደግሞ፡፡

«እንዴው በመድሐኒያለም እስቲ ዝም ብላችሁ አስቡት ሰው ለማያውቀውና ለማይመስለው የባሕር ማዶ ሰው አድሮ ወገኑን ይከዳል!? ባንዳ ማለት ከዋናው ጠላት የበለጠ ክፉ ደመኛ ነው! የከፋ ጉዳት የሚያደርሰውም ይኸው ውስጥ አዋቂው ነው:: ይኸ ክፉ ባንዳ የጠጣ ሽማግሌ! እኔማ ሳየው እነቀው! እነቀው! የሚለኝ ነገር ነው የሚመጣብኝ!» ይላል በንዴት ከሁሉም በእድሜ የሚያንሰው ሰውዬ ደግሞ:: ገና ጎልማሳ የሚሉት አይነት ነው:: ታሪክ ሰምቶ እንጂ ያንጊዜ በቦታው እንዳልነበር ከእድሜው ማወቅ ይቻላል::

«እናንተዬ ይኸ ሰውዬ እኮ የጥሊያን ዘር ሳይኖርበት አይቀርም። አስተውላችሁ አይታችሁት ታውቃላችሁ? ዐይኑ እኮ ቁርጥ የጥሊያኖቹን የመሰለ ድመት ዐይን ነው::» ይላል ሌላው ቀልደኛ ቢጤ ጎረቤት:: ሁሉም በሳቅ ያውካካል::

«ምን የድመት የመሰለ ዐይኑ ብቻ! ሹል አፍንጫውስ ቢሆን፤ እንደ ነገረኛ ሰው የሳሳው ከንፈሩስ ቢሆን፤ ላዛ ጠጉሩስ ቢሆን ቁርጥ እነሱኑ አይደል እንዴ የሚመስልው» አለ የመጀመሪያው ተናጋሪ::

«ዛዲያ አዲያማ ተሆነ ምን ፍርድ አለበት? ዘመዶቹን በረዳ ይኸን ሰው ምን አድርግ ብላችሁ ነው ቂም ስቅሉን የምታሳዩት? ወገንን መርዳት ተገቢ ነው:: ይኸው እናንተስ ቢሆን ለወገናችሁ አሰባችሁም አይደል በሌለበት ጥሬ ሥጋውን የምታብጠለጥሉት::» አሉ ዝም ብለው ሲያዳምጡ የነበሩት ጠና ያሉት ቡና ተርቲመኛ:: ቀጠል አደረጉና «ወገኖቼ! አባካችሁ ተውት:: ከእንግዲህ ልጡ የተራሰ ጉድጓዱ የተማሰ ሰው ነው:: በደሉ ከባድ--- የአገርና የወገን ክህደት ቢሆንም ሽማግሌ ሰው ነው። ይቅር ለእግዚአብሔር ልንለው ይገባል ወንድሞቼ-- ልጆቼ። ሰራው ለራሱ ይጠጥተው» አሉ አዛውንቱ።

ኢትዮጵያ በዱር በገደሉ በተዋደቁ ልጆቿ ደም ነጻነቷ ሲመለስ ኅብረተሰቡ እንደ አባ መሳይ በጊዜው ለጣሊያን ግፈኛ ወራሪዎች እድረው ሲያገለግሉ የነበሩ ባንዳዎችን ከማኅበራዊ ግንኙነቱ ሁሉ አግልሏቸዋል:: ቡና አብረው እንዳይጠጡ አድሞባቸዋል:: ቀብር ላይ እንዳይውሉ--ሰርግ ላይ እንዳይገኙ ፊት ነስቶ አሸማቋቸዋል:: ከሰው መሀል እየኖሩ ባይተዋር አድርጎ ቂሙን ተወጥቶባቸዋል። እንዲህ ዘመን ሸሮላቸው ነው እንጂ እቶ መሳይም ቡና አጣጭ አልነበራቸውም። ከማኅበረሰቡ ጋር እየኖሩ ከሰው ተለይተው በብቸኝነት አለንጋ ተገርፈዋል። የኋላ ኋላ እድሜ እየተጫናቸው ሲሄድ ጎረቤቱ አውቆ «ይቅር ለእግዚአብሄር» ብሎ ሲተዋቸው በህዘንና በደስታ--- በደግ በክፉ ተቀላቀሉ።

ትሩፋት የአባ መሳይን ባንዳነት ስታስበው በፍቅርና በጥላቻ መሀከል ልቧ ይዋልላል። አባባ መሳይን የአባቷን ያህል ትወዳቸዋለች:: ጣሊያን ደግሞ ኢትዮጵያን በግፍ ወራ ሕዝቦቿን የጨፈጨፈች ፋሽስት ናት። በነጻነት ክብረ በዓል ጊዜ ትምህርት ቤት ታሪኩ ተደጋግሞ ሲተረክ ሰምታለች። ከክብረ- በዓላት ሁሉ ለነፃነት በዓል ልዩ ፍቅርና አክብሮት አላት::





በበዓሉ ክብር ዋዜማ ሽኒ ወንዝ ወርዶ ልብሱን የማያጥብ የአዲስ ዘመን ተማሪ አንድ እንኳ አይገኝም። ሰሰልፉ ራሱን ያዘገጃጃል:: ለዚሁ ዝግጅት ሲባልም እንደ ነገ በዓሉ ሲከበር እንደ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ትምህርት አይኖርም::

የበዓሉ እለት የሰካውት ክቡብ አባላት ታንቡር እየመቱ የተማሪውን ሰልፍ ይመራሉ። ከሰካውት ሰልፈኞች ኋላ የኢትዮጵያን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ የያዙ ሰልፈኞች ይቀጥላሉ:: ጫፉ ሾል ብሎ በተቀረጸ ረጅም እንጨት ባንዲራው ይታሰራል:: ሌላው የእንጨቱ ጫፍ ሸንጥ ላይ ያርፋል:: እጅ በቁንጥ እንደ ኮብራ እባብ ጠምዘዝ ብሎ ባንዲራው ከተሰቀለበት እንጨት ላይ ይውላል:: አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ በሰማያዊው ሰማይ ላይ እየፋን እየቀዘፈ ይንሳፈፋል:: እንደ ቀስተ ደመና ዐይን ያማልላል:: ልብን በሀሴት ይሞላል:: የነፃነት ክበረ-በዓል ጊዜ ባንዲራ ይዘው ከሚመሩት ተማሪዎች መሀከል አንዷ ትሩፋት ነበረች። የያዘችው ባንዲራ ሰማይ ላይ ሲውለበለብ ልቧ አብራ በደስታ ሲቃ ሰማየ ሰማያት ወጥታለች ።

የተማሪው ሰልፍ ከአውራጃው ጽህፈት ቤት በር እስኪደርስ ድረስ በኗሪው እልልታና ጭብጨባ ይታጀባል። በሕይወት የሚገኙት አርበኞች ጥይቱ የግራር ፍልጥ የመሰለ ሁለት ዙር ዝናራቸውን ታጥቀው እየፎከሩ--እየሸለሉ የዚያን ጊዜዉን የተጋድሎ ውሎዋቸውን ሲያስታውሱ የአገር ፍቅር ወኔያቸው አገርሽቶ ምድር አልበቃ ትላቸዋለች:: ዛሬም ከወራሪው ጠላት ጋር ፊት ለፊት የገጠሙ እስኪመስላቸው ድረስ በልህ ሲቃ ይንተገተጋሉ:: እንዳንዶቹ አባት አርበኞችማ ዛሬም የሳሳው ሽበት ጎፈሬያቸው በእልህና በንዴት ይቆማል:: መሳሪያቸውን ጨብጠው በአንድ እግራቸው በርከክ ይሉና እንደገና ደግሞ ብድግ እያሉ እየተንቆራጠጡ ሲፎክሩ ላያቸው የያኔው ውሏቸው እንዴት እንደ ነበር ማየትን ያስመኛል:: ገድለ ታሪካቸው ይነበባል:: በግጥም ይወደሳል:: መዝሙር ይዘመርላቸዋል:: የአባቶቻችን ጀግንነት «አልደፈርም---ለባዕድ አልገዛም» ባይነት በዓሉ ላይ ሲያስተውሉት ልብን በኩራት ይሞላል:: አገርን ያለማስደፈርና ዳርደንበሯን የማስከበር እልህና ወኔ ቀጣዩ ትውልድ እንዲላበስ ሆኖ ልብ ላይ መሀተሙን ያሳርፋል:: ክብረ በዓሉ በከፍተኛ ድምቀት ሲከበር መዋሉ በኢትዮጵያዊነት እንዲኮሩ ያደርጋል:: የአገር ፍቅር መንፈስ ከትውልድ ወደ ትውልድ በደም ውስጥ እንዲሰርጽ የሚደረገው በዚህ መልኩ ነበር:: የታሪክ አሻራው እንዳይጠፋ ሆኖ በቀጣዩ ትውልድ አዕምሮ ውስጥ እንዲህ ይቀረጻል።

«አገራችንን ዳር ደንብሯን አናስደፍርም። ለባእድ ወራሪ አንበረከከም። ባርነትን ለልጆቻችን እናወርሰም» ብለው መሪ ሳይኖራቸው---ምንም ዓይነት ወታደራዊ ስልጠና ሳይወስዱ---ስንቅና ትጥቅ ሳይጠይቁ---በራሳቸው የጥጃ መጠበቂያ ብረት በአገር ፍቅር ስሜት ነደው--- በየጎጡ የጎበዝ አለቃ እየመረጡ ደማቸውን ላፈሰሱ ---አጥንታቸውን ለከሰከሱ አባት ጀግኖች ሰማዕታት በሰልፍ መዘከር ሲያንስ ነው:: ታሪካቸው በወርቅ ቀለም ቢጻፍ እንኳ የሚበዛባቸው አይሆንም:: ለመሆኑስ ከነፃነት በላይ ሲተረክለት---

ሊዘመርለት---ሊቀኙለት የሚገባ ክቶ ምን ነገር ይኖራል!!? ጀግኖች አባቶቻችን ምትክ የሌላትን አንድያ ሕይወታቸውን ገብረው ይችን አገር ዳር ደንበሯን አስጠብቀው አስረክበውናል:: ባርነትን አሻፈረን ብለው ነጻነትን አጎናጽፈውናል:: ከሌሎች አፍሪካውያን ወገኖቻችን በተለየ እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም ፊት በኩራት አንገታችንን ቀና -- ትከሻችንን ነፋ አድርገን እንድንኖር አስችለውናል:: ለዚህም ትሩፋት ከጓደኞቿ ጋር በሰልፍ አደባባይ

አርበኞቻችን አርበኞቻችን ሊቃያችሁ፣

ተሰፋ ሆነ ላገራችሁ።

መኖርያ ሳታጡ ቤት ሳይቸግራችሁ፣

ያገርን መዋረድ አናይም ብላችሁ፣

በዱር በገደሉ የተሰደዳችሁ፣

አይጠፋም ዘልዓለም ሕያው ነው ስማችሁ።

አርበኞቻችን አርበኞቻችን ስቅያችሁ፣

ተሰፋ ሆነ ላግራችሁ።

አጽማችሁ ብዕር ሆኖ ደማችሁ ቀለም፣

የገድላችሁ ታሪክ ተጽፎ አያልቅም።

አርበኞቻችን አርበኞቻችን ሲቃያችሁ

ተስፋ ሆነ ላገራችሁ::

የሚለውን መወድስ አርበኞች መዝሙር ድምጿን ከፍ አድርጋ ዘምራለች:: ባንዳን አውግዛለች:: እንዲህ ጠንክር ያለ የፋሽስት ኢጣልያ ጥላቻ ለተቀረጸባት ትሩፋት አባባ መሳይን የአባቷን ያህል ብትወዳቸውም እንኳ ባንዳ ነበሩ። የጣልያን አሽከር እንደ ነበሩ እሳቸውም አልሸሸጓት:: ባንዳነታቸውን ስታሰብ ፍቅሯና አክብሮቷ በጥላቻ እየተሞላ ፈተና እየሆነባት ብዙ ጊዜ ተቸግራለች:: በተለይ የከብረ በዓሉ ለሞን ዐይናቸውን ባታይ ትመርጣለች። ጎረቤቱ እንደሚያማቸው ራሱን ጣሊያኑን መሰለው ይታዩዋታል:: መጽሐፍ ቅዱስ አንብቢልኝ ብለው እንዳያገኟት ትደበቃቸዋለች:: ከብረበዓሉ አልፎ አስክትረሳው ድረስ ትሸሻቸዋለች::





******

ትሩፋት የልጅነት ዘመኗ በአብዛኛው ከዚያች ዙሪያዋን በተራራ ከታጠረች ትንሽ ከተማ ከአዲስ ዘመን አይወጣም:: የሚያሳዝን— የሚያስደስት--- የሚያስቆዝም--- የሚያስፈነጥዝ የሚያበሳጭ --- የሚያዝናና-- የሚያስለቅስ— የሚያስቅ የሚያስከፋ....... ትዝታ ዘየፈርጁ የልጅነት የሕይወት ገጠመኟ ብዙ ነው:: ከሁሉም በላይ ግን የእንጀራ እናቷ የቤት ጧት የምሬት ንግግር አይረሳትም:: ዛሬም ድረስ ከከፉ ትዝታዎቿ ሁሉ ጎልቶ ያስማታል። ከጥሩ የጧት እንቅልፏ ላይ ይቀሰቅሳታል::

«ትሩፋት!---ትሩፋት!---ኧረ ትሩፋት! የፈጠረኝ ጌታ ነብሰሽን እያሳርፋት! ነብስሽ አትረፍ! አንችን እኮ ነው! እንዲህ ላቃዬ እሰቲሰነጠቅ የምጣራው! ውነት አሁን አልሰማ ብለሽ ነው!? አውቀሽ ነው እንጂ የምታስለፈልፊኝ:: 'አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም አሉ። እንዲህ ተጫዎችብኝ እንጂ። ዳሩ ባንች ምን ይፈረዳል!? ይበለኝ! ኧረ ይበለኝ! በገዛ እጄ ያልወለድኩትን የሰው ልጅ አሳዳጊ ሆኜ የምንገላታው እኔ--- አንቺ ምን ታደርጊ! ኧረ ረጥዷል ተነሽ!! ለውና ከብት ሳይረጋግጠው ወንዝ ውረጅና ውሃውን ቀድተሽ ይዘሽ ነይ ብያለሁ አንቺ ልጅ!--- በጥጋብሽ አምላክ!!»

በማያቋርጠው የአንጅራ እናቷ ክፉ ነገር ባና ትነሳለች። ለምን እንዲህ እንደሚማረሩ ይገርማታል። ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብለው ጥጥ ከመፍተል ውጭ የፈሰሰ ውሃ አያቃኑም። የቤቱ ስራ ሁሉ የወደቀው በእሷ ትከሻ ላይ ነው:: ምን ፍጠሪ እንደሚሏት አይገባትም:: እንደ አሮጌ ጨርቅ ብስክስክ ያለው አመላቸው ሁልጊዜ ያሳቅቃታል። ሊታናናሾቿ እንኳን እቤ ተገን አለችላቸው::

ከታናናሾቿ ጋር ለሦስት የተገኘውን ሰኔልና አጎዛ ጣል አድርገው የሚተኙባት ወለል ዝርባቤው የልጅ ጎን ባይሆን ኖሮ እንቅልፍ ውሰዷቸው ባላደሩም ነበር። አንድ አሮጌ ጋቢና ካሊም ለሦስት እየተጋፈፉ እንዲያድሩ ሲፈረድባቸው «ልጅና ፊት አይበርደውም» በሚለው ተረት ደጋፊነት ሳይሆን አይቀርም። ሰማይና ምድር በወጉ ገና ሳይላቀቅ በእንጀራ እናቷ የምሬት ንግግር ደንብራ ትነሳለች። ለጥቂት ሰዓትም ቢሆን ራሔልና ድልነሳን እንዳያበርዳቸው አስተካክላ አልብሳቸው እንስራዋን አዝላ እየተጣደፈች ወንዝ ትወርዳለች። ገና ያልረገፈው ጤዛ ቅዝቃዜው እግሯን ቆርጦ ሊጥለው ይደርሳል:: እጥንቷ ድረስ ዘልቆ ይሰማታል:: ውሃዋን ቀድታ መላ አካሏ በውርጭ ደንዝዞ ወደ ቤት ትመለሳለች:: ከዚህ ሁሉ አካላዊ ሰቃይ ይልቅ ሰቀቀን የሚለቅባት የእንጀራ እናቷ ክፉ ንግግር ነበር:: ያ ድምጽ ዛሬም ድረስ ከለንት ጊዜ በኋላ እንዳባነናት ይኖራል:: ከጣፋጭ የቤት እንቅልፏ ይቀሰቅሳታል።

የትሩፋት እንጀራ እናት አዘው የማይደከማቸው ሴት ነበሩ:: «ትሩፋት ሱቅ ኸደሽ ይህን ግዢተሽ ነዪ --- ቡን አፍይ --- ቤት ጥረጊ--- ቡሆ አቡኪ--- እንጀራ ጋግሪ --- ወጥ ሰሪ ---

አዚያ ጅ --- አዚህ ተመለሽ ....» ትዕዛዛቸው መቼም አያልቅም። አንዱ በአንዱ ላይ ይደራረባል። ትምህርት ቤት ሁልጊዜ ይረፍድባታል።

እናትና አባቷ ሲለያዩ ፍቺ መሆኑ የገባት ቆይቶ እናቷ በወጡበት ሲቀሩ ነበር። ራስ በራስ አከታትለው የሚወልዱት አናቷ ያኔም ነፍሰ ጡር ነበሩ። አዝልዋል። ሶስተኛዋን ልጅ አጇን ይዘው ይንትታሉ። ከአባታቸው ጋር አንዲቀሩ የተፈረደባቸው ትሩፋት፣ ራሄልና ድልነሳ ነበሩ። አውቶብስ ተራ ድረስ ሄደው ሲሸኟቸው እንደ ሁልጊዜው ዘመድ ጠይቀው የሚመለሱ ነበር የመሰላቸው። እንዲህ እንደ ዋዛ የሚለዩዋቸው መሆኑን በፍጹም ያልጠረጠሩትና ያልጠበቁት ነበር።

«ትሩፋቴ» አሏት አናቷ ጸጉሯን እያሻሹና ዐይን ዐይኗን እያዩ ወደ ገፋ ሆዳቸው አያስጠጓት። «ከእንግዲህ ብልህ ነው መሆን ልጄ። እያደጉ አንጂ ልጅ አየሆኑ መኼድ የለም። ልባም ሁኚ የእኔ ልጅ። በትምህርትሽም በርቺ። የልጅና የጢስ መውጫው አይታወቅም። ማን ያውቃል? እንጀራሽም ይሆን ይሆናል። ተንግዲህ እነዚህን ገና ተሳት ተውሀ የሚሉ ታናናሾችሽንም ጠብቂያቸው። ያለ አንቺ ሀይ ባይና ተመልካች ሰው የላቸውም ልጄ! አሺ የእኔ ቆንጆ» እያሉ ሲመክሯት ላለማልቅስ የመጨረሻውን ጥረት አያደረጉ ነበር፤ ግን አልቻሉም። እንባቸው ግድቡን ጥሶ እንደ መስከረም ዝናብ በወፍራሙ ዱብ ዱብ ማለት ጀመረ። ትሩፋት ምክራቸው በቅጡ ባይገባትም ሲያለቅሱ ስታይ ግን ሆዷን ባር ባር አለው። አብራቸው ማልቀስ ጀመረች። ራሄልና ድልነሳ በነገሩ ግራ ተጋብተው እናታቸውንና ትሩፋትን እያፈራረቁ በጭንቀት ይመለከታሉ። እናት ሦስቱንም ልጆች አንገታቸው ስር ሸጉጥ አያደረጉ ስመው ሁለቱን ይዘው ሆዳቸውን አየገፉ ተሰናብተዋቸው ሄዱ። አነትሩፋት የእናታቸውን መምጣት ለብዙ ቀናት መንገድ መንገዱን አያዩ በተስፋ ጠበቁ። እናታቸው ግን ሳይመለሱ ቀሩ።

ትሩፋት አባቷ ከአገቧቸው ሚስቶች የማትረሳቸው ሁለቱን ነው። በአድሜ ጠና ያሉትን መሃኗንና አራት የወለደችላቸውን ልጅ አግሯን እንጀራ አናታቸውን። ሁለቱም ለልጅ የሚመች ፀመል አልነበራቸውም። ትሩፋት ደግሞ የእንጀራ አናት አስከፊ ገጽታ በአዕምሮዋ የተቀረጸው ገና የሁለተኛ ከፍል ተማሪ ሆና ነው። መምህር ኃይሌ የአማርኛ መምህራቸው ነበሩ። ላሜ ቦራ የሚለውን የተረት ጽሑፍ ክፍል ውስጥ ከተማሪዎቹ ፊት ወጥታ አንድታነብ ያደርጓታል። ጽሑፉ ውስጥ የተሳለችው እንጀራ አናት በእንጀራ ልጇ ላይ የምትፈጽመው በደል ልቧን ነካው። አንብባ መጨረስ አልቻለችም። እንባ ተናነቃት። መምህሯ ሁኔታዋን ሲያዩ ንባቧን አቋርጣ አንድትቀመጥ አደረጉ። ክፉ አሻራው ግን አብሯት ቀረ። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም እንጀራ አናቶቿን ሁሉ ስትፈራ፣ ስትሰቀቅና ስትሰጋ የኖረችው። ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂ የምታደርገው ታድያ አባቷን ነው።

«ስድስት ከወለደች በኋላ አናታችን መፍታቱ ሃላፊነት የጎደለው አባት ተግባር ነው።» እያለች ከስንት ጊዜ በኋላ ሁሉ ታዝንባቸው ነበር። ኋላ ላይ ግን ሁሉንም ከልቧ ይቅር





ብላቸዋለች። አባቷና ልጅ አግሯ የአንጀራ አናታቸው የሞቱት ተከታትለው ነበር። ቅሬታዋን ሁሉ አንስታ እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ አቅሟ የፈቀደውን ሁሉ በማድረጓ ከበፀት ተርፋለች። ሞት ሳይቀድማት ቂሟን ማንሳቷንና ይቅርታ ያደረገችላቸው መሆኗን ስታስበው መንፍሷን ደስ ይለዋል።

የነትሩፋት አባት አቶ ማንያዘዋል ገቢያቸው ከመንግሥት ሰራተኛ ጓደኞቻቸው ቢበልጥ እንጂ አያንስም ነበር። የአርበኛው የፊታውራሪ ጣሰው ልጅ በመሆናቸው ተጨማሪ የመሬት እበል አህል ይሰፈርላቸዋል። ምን ያደርጋል? የነትሩፋትን እናት ከፈቱ በኋላ ሚስት አውጭ አግቢ ሆኑ። በዚያ ላይ የወጣላቸው ጠጪ። ሞቅ ሲላቸው ደግሞ ከበር ሥልስ ሲጋብዙ ዐይን የላቸውም። ለኪሳቸው አይሳሱም። የመሸታ ቤት አዝማሪ ሁሉ ሆቺን አመላቸውን አውቆባቸው

ነይማ ላሳይሽ ሸጋ ሸጋውን፣

አዲስ ዘመን ሆና አባ መስጠትን፣

ለኪሱ አማይሳሳ ማንያዘዋልን። እያለ ያሞካሻቸዋል። አባቷ ሞቅ ሲላቸው ሲጋስ ናቸው። ኪሳቸው እስኪራገፍ መዥረጥ እያደረጉ መሸለሙን ያውቁበታል። በዚያ ላይ ጨዋታ ያውቃሉ። ወጋቸው ጥርስ አያስገጥምም። እንዳንድ ጊዜ በቀልድም ጎሸም ማድረጉንም ይችሉበታል። «ሌላው አለቃ ገብረሀና» ይሏቸዋል ጓደኞቻቸው። በዚህ የመሸታ ቤት ሙገሳ እየተገፋፉ አዚያው አምሽተው ሞቅ ብሏቸው አቤት ይገባሉ። ትሩፋት አባቷ ሞቅ ሳይላቸው በጊዜ አቤት የገቡበት ቀን ብዙም ትዝ አይላትም። በዚህ አመላቸው ጨለማው ይዞት የሚመጣው ከሚስታቸው ጋር ሁሌ ጭቅጭቅና ንትርክ ነበር።

«እንደው እንቱዬ አድሜም አያስተምሮዎ! ሁለት ጠጉር ከማውጣትና ከመመለጥ ወዲያ ተነድ አያበቅሉ። ከቶ መቼ ሊሸመግሉ ይሆን? ሁሉም ወንድ ከቤቱ አይወጣም አይባልም። ሁሉም ወንድ አይጠጣም አይባልም። ዛድያ ያመሉን አድርሶ በግዜ ከቤቱ ከትት ይላል። ቤተሰቡን አይበጠብጥ--ገመናውን ጎረቤት አይሰማው። አንዴው እኔስ በሆነ አላሳዝነዎትም እስከ ዶሮ ጩኸት ተጎልቼ እስዎን ስጠብቅ።» ይላሉ ሚስት በማስተዛዘን ጭምር።

«ሙገኛ! አልጋውን ይገፍብሽ የሄድኩ አትመስይም አንዲህ ስታማርሪ! አተኝም ነበር። ምን ይጎልትሻል!?»

«ቆይ ብቻ ይንጋ እንዲህ አንደ ተጫዎቱብኝማ አይቀሩም። ይላሉ ሚስት ንዴት እየተናነቃቸው።

«ለምን ዛሬውኑ ተሸኝተሽ አታድሪም:: መንገዱን ጨርቅ ያድርግልሽ::»

አቶ ማንያዘዋል የስካር እንቅልፍ እስኪጥላቸው ድረስ ጭቅጭቁ አያበቃም። ከተኙ በኋላ ሚስት ቀስ ብለው ከጎናቸው ይተኛሉ። እንደ ጭቅጭቃቸውና ጠባቸው አድረው የሚውሉ አይመስሉም:: እነትሩፋት ግርም የሚላቸው ታድያ ጧት ላይ በአዲስ ፍቅር ሲሞነሸነሹ ማየታቸው ነበር:: የቀንና የሌሊት ሁለት የተለያዩ ፍጡራን ይመስሏቸዋል::

አንድ ቀን ግን ቁርጥ ሆነ:: አቶ ማንያዘዋል እንደ ሌላው ጊዜ አምሽተው በእኩለ ለሊት አልገቡም:: ሚስታቸው እንደ ተለመደው እንቅልፍ እያንገላጀጃቸው ብዙ ጠበቋቸው:: እሳቸው ግን ንግቶም ብቅ አላሉም:: ሚስታቸው የሰላም አልመሰላቸውም:: ሀሳባቸው የተቀላቀለ ነበር፤ ንዴትና ስጋት:: ረፋዱ ላይ አቶ ማንያዘዋል እየተጎማለሉ ከተፍ ሲሉ ግን ለየላቸው:: ተናደዱ! በ--ጣም ተናደዱ! መናቃቸው አንገበገባቸው:: አቶ ማንያዘዋል ወደ ቤት ሲገቡ ሚስት ነጠላቸውን እንጠልጥለው ወደ እህታቸው ቤት ውልቅ አሉ:: እቶ ማንያዘዋል «መንገዱን ጨርቅ ያድርግልሽ» ብለው እንዳልተሳለቁ ሁሉ ተጨነቁ:: ምንም ቢሆን ከአስር ዓመት በላይ አብረው የኖሩ ሚስታቸው ናቸው:: ከእንግዲህ በሽምግልና ዕድሜያቸው ሚስት ማውጣት ማግባቱም አሳፈራቸው:: አስታርቁኝ ብለው ሽማግሌ ላኩ ቄስ መነኩሴ አልቀራቸውም:: ሚስታቸው ግን

«ከእንግዲህ እኔና ማንያዘዋል በአንድ ጣራ ሥር አብረን ኖረን አንሶላ አንጋፈፍም:: ወንድሜን ይሁኑብኝ» ብለው እንቢታቸውን በማህላ አጸኑ:: በቃ በዚሁ ተለያዩ:: ከዚያ በኋላ ነበር እራት የወለደችላቸውንና እስከጊዜ ሞታቸው አብራቸው የኖረችውን ልጅ እግሯን ሚስታቸውን ያገቡት::

በዚያች የወለሷ ድንጋይ ባፈጠጠ፤ የግርግዳዋ ምርጊት በረጋገፈ፤ ቤት ውስጥ የነትሩፋትን ኑሮ ገሀነም የሚያደርገው ,ዘወትር የማያቋርጠው የአባታቸው ስካርና ጭቅጭቅ ነበር። በዚያች ቤት ውስጥ መኝታው አይመች--- ምግቡ አይመች--- ኑሮ አይመች። የእናት ናፍቆት እያብሰለሰላቸው --- የእንጀራ ናት ምላስ እንደ ሳት ላንቃ እየገረፋቸው --- የሰካራም እባት አተካራ ሰቀቀን እየለቀቀባቸው ---ኑሮ ተባለና ይኖራሉ። ትሩፋት እሷና ታናናሾቿን ከዚህ የገሀነም ኑሮ እንዴት ማውጣት እንዳለባት ስታስብ ዙሪያው ገደል ይሆንባታል። መላው እንደ ሰማይ ይርቃታል።

እናቷ እሷን፤ ራሔልንና ድልነሳን ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብተዋቸው ሊለዩዋቸው የተናገሩት ንግግር በእዝነ ህሊናዋ ደጋግሞ ያንሾካሹካል። ግድቡን ጥሶ እንደ ጅረት የወረደው እንባቸው በዐይነ ሕሊናዋ ይመጣል። የአደራ ቃል መሆኑ የገባት ቆይ---ቶ ነው። ለታናናሾቿ ትንሰፈሰፋለች። ርሀባቸው ይርባታል። ጥማቸው ይጠማታል። ጉዳታቸው ሁሉ ጉዳቷ ነው። የአደራ ልጆቿ ይመስሏታል። እነሱን ከዚህ የሰቀቀን ኑሮ ለማውጣት የትም





ብትሄድ ግድ የላትም። ግን የት? አንድ ነገር ግን በሩ---ቁ ይታያታል። ትምህርት መማር--- ግን ገና ስድስተኛ ክፍል ናት---- እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል--- ስድስት የሰቆቃ ዓመታት!

******

ትሩፋት በትምህርት ቤት ሕይወቷ ከማትረሳቸው ጓደኞቿ አንቺነሽ አብጤ ዋነኛዋ ናት። አንቺነሽ እግዜሩ ሲፈጥራት ተንኮል ያደላት ልጅ ነበረች። ቅጽል ስም እያወጣች የማታስቅበት አስተማሪና ተማሪ አልነበረም። በነገር አተናኩሳ የማታጣላውና የማታደባድበው ተማሪ አይገኝም። ታዲያ ተንኮስ አድርጋ እሷ ዘወር ነው። ትሩፋትን ሳይቀር ከስንት ተማሪ ጋር አጋጭታታለች። አንቺነሽ ይሀ ድርጊቷ ተንኮል አይመስላትም:: ለሷ ጨዋታ ነው:: መሳቂያ-- መደሰቻዋ::

አንቺነሽ ተንኮለኛም ብትሆን ትምህርቷ ላይ ቀልድ አታውቅም ነበር። ትሩፋት ጓደኝነቷን የመረጠችው በዚሁ በትምህርት ወዳድነቷ ነው። የስድስተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን በጥሩ ውጤት እንዲያልፉ ሌሲት ሌሊት እየተነሱ እንዲያጠኑ አጥብቃ ትመከራት ነበር:: ትሩፋት ደግሞ የእንጀራ እናቷን ጭቅጭቅ ትፈራለች:: ያቺን ትንሽ ኩራዝ ለኩሳ ለጥናት በሲሊት ብትነሳ ምን ሲፈጠር እንደሚችል ታውቃለች:: እንጀራ እናቷ ሴትን ልጅ ትምህርት ቤት መላክ የትም ስድ እንደ መልቀቅ የሚቆጥሩ ሴት ናቸው:: ሴት ልጅ ቤት ውስጥ አንገቷን ደፍታ የእናቷን ሙያ ተምራ ባሏን አግብታ ልጆችን ወልዳ ማሳደግ አለባት ብለው በጥብቅ ያምናሉ:: ትሩፋትና ራሔል ከትምህርት ቤት ከተመለሱ በኋላ ደብተርና መጽሐፍ ብሎ ነገር ዐይኑን እያዩትም:: እንጀራ እናታቸውን ያስቆጣል:: በመምህራኖቻቸው የሚስጠውን የቤት ሥራ ሁሉ ሰርተው መጨረስ ያለባቸው እዚያው ትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ ነው:: ድልነሳ ወንድ በመሆኑ ከዚህ ዓይነቱ የእንጀራ እናታቸው ተፅእኖ ተርፏል::

የለሲት ጥናት በተነሳ ቁጥር እንደ አንቺነሽ የእናቷን እጠገቧ መኖር ትመኛለች ትሩፋት:: በርቺ እንዲሏት:: ሌሊት እንዲቀሰቅሷት:: አንቺነሽ ደግሞ ይህ የትሩፋት ችግር አይገባትም:: ሆድ የሚያስብሳት መሆኑንም አትረዳላትም:: ጧት ጧት በተገኘኙ ቁጥር የመጀመርያ ጥያቄዋ ይኸው የሌሊት ጥናት ጉዳይ ነበር::

«ዛሬ እኮ የክፍል ጠረጋ ተረኞች ነን። ረስተን እንዳንሄድ» አለች ትሩፋት:: እንቺነሽ እንደ ሁልጊዜው የሌሊት ጥናት ብሎ ነገር እንዳታነሳባት ቀድማ::

«ኧረ አንቺ ትሩፋት ያ-- ማን ነበር ስሙ? በተራ ቁጥሩ ከእኛ ጋር አይገናኝም። ለመሆኑ በምን ምክንያት ነው ከክፍል ጠረጋ ምድባችን ውስጥ ሊገባ የቻለው?» አለች አንቺነሽ::

«ምድባችን ውስጥ ሦስት ወንዶች አሉ። ስለ የትኛው ነው የምታወሪው?» አለች ትሩፋት የለሊት ጥናት ብሎ ነገር ባለመነሳቱ ደስ እያላት::

«ያ--እንኳን ከወረዳ የመጣው ጠፍቶሽ ነው? ያ መምህር አየረዳ የሚያስተምረው!» አለች አንቺነሽ ፊቷን በንቀትና በማንቋሸሽ ከስክስ አድርጋ፡፡

«ፍቅሩን ማለትሽ ነው? ከቁጥር ትርፍ መጥቶ ይሆናል፡፡» የፍቅሩ ከእነሱ ጋር መመደብ ምንም አልመሰላትም ትሩፋት፡፡

«ፍቅሩ ነው ስሙ?» አለች አንቺነሽ፡፡ ያናናቀች መስሏት ነው እንጂ አሳምራ ታውቀዋለች። እሱ ከሚባሉት በጣም ጎበዝ ተማሪዎች አንዱ ፍቅሩ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪ ያውቀዋል፡፡

«መመደቡንስ እሺ ይሁን ከእኛ እኩል የማይጠርገው ዛድያ ምን ልሁን ብሎ ነው? እስቲ አሁን እሱ ከሌሎቹ ወንዶች ልጆች በምኑ በልጦ ነው ዝም ብሎ የሚጀነነው?» አለች አንቺነሽ፡፡ ጥሎባት ጎበዝ ተማሪዎችን አትወድም፡፡ ደረጃዋን ዝቅ የሚያደርጉባት መስሎ ስለሚታያት ጥምድ ነው የምታደርጋቸው፡፡ የክፍሉ አንደኛ ተማሪ ሆና ለመገኘት ሁልጊዜ ትጥራለች፡፡ ፍቅሩን የመሳሰሉ እሳት የላሱ ተማሪዎች ደግሞ እያቀምሷትም፡፡ ተስፋዋን ይገሉባታል፡፡ በዚህ ምክንያት ፍቅሩ ከምትጠላቸው ተማሪዎች አንዱ ነው፡፡ ባታየው ትመርጣለች፡፡ አሁን ደግሞ የክፍል ጽዳት አብሯት ተመድቧል፡፡ ይበልጥ የሚያናድዳት ደግሞ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ቅጠል ቆርጦ አምጥቶ አለመጥረጉ ነው፡፡ መጨረሻ ላይ ቆሻሻውን አፍሶ የሚያስወጣው ግን እሱ ነው፡፡ አንችነሽ በዚህ ድርጊቱ ለጠብ ሰበብ ትፈልጋለች፡፡ ከክፍሉ ጎበዝ ተማሪዎች አንዱ በመሆኑ እየኮራ ይመስላታል፡፡ ከትምህርት በኋላ የመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ሲደወል ክፍል የሚያጸዱ ተማሪዎች ብቻ ወደ ኋላ ቀሩ።

«አንተ ፍቅሩ ጥረግ እንጂ--- ለምን ቁመህ ታየናለህ?» አለች ትሩፋት። አንችነሽ የተናገረችውን አስታውሳ፡፡

«መጨረሻ ላይ ቆሻሻውን የማወጣው እኔ አይደለሁ» አለ ረጋ ብሎ።

«ነቅተንብሃል አባክህ! አቧራ በአፍ በአፍንጫህ እንዳይገባ ብልጥ መሆንህ ነው እንጂ!» አለች አንቺነሽ ነገር ነገር እያላት።

«እውነት! እንደሱ አስቤ አይደለም። እናንተን ቅር ካላችሁ ግን እሺ እጠርጋለሁ» አለ። አሁንም ረጋ እንዳለ፡፡ አርጋታው የልጅ አይመስልም። ቅጠል ቆርጦ አምጥቶ ይጠርጋል መሰሏቸው ጥቂት ጠበቁት፡፡ ቆም ከማየት ውጭ ያደረገው ነገር አልነበረም። አንቺነሽ መናደዷ ፊቷ ላይ ያስታውቃል፡፡ ፍቅሩ ሳያይት ትሩፋትን ጠቀስ አደረገቻት። ጠጋ ስትላት የሆነ ነገር በጆሮዋ ሹክ አለቻት። ትሩፋት ከአቡጀዲ ጨርቅ ራሷ የሰፋችትን የደብተር መያዣ ቦርሳዋን ብድግ አደረገች። አንቺነሽ ፍቅሩ ሳያስበው ከኋላዉ ሄዳ ወደ ኋላ እጣምሮ ይዞት የነበረውን እጁን ከወገቡ ጋር ጥርቅም አድርጋ ያዘችው፡፡ ምን ሊያደርጉ እንደ ሆነ ለማሰብ እንኳ ጊዜ አላገኘም፡፡ ትሩፋት ፈዞ ቆሞ ይመለከታት የነበረውን ፍቅሩን ሳያስበው ባለ በሌለ ኃይሏ ተንጠራርታ በጥፊ አጮለችው፡፡ ለመከላከል ፋታ





አልነበረውም፡፡ አንቺነሽና ትሩፋት ተያይዘው የነፍስ አውጭኝ ሩጫ በረሩ። ራቅ ካሉ በኋላ እየተሳሳቁ ቆም አሉ፡፡ ፍቅሩ ተከትሏቸው እንደ ሆነ ዘወር ብለው ተመለከቱ። እሱ ለራሱ ከክፍልም አልወጣ። የመደንገጥ ይሁን የመገረም ባለየው ስሜት ውስጥ ሆኖ ጥፊ የቀመሰ ጉንጩን እያሻሸ ባለበት እንደ ሀውልት ደርቆ ቆሞ ነበር። በተፈጠረው ድንገተኛ ሁኔታ ሌሎቹ ሁለቱ ወንዶች ልጆች እንኳ ከው ብለው ደንግጠው ፈዘው እየተመለከቱት ነበር፡፡ ወደ ሀሊናቸው ሲመለሱ የተጀመረውን የክፍል ጠረጋ ጨርሰው ወደ የቤታቸው ሄዱ፡፡

ጧት ትሩፋትና ፍቅሩ ተያዩ፡፡ አንቺነሽ ዘግይታ ነበር ክፍል የገባችው፡፡ ፍቅሩ ከሁልጊዜው የተለየ ሁኔታ አልታየበትም። ትሩፋት ግን «አዘናግቶ ይጣላኛል» ብላ ፈርታ ስትሸሸውና በዐይን-ቁራኛ ስትጠባበቀው ዋለች። ፍቅሩ እንደ ፈራችው ሊበቀላት አልሞከረም፡፡ የቃሪያ ጥፊውን ቀምሶ በክፉ ዐይኑ እንኳ አላያትም፡፡ እንደ ተለመደው እይታውን ግን ከእቅስቃሴዋ ላይ አይነቅልም፡፡ በሄደችበት ሁሉ ዐይኑ ይንከራተታል፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ፍቅሩ ከትምህርት ቤት ቀረ። ትሩፋት ከስጋት ተገላገለች፡፡ ትምህርቱን በማቋረጡ ግን ውስጥ ውስጧን ከነከናት። ቆይታም ወደ እብናት መመለሱን ሰማች። አየረዳ ከሚያስተምረው መምህር ክፍሌ ባለቤት ጋር መስማማት አልቻለም ነበር እሱ። ትሩፋት ከልቧ አዘነችለት። እንዲህ ሲሄድ ነገር በአንቺነሽ ተገፋፍታ ጀሮ ግንዱ እስኪ.ቃጠል ድረስ በጥፊ ማጮሏ ቆጫት። አንቺነሽ ግን

«የት አባቱ! ይኸ ጥጋበኛ! ኩራተኛ! እሱ በዚህ እጉል ኩራቱና ትዕቢቱ እንኳን ባአድ እናቱም አትችለው» ብላ ተሳለቀችበት፡፡ ፍቅሩ እብናት ከአንድ ዘመዱ ጋር ሆኖ ትምህርቱን መማር ጀመረ፡፡ ስምንተኛ ክፍል ሲሆን መምህር ክፍሌ የአዲስ ዘመን ጤና ጣቢያ ሰራተኞች ባቋቋሙት የበጎ አድራጎት ድርጅት ውስጥ እየተረዳ እንዲማር ነገሮችን አመቻቸለት፡፡ አዲስ ዘመን ተመልሶ መጥቶ ያለስጋት ትምህርቱን ቀጠለ፡፡

******

የሊቦ አውራጃ ዋና ከተማ ለሆነችው አዲስ ዘመን ትልቁ ትምህርት ቤት የነበራት እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ ነበር፡፡ ለዚህ ይመስላል ተማሪዎቹ ስምንተኛ ክፍል መድረስ ማለት በእውቀትም---በእድሜም--- በአካልም---- በአጠቃላይ በሁሉም ነገር ማደግ መስሎ ይታያቸዋል፡፡ ስምንተኛ ክፍል ሲደርሱ ከከተማዋ ልጆች ሁሉ---ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ሁሉ---የበላይነቱን ቦታ የተጎናጸፉ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ኮራ--- ጀነን የማይል የስምንተኛ ክፍል ተማሪ አልነበረም፡፡ የስምንተኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ካለፉ ወደ ሌላ አውራጃ ሄዶ መማር ከቤተሰብ ጫናና ቁጥጥር መላቀቅ ይኖራል፡፡ «አታምሽ! በዚህ ግባ! በዚህ ውጣ! ይህን አድርግ ይህን አታርግ!» እያለ ትዕዛዝ የሚሰጥ ተቆጣጣሪ አይኖርም፡፡ ምንም እንኳ ቀለቡን ያው ወላጅ ቢችልም በነፃነት በራስ ጎጆ የሚኖርበት እድል ይገጥማል፡፡ የትምህርት ፉከከሩም ቀልድ አልነበረም፡፡ እንዱ ከእንዱ ተሽሎ

ለመገኘት ጥረቱ ከባድ ነበር፡፡ የዛሬ ተማሪዎች ለአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከሚያደርጉት ዝግጅት ቢልቅ እንጂ አያንስም ነበር፡፡ ብቻ ያኔ ሁሉም ነገር ስምንተኛ ክፍል ሲደርሱ ይጀማምራል፡፡ አደኩ--አደኩ ማለትና አዋቂ መስሎ ለመታት የማይደረግ ጥረት አልነበረም፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች የፍቅር ሀ--ሁ የሚጀማምራቸውም እዚሁ ስምንተኛ ክፍል ሲደርሱ ነው፡፡

«ፍቅሩ ለምን ከእኔ ቦታ ላይ ተቀመጥህ? የራስህ ቦታ አለህ አይደል፡፡»

«ለሦስትም እኮ ይበቃል፡፡ ነይ አብረን እንቀመጥ» አለ ፍቅሩ አብሮት ወደ ተቀመጠው ልጅ ጠጋ እያለ፡፡ ውስጥ ድረስ ሰርሰረው በሚያዩዋት ትናንሽ ዐይኖቹ ጭምር እየተለማመጣት አንድ ዴስክ ላይ እንዲቀመጡ ይወተውታል።

«ተጣብቤ መቀመጥ አልፈልግም፡፡ አንተ ለምን ከቦታህ አትሄድም?» ዐይኑን እየሸሸች ትመልስለታለች። ትላልቅ ዐይኖቿ ሰው ወግተው ማየት አይወዱም። ልክ እንደ አባቷ--እንደ አቶ ማንያዘዋል፡፡

«አልሄድም በቃ! እዚህ መቀመጥ ደስ ይለኛል!» ፍቅሩ ፍርጥም ብሎ ይመልስላታል፡፡

«ከእኔ ቦታ!?»

«አዎ ከአንቺ ቦታ!»

«ደረቅ! ምን ዐይነቱ ደረቅ ነው በሀና ማርያም! ቆይ አሁን መምህር ሲገባ አለቦታህ መቀመጥህን ስነግርልህ ልክ ትገባ የለ!» ትዝትበታለች። በግድ የለኝም ዓይነት ትከሻውን ይሰብቅባታል፡፡

«እዚህ ከኛ ጋር መቀመጥ ካልፈለግሽ ደግሞ ከእኔ ቦታ ላይ ሄደሽ መቀመጥ ትችያለሽ፡፡»

«ከአንተ ቦታም ሆነ ከአንተ ጋር መቀመጥ አልፈልግም። ከቦታዬ ላይ ተነስ በጉልበትህ አምላክ!» ትለዋለች ትሩፋት አልህና ንዴት እየተናነቃት፡፡ ሲጨቃጨቁ መምህር ይገባል። እንደ ዛተችው ለገባው መምህር አትነግርበትም። ከሱ ቦታ ላይም ሄዳ አትቀመጥም፡፡ እየተናደደች ሌላ ባዶ ዴስክ ላይ ትቀመጣለች። እቤት የእንጀራ እናት ምላስ እንደ መንጠር እሳት ይገርፋታል። የማያልቀው ትእዛዛቸው ያዋከባታል። ለሰከንድ እንኳ ሳታርፍ ነው ትምህርት ቤት የምትመጣው። እዚህ ደግሞ በሰላም እንዳትማር ፍቅሩ የሚሉት ተማሪ በሆነው ባልሆነው ይተናኮላታል።

«አንተ ፍቅሩ አታርፍም ማለት ነው፡፡ መጽሐፌን ደሞ ምን ልሁን ብልህ ነው የወሰድከው?»





«ላጠናበት፡፡»

«ወይ ጉ---ድ!! ለምን በራስህ መጽሐፍ አታጠናም? ደግሞስ ሳትጠይቀኝ ያለኔ ፈቃድ ነው ዝም ብለህ ብድግ አድርገህ የምትወስደው? አንተ ልጅ ግን በጣም አላበዛኸውም!? በጣም አልተዳፈርከም!?» በቁጣ ትጠይቀዋለች፡፡

«የእኔ ጠፍቶብኝ እኮ ነው። ብጠይቅሽኖሮ ግን 'እሺ' ብለሽ ትሰጭኝ ነበር? እውነትሽን ነው ትሩፋት ትሰጭኝ ነበር?» ቁጣዋን ቻል ብሎ ዐይን ዐይኗን እያየ ይጠይቃታል።

«ሳታስፈቅደኝ በገዛ እጅህ ብድግ አድርገህ ከወሰድከ በኋላ በጥያቄ ብታጣድፈኝ ምን ዋጋ አለው? በል አሁን ስጠኝ፡፡»

«አላመጣሁትም ትሩፊ ይቅርታ!»

«አንተ ልጅ ግን እኔን ለማናደድ ነው አይደል ሆን ብለህ እንዲህ የምታደርገው?»

«ትሩፋት ሙች ላናድድሽ ብዬ አይደለም፡፡ እንድትናደጂ በፍጹም አልፈልግም፡፡ ነገ አመጣልሻለሁ እሺ ይቅርታ፡፡ አ!-- አ! ይቅርታ አሺ!-- በአናትሽ ትሩፊ! ይቅር ብዬሃለሁ በይኝ--ደስ እንዲለኝ» ይላታል እየለመናት--- እየተለማመጣት፡፡

«አንተ ግን በጣም ጠግበሃል አሺ! እዚህ አገር ወላጆችህ የሉም ብዬ እዝኜልህ ነው እንጂ ከሰሼ ማስቀጣት ጠፍቶኝ እንዳይመስልህ፡፡»

«እውነት ትሩፋት! የኔ መጽሐፍ ጠፍቶብኝ ነው፡፡ ረፍዶብኝ ስቸኩል ደሞ ያንችን ረስቸው መጣሁ፡፡ ይቅርታ ካናደድኩሽ!»

በሚቀጥለው ቀን መጽሐፏን ቢመልስላትም ሌላ ጊዜ ደግሞ አዘናግቶ ደብተሯን ወይ አንድ ነገሯን ይወስዳል።

«በፊት ያናደድከኝ ሳይበቃህ ዛሬ ደሞ ደብተሬን ወሰድክ አይደል? አንተ ልጅ አታርፍም ማለት ነው?» በዝምታ ደብተሯን ይመልስላታል። ሲመልስላት ግን ያልጻፈችው ካለ ጽፎ፤ ያላስተካከለችውን ሁሉ አስተካክሎና በአበባና በልብ ስዕል ባሸበረቀ ሽፋን ሸፍኖ ያመጣላታል። ጽሁፉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ጽሁፍ አይምስልም። የተፈተገ ቆሎ ይመስላል። አስተካክሎ ጽፎ ማምጣቱን እንኳ እሷም አትጠላውም። ብዕር አጣጣሉን ትወድለታለች። የሚስላቸው ስዕሎች ደስ ይሏታል፡፡ ግን ደግሞ ያለእሷ ፈቃድ ንብረቷን ብድግ እያደረገ መውሰዱ ያናድዳታል፡፡

ፍቅሩ እንዲህ እያበሳጫት ለትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ወይም ለሚመለከታቸው መምህራን ከሳ ለምን እንደማታስቀጣው ለራሷም አይገባትም። ብትከሰው ሴት ተማሪን እንደ ተተናኮሰ ባለጌ ተማሪ ተቆጥሮ ጧት ሰንደቅ አላማ ሳይ ባንዲራ ለማውጣት በተሰለፈው ተማሪ ፊት ለመቀጣጫ እንደሚገረፍ አጥታው አይደለም፡፡ እንዲህ እንደሱ «ልጃገረዶችን ተዳፈራችሁ---ተሳደባችሁ---አንጓጠጣችሁ» ተብለው ጥቂት የማይባሉ ወንድ ተማሪዎች ሲቀጡ አይታለች፡፡ ፍቅሩን ከሳ ልታስቀጣው ብዙ ጊዜ አስባ ለምን እንደ ሆነ ባይገባትም ትታዋለች፡፡ ችግረኛ ተማሪ ስለሆነ---ወይ ደግሞ ከእናትና አባቱ ተለይቶ በአርዳታ የሚማር ምስኪን ተማሪ ሰለ ሆነ አዝናለት ይሁን ብቻ ምክንያቱን ለይታ አታውቀውም። እንዲሁ አርሷው ተናዳ--- አሷው ፎከራ መልሳ ትተወዋለች። ከሁለት ዓመት በፊት በክፍል ጠረጋ ምክንያት በተፈጠረ አለመግባባት ሳያስበው ጀሮ ግንዱ አስኪነድ በጥፊ ያጮለችው ረዳት አጥቶ ሲሄድ ሰምን ነበር። ትምህርቱን አቋርጦ ወደ አብናት ሲመለስ ግን ሰማንም ያሳዘነችውን ያህል አዝናለት ነበር፡፡

እንዲህ ሲያበሳጫት ደግሞ «ምነው ያኔ አቋርጦ እንደ ሄደ በዚያው በቀረ ኖሮ!» አሰኝቷታል። እድሜ ለአዲስ ዘመን ጤና ጣቢያ ሰራተኞች! እየረዱ ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ፍቅሩ ሆነ፡፡

ትሩፋት ይህ ሁሉ ጫና ቢኖርባትም ስምንተኛ ክፍል ከፍቅሩ ጠናና ከደረጀ ሙሳቱ በስተቀር አሉ ከሚባሉ ጎበዝ ተማሪዎች አንዷ ነበረች። ፡፡ ከሁለቱ የአብናት ልጆች ጋር ግን ማን ይወዳደራል፡፡ በተለይ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታቸው እንኳን ተማሪውን መምህራኑንም ያስገረመ ነበር። አብናት ወረዳ ማን እንግሊዛዊ ፈረንጅ ወርዶ አሰለጠናቸው ያሰኛል። ታድያ በሌሉበት በተማሪው ይታማሉ። ይሄ ሁሉ ጉብዝና የተገኘው በደብተራ ድግምት ነው ተብሎ ውስጥ ውስጡን ይወራል፡፡ ለዚህ ሐሜት መነሻ የሆናቸው ደግሞ የደረጀ አባት ቄስ መሆናቸው ነበር፡፡ የነፍቅሩ ጉብዝና በድግምት መሆኑን አምና የማትቀበል ትሩፋት ብቻ ነበረች፡፡ አባቷ ጠንቋይ፣ ፉቅራ ቀሪ፣ መጽሐፍ ገላጭና ቅጠል በጣሽ ብሎ ነገር አያምኑም ነበር፡፡ ትሩፋትን የአባቷ አለማመን ትልቅ ትምህርት ሆኗታል፡፡

******

ትሩፋት ወደ ስምንተኛ ክፍል ስትገባ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለአንድ ዓመት ነፃ አገልግሎት «ሰርቪስ» ለመስጠት የመጡበት ጊዜ ነበር። እነዚህ ወጣት ሰርቪስ መምህራን የትምህርቱን ክፍለ ጊዜ በአብዛኛው የሚሸፍኑት ዘውዳዊው የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት በመኮነንና በማውገዝ ነበር፡፡ ተግባራቸው መደበኛ ትምህርት ለማስተማር ሳይሆን የፖለቲካ ሰራ ለመስራት የመጡ ነበር የሚያስመስላቸው፡፡





«ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያስፈልጋል፡፡ ሪቮሊውሽን መካሄድ አለበት» ይላሉ ሰርቪስ መምህራኑ፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ዘውዳዊው የኃይለሥላሴ መንግሥት ወድቆ ልክ እንደ ሶቭየት ህብረትና ቻይና የሶሻሊዝም ሥርዓት መገንባት እንደ አለበት ይሰብካሉ፡፡ የማኦን፣ የሌኒንን፣ የቸጉቬራንና የሆቺሚኒን የትግል ገድል በሰፋት ያስተምራሉ፡፡ የተማሪውን ወኔ ለማነሳሳት ይጥራሉ፡፡ በኢትዮጵያ ምድር ለውጥ እንዲመጣ ተግተው ውሰጥ ውስጡን የፖለቲካ ቅስቀሳ ያደርጋሉ፡፡

ትሩፋት በተለይ እያሱ ብርሃነ የተባለውን የሒሳብ መምህሯን ሁኔታ መቼም ቢሆን አትረሳውም። ቀጠን ረዘም ባለው ቁመናው ሳይ የለበሰው እጀ ጉርድ ካኪ ሳሪያን ኮትና ሱሪው አብሮት የተሰፋ ይመስል ነበር። ሲያስተምር ቶሎ ቶሎ ራሱን ስስሚዳብስ ሀር የመሰለው ጥቁር እፍሮ ዞማ ጸጉሩ ቸክ በቸክ ይሆናል፡፡ ቆራጥነት ከሚነበበበት የቀይ ዳማ ፊቱ ላይ ፈገግታ አይጠፋም፡፡ የአፄ ኃይለሥላሴን የግፍ አገዛዝ ሲያነሳ ግን የግንባሩ የግራ ቀኝ የደም ስሮች ስንበር መስለው ይጋደማሉ፡፡ መልከ መልካምነቱን ይበልጥ የሚያጎላዉ ስልካካ አፍንጫው ሳይቀር ቲማቲም መስሎ ይቀላል፡፡ ጥቁር ቀስም የተቀባ የሚመስለው ከንፈሩ በንዴት ደርቆ ኩበት ይመስላል፡፡ ፊውዳላዊውን የኃይለሥላሴ የዘውድ መንግሥት ሲጠላ መቼም ልክ የለውም፡፡ ከሌሎቹ ሰርቪሰ መምህራን ሁሉ የሱ ላቅ--መጠቅ ይላል፡፡

አንድ ቀን ሲያስተምር ቆይቶ ድንገት አንድ ጥያቄ ጠየቀ፡፡

«ልጆች ነገ ቀኑ ሰንት ነው?» ለመልሱ የከፍሉ ተማሪ በሙሉ ማለት ይቻላል እጁን ችቦ አስመችሎ ወደ ላይ አነሳ ፡፡ መምህር እያሱ ለአንዱ ተማሪ እድሉን ሰጠ፡፡

«አርብ ታህሳስ አስራ ዘጠኝ ቀን ገብርኤል ነው» አለ ተማሪው፡፡

«ትክክል ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ሰለ ታህሳስ ገብርኤል የምታውቁት ነገር አለ?» ሲል ደግሞ ጠየቀ መምህር እያሱ፡፡

«የአመቱ ነው፡፡ ለንግሰ ታቦት ይወጣል» አለ አንድ ተማሪ፡፡

«ይህም ጥሩ መልሰ ነው፡፡ ግን ከዚህ በተለየ ሁኔታ የታህሳስ ገብርኤልን ለምን እንደምንዘከረው የሚነግረኝ ተማሪ ይኖራል?» ሲል አንደ ገና ሌላ ጥያቄ አቀረበ መምህር እያሱ። አውነት ለመናገር ጎበዝ የሒሳብ መምህር ነው። ጥሩ ሰለሚያስተምር ተማሪው ሁሉ ይወደዋል። ፖለቲካውንም ሲሰብከ አፍ ያሰከፍታል። አንዱ ተማሪ እጁን አነሳ፤ ፈቀደለት፡፡

«የዓመቱ ገብርኤል ንግስ ሰለሆነ ብዙ ሰው ቤት ጠላ ይጠመቃል፡፡ ዳቦ ይደፋል፡፡ በሰሙ ይዘከራል» አለ ተማሪው፡፡ መምህር እያሱ ባልጠበቀው መልሰ-- ፈገግ ብሎ «ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ» አለ በልቡ፡፡

«ጥሩ ነው፤ ሌላ በተለይ እኛ ተማሪዎች ልናስታውሰው የሚገባ ከልማዳዊው አከባበር በተለየ መልኩ አምና የዛሬ ዓመት በአገራችን አንድ ትልቅ ነገር ተከስቷል:: ያን አገራዊ ጉዳይ ትኩረት ሰጥተን ልንዘክረው ይገባል:: ስለዚያ ትልቅ አገራዊ ክስተት የምታውቁት ነገር ካለ?» አንደ ገና ጠየቀ መምህር አያሉ:: ፀጥታ ሆነ::

«ብሉ ከዛሬ ጀምሮ እወቁት:: ታህሳስ አስራ ዘጠኝ ቀንን ትውልድ ሁሉ በተከታታይ ለዘለዓለም ሲዘክረው የሚገባ ታሪካዊ ቀን ነው:: ታህሳስ አስራ ዘጠኝ ቀንን በሀዘንና በቁጭት እናስበዋለን:: በአንጻሩ ደግሞ በደም የተጻፈ የትግልና የለውጥ እርማ እንድናነሳ የሚያደርገን ልዩ ታሪካዊ ቀን ነው:: ይህ ትውልድ በደም የተሰጠውን አገር የማሳደግና የመለወጥ አደራ በአዲስ ተስፋ-- በአዲስ ራዕይ ቃልኪዳን የምናድስበት ልዩ ቀን ነው::» ብሎ አንደ ገና ሌላ ጥያቄ አቀረበ መምህር አያሉ::

«ጥላሁን ግዛው ሲባልስ ሰምቶ የሚያውቅ ተማሪ አለ?» ከወደጥግ አንድ ተማሪ እጁን አነሳ:: ፈገግታ የመምህሩን ፊት አለበሰው::

«የዛሬ ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ የሞተው ነው አይደል ጋሼ?» ተማሪው በመልሱ ሰለ ተጠራጠረ በጥያቄ ነበር ያቀረበው::

«ልክ ነህ:: ግን ጥላሁን የሞተው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰልፍ ያደረጉለት ሳይሆን በሌላ ጊዜ ቀን ጠብቀው ነው የገደሉት:: ምክንያቱም ጥላሁን ጠንካራ የተማሪዎች መሪ ነበር:: የኢትዮጵያን ለውጥ አጥብቆ የሚሻ ታጋይ:: ከንጉሣውያን ቤተሰብ የሆነ የልዕልት ሳራ ግዛው ወንድም ነበር:: የታገለውና የሞተው ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ሲል ነው:: ታድያ ያለ መደቡ ለጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታገል የሞተን የለውጥ ጀግናን ማሰብ አይገባም ልጆች?»

«እረ ይገባል!!» የሚለው የተማሪዎች ድምጽ አስገመገመ:: ክፍል በገባ ቁጥር ደጋግሞ የሚያነሳቸው መደብ፣ የመደብ ጭቆና፣ ፊውዳል፣ የጉልተኛው ስርአት፣ አድሀሪ፤ ጭቁን ሕዝብ፣ ለውጥ፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲ፣ እውነተኛ ነጻነት፣ እኩልነት፣ የሕዝብ አመጽ..... የመሳሰሉት ቃላት ለተማሪዎች ብዙ ግልጽ አልነበሩም:: ቀስ በቀስ ግን እየተረዷቸው ነበር::

«ጥላሁን ግዛው በጨቋኙ ፊውዳላዊው የኃይለሥላሴ የዘውድ መንግሥት በግፍ የተገደለበት ቀን ታህሳስ አስራ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሁለት ልክ በነገው አለት ነበር። ነገሩ በውል የገባውም ያልገባውም የክፍሉ ተማሪ ሁሉ በጽሞና ትረካውን ያዳምጣል::

«የኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ወራሪ ጠላት ሲመጣበት በራሱ ስንቀና ትጥቅ 'ሆ!' ብሎ ሲነሳ ያውቅበታል። አባቶቻችን በታሪካቸውና በጀግንነታቸው የምንኮራባቸውን ያህል ነፃነትን ከውጭ ወራሪ ጠላት ጋር ብቻ እንድናያይዘው አድርገውናል:: እንደምታዩት የኢትዮጵያ





ሕዝብ በሚያሳዝን ሁኔታ የራሱ አገር ገዥዎች ከባዕድ ወራሪ ጠላት በከፋ መልኩ ሲጨቁኑትና ነፃነቱን ሲገፉት እያየ 'የባሰ አታምጣ' ብሎ ተሸፋፍኖ ተኝቷል» ብሎ እጁን ከካኪ ሰሪው ኪስ ከትቶ ከፍሉ ውስጥ ከበሩ እስከ ጥቁር ሰሌዳው ድረስ ወዲያና ወዲህ ተንጎራደደ:: ድንገት ወደ ተማሪዎች ዞር ብሎ

«አራሹ ገበሬ አፈር መስሎ--- አፈር ለብሶ--- ከአፈር ጋር እየታገለ ያመረተውን እህል ለአንድ ቀን እንኳ ሥራው ላይ ሳልተገኙ የመሬት ከበርቴዎች ሲያስረክብ ግፍ እየተፈጸመበት መሆኑ አይታየውም:: እየተበደለ እንደሆነ አይገባውም:: ቢገባውም ለእግዜሩ ሰጥቶ ዝም ይሳቸዋል:: ልጆቹን እያስራበ ያመረተውን እህል በገዛ እህያው ጭኖ ለጭቃ ሹም፣ ለአጥቢያዳኛ፣ ለፈረሰኛ፣ ለነጭ ለባሽና ምስለኔ ሲገብር መብቱ እየተረገጠ መሆኑን አይገነዘብም:: ጨቋኞቹ ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው እቢ!! ብሎ የአመጽ ከንዱን እያነሳባቸውም:: ይህ ግፍ ግን አስቆጥቶ አያነሳሳም ትላላችሁ ልጆች?» ጠየቀ መምህር አያሉ::

«እረ ያነሳሳል ጋሼ!» የሚለው የተማሪዎች ድምጽ ከፍሉን ሞላው::

«ጥላሁን የሞተው «መሬት ላራሹ» ይሆን ዘንድ ነው። ምኞቱ ገበሬው ያረሰውን እህል ልጆቹን አጥግቦ እንዲመግብ---ያደለበውን ሙከት ራሱ እንዲበላ ነበር። ጥላሁን የሞተው ለሕዝብ ነፃነት ፍትህና እኩልነት ሲታገል ነው:: ሞቱን በማውገዝ የተቃወመው ግን ተማሪ ብቻ ነበር። ሕዝብ አብሮ አልጮኸም--አልተሰለፈም።» አሁንም ለትንሽ ጊዜ ዝም ብሎ በከፍሉ ውስጥ ተንጎራደደ:: አብዛኛው ተማሪ መምህር አያሉ የሚያወራው ግልጽ የሆነለትና የተረዳው አይመስልም:: ግን በፀጥታና በተመሰጦ ያዳምጣል::

ትሩፋት ደግሞ በገዛ አህዮቻቸው እህል ጭነው ያን ሁሉ መንገድ በአግራቸው ተጉዘው ለአባቷ የመሬት አበል የሚከፍሉት ገበሬዎች ታዩዋት:: አባቷ አቶ ማንያዘዋል እንዲት እረም ሳይነቅሉ--- ሳይለፉና ሳይደክሙ ሌሎች የለፉበትን መውሰዳቸው አግባብ እንዳልሆነ እያሰበች ከውስጧ ጋር ሙግት ላይ ነበረች:: የመምህር አያሉ ንግግር ከውስጧ ሙግት ገላገላት::

«የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት ቢለወጥ የተሻለ ኑሮ ይመጣ አይመስለውም። የኃይለሥላሴ መንግሥት ቢወድቅ መዓት ከሰማይ የሚወርድ ይመስለዋል:: የተሻለ ሌላ አስተዳደር ይመጣል ብሎ አያምንም:: ስለዚህ ሌላ አዲስ መንግሥት--አዲስ አስተዳደር አይመኝም። ሁላችንም በኅብረት እጅ ለእጅ ተያይዘን ለለውጥ ከተንቀሳቀስን ግን በሌላው ዓለም የመጣው እኩልነት፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲና ነፃነት ኢትዮጵያ ውስጥም የማይመጣበት ምንም ምክንያት አይኖርም::» ቃላቶቹ እየከረሩ የእሱም ስሜት እየጋለ መጣ::

«የተጨቆነ ሕዝብ  በአንድ ላይ ሆኖ 'ሆ!!' ብሎ መነሳት ይኖርበታል። ስለዚህ እናንተ ወላጆቻችሁን ማሳወቅና ማሳመን ይጠበቅባችኋል። ለምሳሌ እናንተ ከወላጆቻችሁ ጋር ሆናችሁ እዚሁ እንድትማሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊከፈትላችሁ ይገባል። ከወላጆቻችሁ ተነጥላችሁ  በሰንቅ ለምን ትንገላታላችሁ? አዲስ ዘመን ከተማ ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሰርቶላችሁ እዚሁ ብትማሩ ትጠላላችሁ?»

«ኧረ! አንጠላም----ያማ ቢሆን ታደልን ነበር--- እንዲያ ቢሆንልንማ በሰንቅ እጦት ትምህርታችን ይቋረጣል ብለን ባልሰጋን ነበር!....» የተለያዩ መልሶች ከተማሪዎቹ ተሰጡ።

«ይኸ መከረኛ ሕዝብስ መብራት አያስፈልገውም? የተጣራ የቧንቧ ውሃ አይወድለትም? ዘመናዊ የሰልክ መሰመር አይፈልግም?  መንገድ ቢሰራለትና የእግር ጉዞ ቢቀርለት ደስ አይለውም? እናንተ እነዚህ ነገሮች እንዲሟሉ አትፈልጉም? በሉ እስቲ ንገሩኝ አትፈልጉም!?»

«ኧረ እንፈልጋለን!» አሉ አሁንም  በአንድ ድምጽ።

«ይህ የበሰበሰ የፊውዳል ሰርዓት  በተባበረ የሕዝብ ክንድ እስካልተደመሰሰ ድረስ ግን መቼም ቢሆን አታገኙትም!» አለ መምህር እያሱ ቃላቶቹን ጫን እያደረገ።

ይህን ጊዜ ተማሪው ሁሉ ራሱን በቁጭት ይነቀንቃል። በተለይ  ትሩፋት በአባቷ ቤት በተግባር ያየችው ነው። እውነት ግን ይህ የሒሳብ መምህሯ እንደሚናገረው ፊውዳላዊው የኃይለሥላሴ መንግሥት ቢወድቅና ሌላ መንግሥት ቢተካ እነዚያ ባላገሮች የደከሙበትን እህል ለአባቷ ማስረከባቸው ይቀርላቸው ይሆን? እውነት የመንግሥት ለውጥ ቢመጣ የቧንቧ ውሃና መብራት የአዲሰ ዘመን ሕዝብ ያገኝ ይሆን? ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይሠራ ይሆን? የኃይለሥላሴ መንግሥት እንዲወድቅ ከልቧ ተመኘች። የመምህሯን የለውጥ ናፍቆት እሷም ተጋራች። ንግግሩን ቀጠለ መምህር እያሱ።

«ስለ እነጄኔራል መንግስቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይስ ሰምቶ የሚያውቅ አለ?» ጥግ ላይ አንድ ተማሪ እጁን አወጣ።

«መንግሥት ሊገለብጡ ሲሉ ተይዘዉ የተሰቀሉ ናቸው» አለ ተማሪው በእርግጠኝነት።

«ለምን መንግሥት ሲገለብጡ ፈለጉ?»  መምህር እያሱ መልሶ  ያንኑ ተማሪ ጠየቀው።

«እነሱ ደም ሊነግሱ ፈልገው ነዋ! ሌላማ ለምን ይሆናል ጋሼ?»  አለ ተማሪው።

«እያችሁ ልጆች ያገራችሁን ታሪክ ጠንቅቃችሁ ማወቅ ይኖርባችኋል። የራሱን አገር ትክክለኛ ታሪክ ጠንቅቆ ያላወቀ ትውልድ የውሃ ላይ ኩበት ማለት ነው።  እውነተኛ





የአገራችሁን ታሪክ ለማወቅ  ወላጆቻችሁን ጠይቁ። አዛውንቶችን አነጋግሩ። ታሪክ አዋቂ ሰዎችን አወያዩ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የታሪክ መጽሐፍትን ጠንክራችሁ አንብቡ። የራስን ታሪክ ማወቅ ያኮራል። ሳይፈሩና ሳያፍሩ በእርግጣኝነት ለሌላው ሰው ለመናገር ያረዳል። በራስ መተማመንን ያጎለብታል። ከጥራዝ ነጠቅነት ይከላከላል። ራስን ሆኖ እንደ ራስ ለመኖር የራስን ታሪክ ጠንቅቆ ማወቅ በእጅጉ ይጠቅማል» አለና ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ።

«በደንብ አዳምጡ ልጆች! ጀነራል መንግሥቱና ወንድሙ ገርማሜ ንዋይ ስልጣን ነበራቸው። በቂ ሀብትም ነበራቸው። የቸገራቸው ሰዎች አልነበሩም። የሌላው ዓለም ሥልጣኔ በአገራችን እንዲመጣ ኋላ-ቀሩ የፊውዳሊዝም የኃይለሥላሴ መንግሥት ተገርስሶ የተሻለና የሰለጠነ መንግሥት እንዲመጣ ነበር የታገሉት። የኃይለሥላሴን መንግሥት ገልብጠው እነሱ ለመንገሥ አስበው አልነበረም።» ድንገት አንድ ተማሪ እጁን አወጣ። እንዲናገር ፈቀደለት መምህር እያሱ።

«ንጉሡን አውርደው እነሱ ካልነገሡ አልጋውን ማን እንዲይዘው አስበው ነው ታዲያ ጋሼ እስተሞት የተናነቁት?» መምህር እያሱ ያልጠበቀው ጥያቄ ነበር።

«አ.....እ...እ» እያለ እንዴት ማስረዳት እንዳለበት ለጥቂት ጊዜ አብሰለሰለ።

«ምን መሰላችሁ ልጆች፤ እነሱ የታገሉት የኢትዮጵያን ሕዝብ ያለ አድልዎ  እኩል የሚያስተዳድሩ ሰዎች ስልጣን እንዲይዙ ለማድረግ ነበር። ሕዝብ ለመምራትና አገር ለማስተዳደር እውቀቱና ችሎታው ያላቸው የተማሩ ሰዎች እንዲመሩ ነበር የታገሉት። አገር ማስተዳደር በዘር ሀረግ ሳይሆን በችሎታቸውና በእውቀታቸው ሕዝብ  ወዶና ፈልጎ የመረጣቸው ሰዎች  እንዲያስተዳድሩ ነበር እስከሞት የታገሉት።»

«የሰለሞናውያን ዘር ካልሆኑ ስልጣን ዝም ብሎ ይገኛል እንዴ ጋሼ እግዜር ካልቀባው?» ሌላ ተማሪ  ጥያቄ ጨመረ። መምህር እያሱ እስካሁን የተናገረው  ግልጽ እንዳልሆነላቸው ተገነዘበ። እስከ ዛሬ ሲሰብክ የነበረው ሁሉ ይህን ያህል ፍሬ እንዳላፈራ ተረዳ። ቢሆንም ተስፋው ጨርሶ አልተሟጠጠም። ነገሩ  ግልጽ የሆነላቸው ጥቂት ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ ተጽናና። የተረዳው ነገር ቢኖር ይበልጥ ግልጽ እንዲሆንላቸው ተግቶ መስራት እንዳለበት ነበር።

«የሰለሞናውያን ዘሮች ነን እያሉ ንጉሡና ቤተሰቦቻቸው በሕዝብ ገንዘብ ሲንደላቀቁ ኖረዋል። የኢትዮጵያ ጭቁኑን ሕዝብ ደግሞ ሲረገጥ ሲበደል--ሲራብ--ሲጠማ-- ሲታረዝ-- ሲቸገር ኖሯል። እስኪ የወላጆቻችሁንና የራሳችሁን ኑሮ ዘር ብላችሁ እስተውሉት። ደልቷችሁና ተመችቷችሁ ነው የኖራችሁት?»

«እረ አይደለም ጋሼ!» በአንድ ድምጽ መለሱ።

«ታዲያ የሁላችንም በሆነች አገራችን ውስጥ ለው መሆናችን ታውቆ እንደ እነሱ እኩል መኖር የለብንም? ሌላው ቀርቶ ተበደልን--- ተጨቆን--- ተገፋን---- ከፉን ብለን እንኳ ለንወጣ በግፍ የምንደበደብ፣ የምንታሰርና የምንገደል ከሆነ እውነት ነፃነት አለን ለማለት እንችላለን? የጭቆና ቀንበር ተጭኖብን ሳይደላንና ሳይመቸን በችግር ተቆራምደን ጊዜ ሞታችንን እንድንጠብቅ የፈረደብንን መንግሥት እንዲቀጥል ትፈልጋላችሁ?»

«ኧረ አንፈልግም!»

«በጣም ጥሩ! እንዲያ ከሆነ ለጭቁኖች ጥቅም የሚያስብ--ለጭቁኖች መብት የሚቆረቆር መንግሥት ያስፈልጋል:: ጢሰኛና ባለጉልት--ገባርና ባላባት-- ጌታና ሎሌ--- ንጉሥና ባርያ ተብሎ መድሎ የማይኖርበት --ሁሉም ኢትዮጵያውያን እኩል ተጠቃሚ የሚሆንባት አገር ታስፈልገናለች:: አታስፈልገንም ልጆች?»

«ታስፈልገናለች ጋሼ!»

«ለለዚህ ለአገር ስልጣኔ የሚተጉ፤ ለሕዝብ ብልጽግና የሚጥሩ፤ ከኋላ ቀር አስተሳሰብ ተላቀዉ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ መሪዎች ያስፈልጋሉ:: ይህን ለውጥ ለማምጣት ነበር እነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የታገሉት» አለ:: አንዳንዶቹ ተማሪዎች የገባቸው መሆኑን ለማሳየት ራሳቸውን ነቀነቁ፤ አብዛኛው ተማሪ ግን አሁንም ከግርታው አልወጣም:: መምህር እያሱ ገለጻውን ቀጠለ::

«እነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የለኮሱትን የለውጥ እሳት ለማስቀጠል ሲል ነበር ጥላሁን ግዛው ደግሞ በጨካኙ የፊውዳል የኃይለሥላሴ መንግሥት የተሰዋው። ልንዘክረው ይገባል:: አርማውን አንስተን ለለውጥ ልንነሳሳ ይገባል» አለና ትከዝ ብሎ እከፍሉ መሀል ቆም አለ::

«ልጆች እኔ ነገ እላስተምርም» አለ:: የቀይ ዳማ ፊቱ በሀዘን ዳምኖ:: «እኔ ነገ አላስተምርም:: በእኔ ከፍለ ጊዜ የፈለጋችሁትን መስራት ትችላላችሁ። የጥላሁንን ሙት ዓመት እዘከራለሁ:: ከኔ ጋር ጥላሁንን ማለብና ዓርማውን ማንሳት የሚፈልግ ተማሪ ካለ ደግሞ ነገ ሀና ማርያም ቤተክርስቲያን እንገናኝ» ብሏቸው ወጥቶ ሄደ::

«የስምንተኛ ከፍል ተማሪ ሊገባው በሚችል ቋንቋ አቅርቤላቸው ይሆን» ብሎ የተናገረውን እንደ ገና በውስጡ ማሰላሰል ያዘ:: የፈለገውን ያህል የሆነለት አልመሰለውም:: ድፍረቱ ይገርማል። እንደ መለኮት የሚፈራውን ዘውዳዊውን የኃይለሥላሴ መንግሥት ትቢያ ሲያለብሰው «ጆሮ ጠቢ ይለማኛል» አይልም።

«የራስ መንገሻ ለዩም የቅርብ ዘመድ ለለሆነ ማንም አይነካኝም ብሎ ነው እንዲህ የሚዳፈረው» ይሉታል እንደ እሱ ለለርቢስ የመጡ እንዳንዶቹ መምህራን።





መምህር እያሱ በከፍል ቅስቀሳ ብቻ አላቆመም:: የቲያትርና የሥነጽሑፍ መድረከ በማዘጋጀት ወደ ኅብረተሰቡ ዘልቆ ለመግባት ያላደረገው ጥረት አልነበረም:: ትሩፋት በዚህ ሁሉ ከፍተኛ ተሳትፎ ነበራት:: መምህር እያሱ ለአዲስ ዘመን ከተማ መብራት፣ ዘመናዊ ስልክ፣ ንጹህ ውሃ፣ መንገድ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ሌሎች እድገቶችና መሻሻሎች እንደሚያስፈልጋት በቲያትርና በተማሪው ጽሑፎች ኅብረተሰቡን ለማስተማር፣ ለመቀስቀስና ለማንቃት የቻለውን ያህል ደከሟል:: ለሕዝብ እንዲቀርቡ ከተደረጉት ጽሁፎች በተለይ «መብራቱ ይብራ» የሚለውን ግጥም የብዙዎችን ቀልብ ገዛ ነበር:: ግጥሙን ያነበበችው ትሩፋት ነበረች:: መድረከ ላይ ቆማ ስታነብ አባቷ ፊት ለፊቷ ተቀምጠው የደስታ እንባ ባቆረዘዙ ዐይኖቻቸው ይመለከቷት ነበር::

መብራት ይብራ በከተማ፣

ትሻሻል ትበልጽግ አዲስ ዘመን ትልማ::

ጨለማ ይወገድ አገር ትስልጥን፤

እንሻሻል ይብቃን በጢስ መታፈን::

በኤሌክትሪክ ብርሃን ዓለም ተጥለቅልቆ፣

የእኛ ሕይወት አለ በጨለማ ታንቆ::

መብራት ያስፈልጋል በገጠር ከተማ::

ኤሌክትሪክ ይግባ አዲስ ዘመን ትልማ::

መምህር እያሱ የኃይለሥላሴን ፊውዳላዊ የዘውድ አገዛዝ ጭቆናና ብዝበዛ ከራሳቸው የአለት ኑሮ በመነሳት ተማሪዎች እንዲረዱት ለማድረግ ነፍሱ እንዴት ትቃትት እንደ ነበር ትሩፋት ምንጊዜም አትረሳውም::

******

የስምንተኛ ከፍል ትውስታዋ ብዙ ነው ትሩፋት:: በተለይ የእንቺነሽ ተንኮል፤ የፍቅሩ ጠና በሄደችበት ሁሉ ማነፍነፍ፤ ከመምህራን ደግሞ የሒሳብ መምህሯ ለውጥ ናፋቂነት በሕይወቷ ጎልተውናና ገዝፈው የሚታሰቧት የልጅነት የትምህርት ቤት ትዝታዎቿ ናቸው:: የሰምንተኛ ከፍል ብሔራዊ ፈተናን በጥሩ ውጤት ለማለፍ የነበረው ፉከከር፤ ፎርም ለመሙላትና ፎቶ ለመነሳት የነበረው መሯሯጥ መቼም አይረሳትም:: በዚህ የጥድፊያ

ወቅት ደግሞ ፍቅሩ ስር ስሯ ይከተላታል:: ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በነገር ይጎነትላታል:: የማትፈልገውን ነገር ሁሉ እየጠየቀ ያስቸግራታል::

«ትሩፋት ፎቶሽን ለማስታወሻ ትሰጭኛለሽ አይደል? አንቺ የእኔን» አለ ፎቶ የያዘ እጁን ዘርግቶ::

«የምን ፎቶ ? ምን ሊያደርግልኝ? ኧረ እኔ አልወስድም!»

«ማስታወሻ እኮ ነው! የከፍል ጓደኛሽ አይደለሁ ምናለበት?»

«አንተ ብቻ ነህ የከፍል ጓደኛዬ? ሌሎቹስ አሉ አይደል:: ከሽፈራው ጋርስ ከጥል የደረስነ በዚሁ በፎቶ የተነሳ መስሎኝ:: በል ወንድሜ እኔ የማንንም ፎቶ አልወስድም፤ የእኔንም ለማንም አልሰጥም» አለች ትሩፋት ኮስተር ብላ::

«እኔ ግን ፎቶሽን እንድትሰጭኝ እለምንሻለሁ:: የእኔንም ብትቀበይኝ ደስ ይለኛል» አላት እርግት እንዳለ። ይህ እርጋታው ሳይሆን አይቀርም በብዙዎች ዘንድ እንደ ትዕቢተኛና ኩራተኛ የሚያስቆጥረው።

«ያንተንም ፎቶ አልወስድም በቃ!» አለችው ቆጣ ብላ::

«ምን አለበት ትሩፋት? ፎቶ እኮ ማስታወሻ ነው:: ሌላ ምን ማለት መስሎሽ ነው?»

«ቢሆንም! እኔ በበኩሌ ፎቶ መለዋወጥ አልፈልግም ነው የምልህ ፍቅሩ::»

«የአንችን አልሰጥም ካልሽ እሺ ተይው አትስጭኝ። እኔ ግን እንድታስታውሽኝ ስለምፈልግ ባይሆን የኔን ተቀበይኝ» አላት:: በዐይኑም ባነጋገሩም እየተለማመጣት። እንደ አንዳንዶቹ ተማሪዎች ነጥቆ ወይ አስፈራርቶ ለመውሰድ አልሞከረም። ሽፈራው የሚባለው የከፍሏ ተማሪ ቀምቶ ቢወስድባት እንኳ እስከ መደባደብ ደርሶ ነው ያስመለሰላት።

«ምን አለበት ተቀብለሽኝ ደስ ቢለኝ። ቢከፋኝና ባዝን ምን ትጠቀሚያለሽ ትሩፋት?» አላት መከፋቱ ፊቱ ላይ እየተነበበ።

«እንዲከፋህ ወይን እንድታዝን ፈልጌ አይደለም ፍቅሩ። ወስጀው ደስ የሚልህ ከሆነ ምን ችግር ነበረው? ድንገት አባቴ ቢያገኝብኝ ግን 'የወንድ ፎቶ ምን ሊሆንሽ ያዝሽው?' ብሎ ይጣላኛል። አንተስ ብትሆን ይኸ እንደሚሆን ጠፍቶህ ነው? እንዴው ከኔ ጋር በሆነ ባልሆነው መጨቃጨቅ ያስደስትሃል ልበል እንተየ?» በዝምታ እትኩሮ ተመለከታትና ሄደ። ሌላ ጊዜ ፎቶውን ደብተሯ ውስጥ አገኘችው። ቀዳዳ አልጣለችውም፤ በእሳት





አላቃጠለችውም። ማንም ሰው እንዳያገኝባት በወረቀት ጥቅልል አድርጋ ደብተሯ ሽፋን ውስጥ በጥንቃቄ አስቀመጠችው። ለምን እንዳልቀዳደደችው ዛሬም ድረስ መልስ የላትም::

በዚያ ሒሳብ መምህሯ አማካኝነት የፖለቲካ ሀ--ሁ መሰረቱ የተጣለው ስምንተኛ ከፍል ሆና ነው:: የፍቅርን አቦጊዳ ፍቅሩ ሊያስቆጥራት ያልቆፈረው ጉድጓድ-- ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም:: ውሃ ልትቀዳ ወይ ልብስ ልታጥብ ሸኒ ወንዝ ትውረድ--ፍቅሩ አለ። ተልካም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የትም ቦታ ትሂድ ከፊት ለፊት ወይ ከኋላዋ ፍቅሩ ከየት መጣ ሳትለው ኩች ይላል። ምን መግነጢሳዊ ኃይል ወደ እሷ እንደሚስበው አታውቅም። እንደ ጥላ ይከተላታል። ኋላ--ኋላማ እሷም ሳታየው ስትውል ቅር ቅር ይላት ጀምሮ ነበር።

«ዘጠነኛ ከፍል ስትሆኚ የምትማሪው ደብረታቦር ነው አይደል?» አላት ፍቅሩ። አንድ ቀን ወደ ሸኒ ወንዝ ስትወርድ ድንገት ከኋላዋ ደርሶ:: ደነገጠች:: ኮቴውን እንኳ አልሰማችውም ነበር:: ሳታስበው ትላልቅ ዐይኖቿን ጣለችበት::

«አንቺነሽ ጓደኛሽ ግን ጎንደር ነው የምትማረው» አላት ደግሞ ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ሳትሰጠው::

«እንዴት አወቅህ? ማን ነገረህ? ቢሆንስ አንተን ምን አስጨነቀህ? በጥያቄ አጣደፈችው ግርም እያላት:: እውነትም ወደ ዘጠነኛ ከፍል ካለፈች የምትማረው ደብረታቦር ነው::

«እኔ ግን ድርጅቱ ከጎንደር ውጭ ሌላ ቦታ ሄጄ እንድማር አይፈቅድልኝም» አላት ጥያቄዎቿን ወደ ጎን ትቶ።

«ጥሩ ነዋ! የእግር መንገድ ቀረልህ:: ታድለህ! በመኪና ትንሸራሸራለህ። ደብረታቦር ብትሆን ኖሮ ግን በእግርህ መኳተን ነበረብህ። በዚያ ላይ ቄስ ጥሩ የምትባል ቀጥ ያለች ተራራ አለች አሉ። ልብ ፍስስ-- ጉልበት ብርክርክ የምታደርግ::»

«ለእኔ ግን የሚረዳኝ ባገኝ አንቺ ከምትሄጅበት ደብረታቦር ሆኜ መማሩ ይሻለኝ ነበር» አላት ቆዝም ብሎ::

«ቄስ ጥሩ ስለተባለችው ተራራ ባትሰማና ባታውቅ ይሆናል ጎንደር መማርህ ያላስደሰተህ::» ይህን ትበለው እንጂ ለምን ጎንደር ሄዶ መማር እንዳልፈለገ ውስጧ ያውቃል:: የእለት ከእለት ከትትሉ እሷንም ግራ እያጋባ ያስጨንቃት ጀምሯል::

«እኔም ደብረታቦር አንተም ጎንደር መሄድህ ጥሩ ሆነ:: መለያየታችን ለሁለታችንም ይበጃል» አለች ለእሱ ሳይሆን ለራሷ::

«አንኳን የእግር ጉዞ-- እንኳን የቁስ ጥሩ እቀበት የፈለገ ነገር ደርሶብኝ ካንቺ ጋር ደብረታቦር መማር የምችል በሆነ።።»

«ለምንድን ነው ቁስ ጥሩ የተባለችው?» ጠየቃት።። እንድታወራውና እብራው እንድትቆይ ፈልጎ እንጂ የቁስ ጥሩ ተራራን ታሪክ የማያውቅ የአካባቢው ሰው የለም።

«አየውልህ አመድበር የምትኖር እንዲት ሴትዮ ነበረች አሉ።። የቁስ ጥሩ ተራራን ከፉ ወሬ እየሰማች በጣም የምትፈራ።። ሰዎች ደሞ መፍራቷን እውቀው እግር እሳት ካለ ገደል መግባት ነው።። ተለቅሞ የሚቀበር አጥንት እንኳ አይገኝም እያሉ የበለጠ ሲያባብሱባት ኑረዋል።። እንድ ቀን ግን ደብረታቦር የሚያስኬድ የማትቀርበት ያዘመድ ለቅሶ ያጋጥማታል።።»

«እየፈራችና እየተርበተበተች ልብ ቀጥ የምታደርገውን ተራራ ልትያያዛት በጧት ትነሳለች። የቀኑ ሀሩር እንዳይበላት ማልዳ ጉዞዋን ጀመረች።። ጮራ ሳትፈነጥቅ ከተራራዋ እግር ስር ትደርሳለች። ከስሯ ቁማ ወደ ላይ እንጋጣ እየተመለከተች በፍርሀት ትርድ ጀመር አሉ» አለች ትሩፋት።። ፍቅሩ የሚያውቀውን ታሪክ ዐይኑንና አፉን ከፍቶ የሚያዳምጥ ይምሰል እንጂ ውስጧ ድረስ ዘልቆ የሚመለከተው ስታወራ የምትሆነውን ነበር።። ፍልቅልቅ የሚለውን የልጅነት ገጽታዋን፤ የዐይኖቿን ከቦታ ቦታ ከርተ--ት ማለት፤ ውብ ጥርስና ከናፍሯን፤ እንደ እርሳስ ሜፋቸው ሾል ሾል ያሉትን ደስ የሚሉትን የጧቶቿን እንቅስቃሴ--ብነፋስ የሚጋሸበውን ጥቁር እርጥብ ሀር የመሰለ ረጅም ጸጉሯን ነበር በተመስጦ የሚያስተውለው።። የውቦች ውብ ሆና ታየችው፤ ይበልጥ ወደዳት።። መቶ እጥፍ አፈቀራት።። ከእጠገቧ ሳይለይ እንዲህ እንደ እሁኑ ብቻቸውን እብረው ቆመው ለዘለዓለም እንዲኖሩ ተመኘ።። ከሷ የመለየትን ነገር ገና ሲያስበዉ ብርከ ያስይዘዋል---ያንቀጠቅጠዋል።።

«ፈርታ ወደ ቤቷ ተመለሰች እንዳትይኝ ብቻ» አለ ማዳመጡን ለማሳወቅና ታሪኩን የማያውቀው ለመምሰል እየሞከረ።።

«ምን ትመለሳለች።። ጭንቅ እንደ ያዛት እብረዋት የነበሩ ሰዎች አደፋፍረዋት ያን ደረቱን የሰጠ ዳገት ለመውጣት ተያያዘችው እንጂ አሉ። እንደ ምንም ድህ ተራራዋን ወጥታ ስትጨርስ ረባዳው ላይ ተዝለፍልፋ ወደቀች አሉ። ልቧ እየመታ-- ነጭ ላቧ እየተንጥፈጠፈ-- ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ሲል ጊዜ የምትሞት መሰሏት እብረዋት ያሉትን ሰዎች 'እባካችሁ ከመሞቴ በፊት ንሰሀዬን ልናዘዝ ቁስ ጥሩልኝ' አለች አሉ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተራራዋ መጠሪያ ቁስ ጥሩ ሆነ እልሃለሁ። እየሀ ፍቅሩ እንተ እድለኛ ነህ።። ጎንደር መማርህ በእግርህ ዳገት ከመውጣት ቁልቁለት ከመውረድ ገላገለህ» ስትለው በእሷ ጨዋታ ፈከቶ የነበረው ገጽታው ጥቁር ሲል አየችው።።





«አባከሽ ትሩፋት ይበልጥ እንዲከፋኝ አታድርጊኝ» ሲላት ድምጹ ውስጥ የእንባ ሰርቅርቅታ ነበረው።።

«ለምን ይከፋሃል ፍቅሩ? ጎንደር እኮ ከደብረታቦር የተሻለ ከተማ ነው።። የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ።። እንኳንም ጎንደር ሆነልህ።። ከደብረታቦር በብዙ ነገር ይሻልሀል» አለችው። እሷ ግን መለያየታቸው አስደስቷታል። የግንኙነታቸው አዝማሚያ አላማራትም።። ፈርታዋለች።።

«አይሻለኝም!--አይሻለኝም!» አለ በጩኸት። አስደነገጣት።። ፍቅሩ እንደዚህ ጮሆ ሲናገር ሰምታው አታውቅም።። የነብር ግልገል ዐይን በመሰሉ ትናንሽ ዐይኖቹ እንባው ማጥም ሲል አየችው።

«የተሻለ ከተማ ነው ሂድ የተባልከው ምን እንዲህ ያደርግሃል አንተየ? በእግር ከመኳተን ምን ጉዳይ አለህ? ኧረ ጡር ይልብሃል!! ታውቃለህ አይደል ስንቱ ተማሪ መማር እየፈለገ የሚረዳው አጥቶ ትምህርቱን አቋርጦ በየቤቱ እንደቀረ።። የአንተ እኮ የጥጋብ ነው።። እየረዳ የሚያስተምርህ አግኝተህ ደግሞ አገር ማማረጥህ ምን የሚሉት መፎርሸት ነው!? ተማር እንጂ ደሞ የትስ አገር ቢሆን ምን ቸገረህ? በአናትህ ፍቅሩ ግፍ ፍራ፤ እግዜርንም አታሳዝን» አለችው ከልቧ።።

ልውረድ አልውረድ እያለ የሚተናነቀው እንባው ከሷ ፊት ኮለል ብሎ ከመውረዱ በፊት ሳይለናበታት ፊቱን አዙሮ ሽመጠጠ። ለጥቂት ጊዜ ባለችበት ቁማ ፍዝዝ ብላ በዐይኗ ተከተለችው። የግንኙነታቸው ሚሥጢር አልገባት ብሎ። ልቧን ሰቅል ሆዷን ብጥብጥ እያደረገው።

«ይኽ ልጅ ምን መሆኑ ነው? ፍቅር እንዲህ ይሆን እንዴ የሚያደርገው? እኔስ ራሴስ ምን እያደረኩ ነው? በየሄድኩበት እየተከታተለ አላስቆም አላስቀምጥ ሲለኝ ጨከኜ የማልጣላውና የማልሸሸው? ምን ነክቶኝ ይሆን? ኧረ እንዴውም መቀራረባችንን ልቤ የፈቀደው ነው የሚመስለው» አለች።። ልቧን ወደ ውስጥ እየመረመረች።። «አቅሌን ልስት ምን ቀርቶኝ? በይ ሞኟ ልቤ እትኛኛይ።። አደራ አለብሽ። የአደራ ቃል ደሞ አይበላም ነውር ነው።። ማተብን የመበጠስ ያህል ከህደት ነው።። ይልቅስ ጠንከር በይና ወደ አላማሽ—ወደ ግብሽ-- ወደ እናትሽ የአደራ ቃል።» ለልቧ ነግራ እሷም ፊቷን አዙራ ገስገሰች።።

ተማሪው በፉከከርና በጉጉት ይጠብቀው የነበረው የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተሰጠ።። ሰርቪስ መምህራንም አገልግሎታቸውን ጨርሰው ሄዱ። መምህር እያሉ እንደ ቀሰቀሰውና ተማሪው ሁሉ እንደ ተመኘው የእዲስ ዘመን ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አልተሰራላትም። ውሃና መብራትም አላገኘችም። ያው እንደ ነበረች አለች። ይመሻል--ይነጋል.....

## ደብረታቦር

ምናልባት ከትልቁ ራስ አሊ ጀምሮ  የከተማ ወግ  ሳይጀመርባት አይቀርም ተብሎ ይታሰባል:: የትንሹ ራስ አሊ ዋና ከተማቸው እንደነበረች ይነገርላታል:: ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በትልቁ አስበው ከትመውባት ነበር:: የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ማዕከል ሊያደርጓት ተመኝተው ይመስላል ጋፋት ላይ የጦር መሳሪያ ፋብሪካ መሰረት የጣሉባት:: የዚህ ረጅም እድሜ ባለጸጋ እንደ መሆኗ ግን አላደገችም:: እንደ አዲስ ዘመን ሁሉ ደብረታቦርም የአውራጃው ዋና ከተማ ናት ግን ሁኔታዋ ከአዲስ ዘመን  ከተማ ቢብስ እንጂ አይሻልም:: ከአዲስ ዘመን የምትለየው የአንድ አነስተኛ አይሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ባለቤት በመሆኗ ብቻ ነው:: ካልተበላሸ  በሳምንት ወይ በአስራ አምስት ቀን ብቅ የሚል አንድ መለስተኛ አውቶብስ ነበር :: የሹፌሩ ስም ገብሬ በመሆኑ ኗሪው «ገብሬ መኪና» ብሎ ሰይሞታል:: መነሻው ጎንደር ከተማ  ሆኖ እልፎ እልፎ ጋይንትም ይደርሳል። ገብሬ መኪና ባይኖር ኖሮ በሃያኛው ክፍለ ዘመን መኪና ምን አይነት እንደሆነ የማያውቅ የደብረታቦር ኗሪ ጥቂት ባልሆነም ነበር። አገልግሎት የሚሰጠው ደግሞ  ከጥቅምት እስከ ግንቦት ወር ብቻ ነበር። ዝናብ ሳይጥልና መንገዱ ጭቃ በጭቃ ሳይሆን። ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ቀርቶ ከጎረቤት የአውራጃ ከተሞች ከአዲስ ዘመንና ከጋይንት ጋር የሚያገናኝ ዘመናዊ የመኪና መንገድ አልነበራትም እጅግ ኋላ ከቀሩት የዱሮ ከተሞች አንዷ የሆነችው ደብረታቦር:: በንጉሡ ዘመን መብራትና ውሃ መቼም ይገባላታል ተብሎ ያልታሰበላት የሃያኛው ክፍለ ዘመን ጨለማ ከተማ። ቀድማ ተቆርቁራ---ቀድማ ዘምና--ኋላ የቀረች— የተረሳች ከተማ::  ኗሪው ዘመናዊ ስልክ፣ መብራትና ውሃ ማግኘት መብቱ እንደ ሆነ የተገነዘበ አይመስልም:: የአፄ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ  ጠይቆ አያውቅም። ባለው «ተመስገን» ብሎ ይኖራል። የባሕርዛፍ ፍልጥ እንጨቱን እያነደደ::

ትሩፋት የምትኖርባቸው የአባቷ ዘመድ እማ ጥሩ መካን ናቸው። ባለቤታቸው ከሞቱ ቆይተዋል። ብዙ ጊዜ አብራቸው የኖረች ሰራተኛቸው አለች:: አባታቸውን የማያውቁ ወንድና ሴት ሁለት ልጆች አሏት:: አሳቸው ጋር ሆና ታሳድጋቸዋለች። ከባለቤታቸው በወረሷት አነስተኛ የጡረታ ገንዘብ አራት ነፍስ ያስተዳድራሉ:: ሴቶቹ ያገኟትን አብቃቅተው «አንቺ ትብሽ---አንቺ ትብሽ» ተባብለው  በፍቅር ይኖራሉ። ስኳር መጥቶ ጭቅጭቅ የሚፈጥር አባወራ የለባቸውም። ትሩፋት ተመችቷታል። ከታናናሾቿ ናፍቆትና ሐሳብ በስተቀር ደስ ብሏት ያለስጋት ትማራለች። ራሔልና ድልነሳ ኑሮ ባይመቻቸውም እዚያዉ አዲስ ዘመን ከአባታቸው ጋር ሆነው ይማራሉ።  ሦስቱ እህቶቿ  ገጠር ከእናታቸው ጋር ናቸው::  እናቷ  ከአቶ ማንያዘዋል ጋር ከተለያዩ በኋላ አንድ የገጠር ሀብታም አግብተው ደህና ኑሮ ይኖራሉ። በአካባቢው ትምህርት ቤት ባለመኖሩ እህቶቿ የመማሪያ እድሜያቸው ሊያልፍ መሆኑ ሲሰማት ታዝናለች:: ለሁሉም መፍትሄው የእሷ ጠንክራ መማር  ነው ብላ ደምድማለች:: እንደ ጥላ የሚከተላት ፍቅሩ ዛሬ የለም። ያለ ስጋት ትማራለች-- ታጠናለች።





«ትሩፋቴ እደራሽን ልጄ አንዳንድ ባለጌ ጓደኛ እንዳያሳስትሽ ተጠንቀቂ። ከእህያ ጋር የዋለች ጊደር ምን ተሰተምራ ትመጣለች' የሚባለው ተረት ውሸት እንዳይመስልሽ ልጄ! ጓደኛ ያለማል---ጓደኛ ያጠፋል:: እጉል ጓደኛ ይዞ ይሞታል:: ከደህና ልጆች ጋር ነው መግጠም»  ይሏታል እማ ጥሩ ሁልጊዜ ከትምህርት ቤት ስትመለስ::

«እሺ እማማ ጥሩ እጠናለሁ።  ግድየለዎትም አልወድቅም። አላሳፍርዎትም» ትላቸዋለች። ስጋታቸው በትምህርት መውደቁ ብቻ እንዳልሆነ ይገባታል። የሴት ልጅ እደራ ከብዷቸው ነው።

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ትምህርት ቤት የተገነባው የተንጣለለውን የእጅባር ሜዳን ተንተርሶ ነው:: ከአዲስ ዘመንና ከጋይንት  መጥተው ለሚማሩ ተማሪዎች እማካይ ነው ተብሎ በመታሰቡ ነው ደብረታቦር ላይ የተሰራው:: በወቅቱ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ቤት ነበር:: ትሩፋት ከአራዳ እስከ እጅባር ያለው ረጅም የእግር መንገድ እያሳሰባትም:: እጅ እግር የሚቆራርጠውን የደብረታቦር ውርጭ ከእቁብ አልቆጠረችውም:: የስፈሯና የክፍሏ ልጅ ከሆነችው ዝናሽ ጋር ተጠባብቀው አብረው ይሄዳሉ:: አብረው ይመለሳሉ:: ሕልሟን ለማሳካት ትምህርቷን  በትጋት ተያይዛዋለች::

******

ምንጊዜም የመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ሲደወል  ተማሪው  እመል ብሎበት  ውጭው በር ላይ መጋፋት ይወዳል::   ትሩፋትና ዝናሽ ከግፊው መሀል ወጥተው የቤታቸውን መንገድ ሲይዙ ትሩፋትን ከኋላ አንድ እጅ ጎተት አደረጋት። ዞር አለች።  በድንጋጤ ከመጮኋ በፊት አፏን በሁለት በእጆቿ አፍን አድርጋ ያዘች። ዐይኗ ፈጠጠ::

«ፍ---ፍ---ቅ---ሩ! ም —ን ንፋስ ጣለህ? ም---ን—እንዴ--ት መጣህ?» ከመደንገጧ የተነሳ መናገር አቃታት፤ ተንተባተበች::

«አንችን ብዬ የመጣሁ አይመስልሽም? እለዚያማ ደብረታቦር ድረስ  የሚያስመጣ ምን ጉዳይ ይኖረኛል ብለሽ ትሩፌ?» አለ  ድንጋጤዋ እሱንም እስደንግጦታል።

«አታደርገውም! ትምህርትህስ?» ጠየቀችው ከድንጋጤዋ ሳትወጣ:: ጓደኛዋ ዝናሽ ፈንጠር ብላ ቆማ ሁኔታቸውን እያጠናች እየጠበቀቻት ነው።

«ተረጋግቼ መማር  አልቻልኩም::»

«ምን ማለትህ ነው 'ተረጋግቼ መማር አልቻልኩም' ስትል?»

«ብቻ! እንቺ በሌለሽበት አገር ሆኜ መማር አቃታኝ፡፡ ምን ላድርግ?» አለ እሱም እንደ ደነገጠ ነው፡፡

«ይኸማ የአብድ ሥራ ነው» አለችው ዐይኗን ጠበብ አድርጋ እያየችዉና አንገቷን እየነቀነቀች፡፡

«እንጃ! አላውቅም ትሩፌ፡፡ ምናልባት እብጄ ይሆናል። ጠንቅቄ የማውቀው ነገር ቢኖር ከአንቺ ተለይቼ መኖርና መማር አለመቻሌን ብቻ ነው። ያለፈው ዓመት በስንት መከራና ስቃይ እንዳለፈልኝ የምናቀው እኔና አንድ ፈጣሪ ብቻ ነን፡፡ የማብድ ቢሆን ኖሮ ልብሴን መጣል የነበረብኝ አምና ነበር» አላት ፍርጥም ብሎ፡፡

ሲታየው ደነገጠች እንጂ እንደ አዲስ ዘመኑ የልጅነት ጊዜዋ ባለበት ትታው አልሸሸችም፤ አልተቆጣችም። ዝናሽ ትንሽ ራቅ ብላ ሁኔታቸውን እየተከታተለች ነው፡፡

«እዚህ የሚረዳህ ሰው ወይ ድርጅት አገኘህ ማለት ነው?» አሁን ተረጋግታ ነበር የጠየቀችው፡፡

«ገና ትናንት ነው የመጣሁ። ፈልጌሽ ነበር፡፡ አላገኘሁሽም። ቢሆንም ባይሆንም ብዬ ከዳይሬክተሩ ቢሮ ገብቼ የትምህርት ማስረጃዬን ሰጠኋቸው። ውጤቴን አይተው ፈገግ አሉና ምን እንደምፈልግ ጠየቁኝ» ብሎ ዝም አለ።

እውነትም ትሩፋት ትናንት ትምህርት ቤት አልነበረችም፡፡ እማ ጥሩ ታመው ምሽን ግቢ ከሚገኘው ሐኪም ቤት አብራቸው ሄዳ ነበር፡፡ ለዚህ ነው እንጂ ፍቅሩ ከሺህ ሰው መሀከል ብትሆን እንኳ ትሩፋትን ፈልጎ ያጣታል ማለት ዘበት ነው፡፡

«በረዳት ማጣት ምክንያት እስከሁን እንደ ቆየሁና አሁንም ረዳት እንደ ሌለኝ ስነግራቸው ትክዝ እንደ ማለት ብለው 'ማንኛውንም ሥራ ብንሰጥህ ሳትንቅ ትሰራለህ?' ብለው ጠየቁኝና ትኩር ብለው ተመለከቱኝ፡፡

«ታዲያ አንተ ምን መልስ ሰጠሃቸው?» ለመጨረሻው መልስ ጓጉታለች ትሩፋት፡፡ ዝናሽን ማስቆሟ ደግሞ ከብዷታል፡፡

«መልስ ከመስጠቴ መፊት ቀጠል አደረጉና 'ሥራ ሳትንቅ የምትሠራ ከሆነ በትምህርት ቤቱ ባጀት አንድ ጊዜያዊ የጸዳት ሰራተኛ ለመቅጠር አስበናል። በተለይ የተማሪዎችን ሽንት ቤት የሚያጸዳ አንድ ሰው ይፈለጋል፡፡ የወር ክፍያው ከአሰራ አምስት ብር በታች አይሆንም ብዬ እገምታለሁ።' አሉና አሁንም ፊቴን የሚያነቡ ይመስል አስተውለው ተመለከቱኝ፡፡»





«እና አንተ ምን አልካቸው?» አለች ትሩፋት አሁንም ለመልሱ ቸኩላ።

«እኔማ ምን አላቸዋለሁ? ምንስ ምርጫ ይኖረኛል? አሁን ችግሩ ሥራው አይደለም።»

«እንድትማር ከተፈቀደልህ— ለወር አስራ አምስት ብር ካገኘህ ሌላው ችግር ደሞ ምንድን ነው?» ዝናሽ አሁንም በመቁነጥነጥ እየጠበቀቻት ነው።

«ገንዘቡን ቅድሚያ ካልሰጡኝ ምን እየበላሁ እቆያለሁ? የትስ አድራለሁ? ትናንት ያደርኩት እኮ ከዘበኞች ጋር ነው። ለራሳቸው የያዟትን ምግብ ተቧጭቄ በላሁ። ነገ ከነገ ወድያስ እንዴት ላደርግ ነው? ልማር ብል እንኳ ከደብተርና ከእስክርቢቶ አቅም የለኝም» አላት። ግራ ተጋብቶ። ከአንጀቷ አዘነችለት። ከታናናሿ ሌላ ከልቧ ያዘነችው ለፍቅሩ ነው፡፡

«ደብተርና እስክርቢቶ እንኳ የእኔን እንካፈል ነበር» አለች እንደ ተጨነቀች። ቢቃ! የመርዳት አቅሟ እስከ እዚህ ድረስ ነው። ዝናሽ መቆሙ ሰልችቷታል።

«ደብተርና እስክርቢቶውንስ አንቺ ሰጭኝ፡፡ ገንዘቡን ቅድሚያ ካልሰጡኝ የማደሪያውና የቀለቡ ነገርስ እንዴት ይሆናል?»

«እንዴው አንተየ አርፈህ ጎንደርህን ብትማር አሁን ምን ነበረበት? በአንድ ልቤ ትምህርቴን እንዳልማርስት ተጨንቀህ የምታስጨንቀኝ ምን አድርጌህ ነው? እስቲ አስበው በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን እኔና አንተ ምን ማድረግ እንችል ይመስልሃል? ተማሪዎች መሆናችን ትረሳዋለህ ፍቅሩ? እንደኔ እንደኔ ምክሬን የምትቀበል ከሆነ አሁንም በጣም ሳትዘገይ ጎንደር ተመልሰህ ብትሄድ ይሻላል፡፡ እባክህ! እባክህ! ተለመነኝ ፍቅሩ እሺ በለኝና ተመልሰህ ጎንደር ኸደህ ትምህርትህን ቀጥል፡፡ ትምህርታችን ጨርሰን ሥራ ሲኖረን ሁሉም ነገር ይሆናል፡፡ በፈጠረህ አታሰጨንቀኝ!» ስትል ከልቧ ተማጸነችው።

«እሱንማ ሞክሬው ቢያቅተኝ እኮ ነው ትሩፌ -ጥዬው የመጣሁ። ሂድ ብረር-- ሂድ ብረር እያት-- እያት የሚል ነገር እየመጣ ጤና ቢነሳኝ፡፡ ተረጋግቼ መማር ብችል በርሬ እመጣ ይመስልሻል? ላብድ ደረስኩ እኮ! ራሴ ሲፈነዳ--- ልቤ ጧ ትርትር! ልትል ሆነ! ምን ላድርግ? ልበድ ትሩፌ ---ልበድ ---!?»

«እንዴው እኔስ ለአንተ ስል የት ልግባ? ይህንን ትምህርት የት ሄጄ ልጨርስ?» አለች ትሩፋት ምርር ብላ፡፡

«ሁሉም ነገር ከምችለው በላይ ሆኖ አስጨነቀኝ እኮ! እሺ እኔስ ምን ልሁን? እንዴው በእናትሽ ትሩፌ! ምናለ የውስጤ ጭንቀት ቢገባሽ! ስቃዬ ቢታይሽ! ፈልጌና ወድጄ እንዲህ የምሆን ይመስልሻል?»

«እዚህ በመምጣትህስ ቢሆን ምን የምታገኘው ነገር ይኖራል ፍቅሩ? ትምህርትህ ከመቋረጡ በስተቀር ምን የሚፈጠር ነገር ይኖራል ብለህ አስበህ ነው? መቼም ተጋብተን ጎጆ አንመሰርት ነገር፡፡»

«እንዴው ጧትና ማታ ስንገናኝ ሂድ--ሂድ ---ብረር-— ብረር የሚለኝ አባዜ ይለቀኝ እንደሆነ፡፡ አጠገብሽ ሆኜ ሁልጊዜ ሳይሽ ጭንቀቴ --ጥበቴ ይቀልልኝ እንደ ሆነ ብዬ እንጂ ሌላማ ምን አገኛለሁ ትሩፌ?»

«የእኔንና የአንተ ነገር መጨረሻው ምን እንደሚሆን እሱ መድሃኒአለም ይወቀው እንጂ እኔስ ግራ ገብቶኛል። መፍትሄ ለሌለው ነገር ይልቁንስ እላፊ አግዳሚው እስኪታዘብ ድረስ ብዙ ቆምን። ጓደኛዬንም አስጠበቅኳት። በል ደህና እደር» ብላው በቆመበት ትታው ሄደች። ፍቅሩ ግራ ገብቶት ፍዝዝ እንዳለ ባለበት ቆሞ ቀረ፡፡

«ብዙ ቆየሽ እኮ ትሩፋት። ልጁ ምንሽ ቢሆን ነው እራቴ! ይህን ያህል ሰዓት ያቆምሽኝ? ሙች ትሩፌ እማማ ጥሩ ይቆጡኛል ብዬ ነው እንጂ ጥየሽ ልሄድ ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር፡፡ መቆም ስልችት ብሎኝ» አለች ዝናሽ ቅሬታዋን ሳትደብቅ፡፡

«ይቅርታ ዝንዬ ከጎንደር የመጣ ዘመዴ ነው» አለች። «ዘመዴ» ስትል እንዳች ቅሬታ እየተሰማት።

«እ--! ዘመድሽ ከሆነ ዛድያ ከምትኖሪበት ቤት አይመጣም ነበር? የሚያልፍ የሚያገድመው ሰው ሁሉ 'ጉድ' እስኪል ድረስ መንገድ ዳር ከሚያቆምሽ?» አለች በጥርጣሬ ዓይን እያየቻት።

«እማማ ጥሩ ለእኔ እንጂ ለእሱ አይዘመዱትም» አለች ትሩፋት ሌላ ጥያቄ እንዳትጨምርባት በልቧ እየጸለየች።

«እንዴው ለመሆኑ ለምን ጉዳይ መጥቶ ነው እንዲህ መንገድ ላይ አቁሞ በወሬ የያዘሽ?»

«አይ ዝናሽ ወሬ መስሎሽ ነው? የከፋ ችግር ገጥሞት ነው እባክሽ፡፡ ጎበዝ ተማሪ ነበር። ምን ያደርጋል አረዳት አጥቶ የኸውልሽ ከቦታ ቦታ ይንከራተታል። ዳይሬክተራችን የትምህርት ቤቱን ሽንት ቤት እያጸዳ እንዲማር ፈቅደውለት እሱን እያጫወተኝ ሳይታወቀኝ ብዙ አቆምኩሽ ይቅርታ ዝኑ»

«በደብረታቡሩ አየሱስ! እውነትም እንዴት ያሳዝናል እባክሽ! ይህን የመሰለ ልጅ ማንም ተማሪ ያጨማለቀውን ሽንት ቤት ሊጠርግ! ሲያሳዝን! ደም እኮ የቸገረዉ አይመስልም። ምኑን ቅባት አትፍ ትፍ ቢልበት ነው እንቸየ እንዲህ ወዙ በጭልፋ የሚጨለፍ የሚመስለው? የፈገግታው--- አሣ የመሰለ ጥይምናው የ......»ብላ ልትቀጥል ስትል





«ኧረ በፈጠረሽ ዝናሽ ዝም በይ! በቁም ነገር ስለችግሩ ከብደት— የሚልስው የሚቀምሰው ስለማጣቱ--- ማደሪያ መጠጊያ ስለመቸገሩ እያወራሁልሽ 'ወዙ---- ፈገግታው--- ምናምኑ' እያልሽ ትተርኪያለሽ። 'ያልተነካ ግልግል ያውቃል' እሉ አማማ ብርቄ» አለች ትሩፋት ተገርማ፡፡

«ማደርያም የለው? እንዲህ እንደ እናንተ የሚያስጠጋ ዘመድ በድፍን ደብረታቦር ውስጥ አላገኘም? የእውነት እንዴት ያሳዝናል!» ትሩፋትና ዝናሽ ስለ ፍቅሩ የጀመሩትን ወሬ በቅጡ ሳይቋጩት ሰፈር ደረሱና ተሰነባብተው ተለያዩ።

ጠዋት ከትምህርት ቤቱ በር ላይ እንደሚጠብቃት እርግጠኛ ነበረች ትሩፋት፡፡ ወደ ግቢው ለሚገቡ ተማሪዎች ሁሉ ምንም ትኩረት ሳይሰጥ ቆይቶ እሷን ሲያይ ሰውነቱ በእንዳች ኃይል በቁጥጥር ስር የዋለ መሰለው፡፡ ፍዝዝ ብሎ ተመለከታት፡፡ በደብረታቦር የጠዋት ውርጭ ተቆፍኖ የነበረው አካላቱ ከውስጥ ሲፍታታና ሙቀት ሲረጭ ተሰማው፡፡ አጠገቡ ስትደርስ ፈገግ ብሎ

«ደህና አደርሽ ትሩፋት?» አላት እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ።

«እግዚአብሄር ይመስገን። እንደ ምን አደርክ ፍቅሩ? አለች ለሰላምታ የዘረጋውን እጁን እየጨበጠች። እጇን እጁ ውስጥ ይዞ ቆም አለ። ተጨነቀች። ትናንት ለረጅም ጊዜ ቆመው ታይተዋል። ዛሬ ደግሞ ሲደገም ምን ይባላል? የተማሪ መተራረቢያ እንደ መሆን የሚያስጠላት ነገር የለም። የመንጠቅ ያህል እጇን ስባ አስለቀቀችው።

«ገንዘቡን ቅድሚያ የሚሰጡህ ይመስልሃል?» ዝናሽ ዛሬም ፈቀቅ ብላ ሁኔታቸውን ትከታተላለች፡፡

«እንግዲህ ዛሬ ነው 'ወስነን እንነግርሃለን' ያሉኝ። እንዴው ግን ትሩፌ ያንቺ ዘመዶች የማደርያ ቦታ አያገኙልኝም?»

«ኧ--ረ! እንኳን የማያውቁህን ቢያውቁህም ቤታቸው ጠባብ ናት። እኔም የማልገፋ ዘመድ ሆኜባቸው ነው እንጂ ሰው የሚያስጨምር ቤት ኖሯቸው አይደለም» እለችው እንዲህ በማሰቡ እየገረማት። «ይኸ ልጅ እውነትም ተጃጅሏል» አለች ለራሷ።

ፍቅሩ ተሰፋ የጣለበት የትምህርት ቤቱ ከፍያ ቀድሞ አልተሰጠውም። የዲሬክተሩ መልካም ፈቃድ ብቻ ቶሎ ተፈጻሚ ሊያደርግለት አልቻለም። የነዚያን ምስኪን ዘበኞች ምሳና እራት እየተካፈሉ መብላት ደግሞ ሊቋቋመው የማይችለው ሰቀቀን ለቀቀበት። እነሱ አንኳን ቤት ያፈራውን ተካፍሎ መብላቱ ምንም አልመሰላቸውም ነበር። እንዲያውም በረዳት ማጣት ምክንያት ገና በለጋነት እድሜው ለዚህ ሁሉ ችግር በመዳረጉ ያዝኑለታል። በቅርብ ሆኖ ትሩፋትን ጧት ማታ በማየቱ ነብሱ ብትረካም የስጋ ፍላጎቱን የሚያሟላ

ምንም ነገር አልተፈጠረለትም። ከሁለት ሳምንት በኋላ ይህንን ፈታኝ ሁኔታ የሚቋቋምበት አቅም አጣ።

ትሩፋት ለትምህርቷ ትኩረት ሰጥታ እየተከታተለች ነው። የእናቷ የአደራ ቃል ጉልበት ሆኗታል። አንዳንዴም ቢሆን ፍቅሩን ማሰቧ አልቀረም። በእሷ አለችሎት «እዚህ ሄድኩ» ሳይላት ከደብረታቦር ምድር መሰወሩ ይገርማታል።

«ኧረ የደብረታቦሩ እየሱስ ልቦና በሰጠው። በኔ ላይ ያለው ከንቱ የማይጠቅም አባዜ ከላዩ ላይ ብን ብሎ በጠፋለትና በለቀቀው። ምነው ልቡ ጠንክሮ በቆረጠለትና ከአንዱ ቦታ ተረጋግቶ መማር በቻለ» መልካሙን ሁሉ ተመኘችለት ለፍቅሩ። በግማሽ ዓመቱ የአሰረኛ ከፍል ትምህርት የከፍሏ ሦሰተኛ ደረጃ ተማሪ ሆነች -- ።

******

«ትሩፋት ከዳይሬከተሩ ቢሮ ትፈለጊያለሽ» አለቻት ቀጠን ረዘም ያለችው ጠይሟ ተላላኪ። የለበሰችው አረንጓዴ ቴትሮን ቀሚስ ከኋላዋ ጠርዙ ተጨማትሯል። የመልኩ ቀለም የማያስታውቀው አዳፋ የውሰጥ ልብሷ በትንሹ ይታያል። ጸጉሯን ያሰረችበት አሮጌ ጥቁር ሻሽ እሷንም ያለ እድሜዋ አስረጅቷታል። አረፍት ነው። ተማሪው ሁሉ በቡድን በቡድን ሆኖ ስለወቅቱ የአገሪቱ ሁኔታ ይወያያል። ሞቅ ያለ ትኩሰ የፖለቲካ ወሬ ይዟል። ከርከሩና ውይይቱ በተሟሟቀበት በዚህ ጊዜ ነበር መልዕከቱ የደረሳት። ተላላኪዋን ተከትላ ቢሮ እስከትደርሰ «ሳላውቀው ምን ጥፋት ሰርቼ ይሆን?» እያለች እየተጨነቀች ነበር። **ሁሉም ተማሪ** ቢሮ ሲጠራ አይወድም። የሚጠራው በጥፋት እንጂ በበጎ ነገር **አይመሰላውም**። አብዛኛውን ጊዜ የሚሆነው ደግሞ እንደዚያ ነው። ከርእሰ መምህሩ ቢሮ ሰትገባ አቀርቅረው ይጽፉሉ። መግባቷን የሰሙ አይመስሉም። ድንገት ቀና ሲሉ የብርጭቆ ቂጥ በመሰለው መነጽራቸው ውስጥ ነጩ የበዛበት የሚመሰለው ዐይናቸው ያፈጠጠባት መሰላት። ፍርሃቷ ጨመረ።

«ትሩፋት መጣሽ? ቁጭ በይ» አሏት። ወንበር እያመለከቷት። ልቧ መለሰ አለች። በጥፋት እልተጠራችም። አቀራረባቸው ያሰታውቃል። ቅርቧ ያለውን ወንበር ሰባ ተቀመጠች።

«የመምህራን ኮርሰ ለመውሰድ ከተመዘገቡት ተማሪዎች ዝርዝር ውሰጥ ስምሽን አገኘሁት። ትምህርት ቤታችን ለከፍተኛ ትምህርት ይበቃሉ ከሚላቸው ተማሪዎች ውሰጥ አንዷ አንቺ ነሽ። ለምን የአስራ ሁለተኛ ከፍል መልቀቂያ ፈተናን አትወሰጅም? ይህንን ልጠይቅሽ ነው ያስጠራሁሽ» አሏት።

«ቶሎ ሥራ ይዤ ቤተሰቦቼን መርዳት ፈልጌ ነው» አለች ባጭሩ አንገቷን አንደ ደፋች።





«ትሩፋት! የአሰራ ሁለተኛ ከፍል መልቀቂያ ፈተናውን ብትወስጂ እርግጠኛ ነኝ ለከፍተኛ ትምህርት ትበቂያለሽ። ይህንን እድል ብትጠቀሚበት የተሻለ ሁኔታ ታገኛለሽ። አሁን ልትሄጅበት ካሰብሽው የመምህራን ኮርሰ የተሻለ እድል ይገጥምሻል። ሰለሆነም የበለጠ ራስሽን ጠቅመሽ ቤተሰቦችሽንም መርዳት ትችያለሽ።» ብለው አስተውለው ተመለከቷት።

«ጥሩ ችሎታ አለሽ። ማን ያውቃል ለአገርና ለወገን የሚያኮራ ሥራ መስራት ትችይ ይሆናል። በዚያ ላይ ልጅ ነሽ። የሁለት አመት ዕድሜ መጨመር አቅቶሽ አሁን በምትወስጅው እርምጃ በኋላ እንዳትፀፀች። በልጅነት ዐይን አይተሽው እንዳይሆን። አሰቲ ጊዜ ወስደሽ በደንብ አሰቢበት። ከቤተሰብ ጋርም በርጋታ ተመካከሪበት። ለዚሁ ነው ያስጠራሁሽ። መሄድ ትችያለሽ አሏት። እጅ ነስታ ወጣች።

«የደላቸው። ማትሪክ ወሰጄ ዩኒቨርሲቲ ብገባ ጠልቼ ይመስላቸዋል? ደሞ ከቤተሰብ ጋር ተመካከሪ ብሎ ነገር። ማንን ሸሽት ሆነና ነው ትምህርቴን ባጭር የማሰቀረው?» ብላ ከኮነነቻቸው በኋላ መልሳ ደግሞ «ብቻ እግዚአብሔር ይሰጣቸው። ለእኔ አስበውና ትልቅ ደረጃ እንድደርሰ ተመኝተው አይደል ቢሮ ድረስ አሰጠርተው የመከሩኝ። ግን አልችልም--! አልች---ልም! ከዚያ የሲአል ኑሮ ታናናሾቼን መገላገል ይኖርብኛል። ፈተናውን ልለፍ እንጂ ከዚህ ኮርሰ አልቀርም። ወዲያውም እኮ ትምህርትና ዳገት እያረፉ ነው ተብሏል። ታናናሾቼን አስተምሬ እነሱ ሰራ ሲይዙ እየረዱኝ ዩኒቨርሲቲ እገባለሁ። ተራ በተራ እየተረዳዳን እንማማራለን» እንደ እብድ ብቻዋን እያወራች ከፍሏ ደረሰች።

በዚህ ዓመት ሁሉም ተማሪ ከፖለቲካ ውጭ ሌላ ወሬ የለውም። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚወስዷቸው እርምጃዎች ሁሉ በንፋስ ፍጥነት ደብረታቦር ይደርሳሉ። ተማሪው ትምህርት በማቋረጥና ባለማቋረጥ መካከል ሲዋልል የጥላሁን ግዛው የሙት ዓመት መታሰቢያ ቀን ደረሰ። በተማሪና በፖሊስ መካከል ግብግብ ከሚፈጠርባቸው ጉዳዮች ዋነኛው ይኸው የጥላሁን የሙት ዓመት መታሰቢያ ቀን ሆኗል። መድሐኒያለም ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ለመግባት ተማሪዎች በጧት ሲሰባሰቡ ፀሐይ ገና ከአድማሰ ጥግ እንደ ተሸንጠች ነበር። ሆኖም ፖሊስ ቀድሞ ቦታዉን ተቆጣጥሮት ያገኙታል። ረብሻው የሚፈጠረው ቤተከርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ውስጥ ተማሪዎች «እንገባለን» ሲሉ ፖሊስ ደግሞ «አትገቡም» በሚል ውዝግብ ነው። ተማሪዎች በኃይል ለመግባት ሲሞከሩ ፖሊስ በቆመጥ እያሰፋራራ ለመበተን ይሞክራል። ተማሪ ድንጋይ መወርወር ይጀምራል። ፖሊስ ወደ ላይ እየተኮሰ ያገኘውን ተማሪ ሁሉ በቆመጥ ይደበድባል። እናቶች ነጠላቸውን ጥለው እንደ እብድ እየጮሁ አካባቢውን ቀውጢ ያደርጉታል። ታህሳስ ገብራኤል የምጥ ቀን ሁና ትውላለች። በዱላ የቆሰለውም ቆስሎ ያመሰጠውም አምልጦ በሚቀጥለው ቀን ትምህርት ይጀመራል። የዘንድሮው ግን ለየት ብሏል። ከጥላሁን ግዛው ሙት ዓመት ዝከረ ከብር ግርግር በኋላም ትምህርት በወጉ አልተጀመረም። ተማሪው እንዲሁ ውስጥ ውስጡን እንዳጉረመረመ አንደኛው ወሰነ

ትምህርት እለቀ:: ሁለተኛው ሴሚስተር ሲጀመር ሲል ግን ለየለት:: የተማሪዉ እንቅስቃሴ ቅርጽ ያዘና ሴሎች ጥያቄዎችንም አካቶ ተነሳ።

የመኪና መንገድ ይሰራ!!

መብራት፤ ንጹህ ውሃና ዘመናዊ ስልክ ለደብረታቦር ሕዝብ!!

ትክክለኛ ፍትህ ለጭቁኑ ሕዝብ!!

የታሰሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ይፈቱ!!

የመሬት ለአራሹ ጥያቄ የእኛም ጥያቄ ነው!!

«እነዚህ ያነሳናቸው ጥያቄዎች ካልተመለሱ ትምህርት እንጀምርም» አለ ተማሪው። ከአንደኛው ወሰነ ትምህርት በኋላ ትምህርት ቤት የሚሄደው ለመሰባሰብና ለመገናኘት እንጂ ለመማር አልነበረም። ትምህርት ለመጀመር ዳር ዳር የሚሉ ተማሪዎች «ባንዳ» የሚል ቅጥያ ተለጠፈባቸው:: ከዚህ በከፋም ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዴት ገብተው-- እንዴት ወጥተው? የድንጋይ ውርጅብኝ ይወርድባቸዋል። ተምረው ሳይማሩ ትርፉ «ባንዳ» የሚል ክፉ ስም መለጠፍ ብቻ ሆነ::

ትሩፋት እላማዋን ለማሳካት ትምህርት ዋና መሰላሏ እንደሆነ ገብቷታል። ግን ደግሞ ለመማር እንደ ሞከሩት ተማሪዎች «ባንዳ» መባል ፈጽሞ አትፈልግም። እንደ አባቷ የምታያቸው አቶ መሳይ በጊዜው የሰፈሩ ሰው ሁሉ «ባንዳ » እያለ ቡና ላይ እንዴት ያብጠለጥላቸው እንደ ነበር መቼም አትረሳውም። ተማሪው ይዞት የተነሳውንም ጥያቄ ታምንበታለች። ደብረታቦር የመኪና መንገድ ቢሰራለት ኖሮ በግሯ አትኳትንም ነበር። ቁስ ጥሩ ተራራ ነፍስና ስጋዋ የተለያዩ አስኪመስላት ድረስ አትፈታተናትም ነበር። መብራት ቢኖር ኖሮ በኩራዝ ጢስ ባልታፈነችም ነበር። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችስ ቢሆኑ? «አገር ትሻሻል-- ትደግ-- ትበልጽግ፡» ብለው ለአገር ለወገን በቆሙ ክፉ ሐሳብ እንዳሰቡ ሁሉ ለምን ይታሰራሉ? መሬትም ላረሳትና ለለፋባት መሆን ይገባታል። የተማሪው ጥያቄ ጥያቄዋ ነው።

ለውጡ እሚመጣው እንዴት ነው? በዚህ በተማሪ ግርግር ብቻ? ትምህርት በማቋርጥ ብቻ? መልስ ያላገኘችላቸው የማይገቧት ጥያቄዎች ናቸው። ለውጥ በተማሪ ግርግር ብቻ እንደማይመጣ ያ የስምንተኛ ክፍል የሒሳብ መምህሯ አስረግጦ ተናግሯል። የሚነበቡ ቀስቃሽ ግጥሞች ደግሞ ይማርኳታል:: በተለይ አንድ ታደሰ የሚባል ተማሪ የሚያቀርባቸውን መነባንቦች ትወድለታለች:: ግጥሙን ሲያቀርብ የሚታይበት ትንታግ ስሜቱ ወኔዋን ያነሳሳዋል:: ይበልጥ የወደደችለት ደግሞ «ሰላም እትለምኑ» የምትለዋን ግጥሙን ነበር::





ሰላም አትለምኑ ለመረረች ሕይወት፣

ተነቅሎ ሳይጠፉ የአንጀራው ጦርነት::

ተሰባብሮ ሳይወድቅ የጭቆና ቀንበር፣

ደፍርሶ ካልጠራ ሰላም አይፈጠር!!

ላለየለት ሕይወት ቀኑ ወይ ማዕልቱ፣

ቢኖርስ ባይኖርስ ሰላም ምናባቱ!! ይል ነበር::በዚያ እለገምጋሚ ድምጹ!!

ትሩፋት በየጊዜው የሚነበቡ መጣጥፎች እየሳቧት--- እየሳቧት መጡ። አንድ ቀን እንደ ተለመደው ተማሪው ክክፍል ሳይገባ ኳስ ሜዳው ውስጥ ተሰባሰበ። ውይይቱ ተጧጧፈ:: መፈክሮች ተሰሙ:: የተለያዩ ጽሁፎችና ግጥሞች ቀረቡ:: በዚያን ቀን ከቀረቡ ግጥሞች አንዱ «መቃብሩ ይፍረስ» በሚል ርዕስ የትሩፋት ነበር::

ምዕተ ዓመት ቢቆጠር ስጋው ቢበሰብስ፣

መንፈሱ ይጠራ-- መንፈሳችን ይዳስ፣

ያገር ፍቅሩ ወኔው በጭራ ይዳረስ፣

ይነሳ ቴዎድሮስ መቃብሩ ይፍረስ::

ታጠቅ የለበሰው ያገር ፍቅር ሸማ፣

መቅደላ አፋፉ ላይ ይጮሃል! ይጣራል! ለኛ ሊሆን እርማ!

«ተነሱ! ታገሉ! ዳር ደንበሯ ይለፋ-- ትበልጽግ ትሻሻል ኢትዮጵያ አማማ»

እያለ ተጣራ! እለተጋባ ድምጹ ትውልድ እንዲሰማ::...

ግጥሟን እንብባ አልጨረሰችም:: ግቢው ድንገት ብሔራዊ ጦር በሚባሉ ልዩ ወታደሮች ተጥለቀለቀ። ውሃ ሰማያዊ ዩኒፎርምና ቀይ መለዮ አድርገዋል:: ሁሉም ውሃ የማያስኝ አጭር ቆመጥ ይዘዋል:: እነዚህ ብሔራዊ ጦሮች ምንም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ፤ ወታደራዊ ስልጠና እንኳ በአግባቡ ያልወሰዱ ናቸው:: እንደ ሮቦት የታዘዙትን ብቻ እንዲፈጽሙ ሆን ተብሎ ለዚሁ የአመጽ እንቅስቃሴን ለማፈን የተዘጋጁ የንጉሡ ልዩ ምልምሎች ናቸው:: ተማሪውን ሁሉ እያሳደዱ ያለርህራሄ በያዙት ቆመጥ ያቀምሱት

ጀመር። በዱላ ተቀጥቅጠው ከተያዙት ተማሪዎች ውስጥ አንዷ ትሩፋት ነበረች። ታፍሰው ፖሊስ ጣቢያ ታሰሩ፡፡ ጥቂት ተማሪዎች ማታውኑ ተፈተው አደሩ። ትሩፋት የተያዘችው ከነግጥም ወረቀቷ ነበር። ከሌሎቹ እስረኞች በተለየ ጉዳይዋ ከረር እንዲል አደረገባት። በተያዘባት ግጥም ምክንያት እንደ ሌላው ተማሪ በማስጠንቀቂያ ብቻ አልታለፈችም፡፡ ጠንካራ ዋስ ጠርታ ነበር የተፈታችው። በብሔራዊ ወታደር ቆመጥ የተቀጠቀጠው እጇ አብጧል፡፡ ጭንቅላቷ ተፈንክቷል-- ሆኖም ከእስር በመለቀቋም ደስ ብሏታል፡፡

ውሎ አድሮ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከእስር ተለቀቁ ተባለ። ትምህርት ጀምረዋል የሚል ወሬ ተናፈሰ፡፡ የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ሳይቀሩ ወደ ትምህርት ገበታቸው እየተመለሱ እንደ ሆነ ተሰማ፡፡ ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ሊያልቅ ጥቂት ቀኖች ቢቀሩትም ተማሪው ሁሉ ገብቶ መማር ጀመረ። የዳግማዊ አጼ ቶዎድሮስ ትምህርት ቤት የወትሮ መልኳን ያዘች፡፡ መረጋጋት በግቢዋ ሰፈነ፡፡ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ለመግባት የቃልና የጹሑፍ ፈተና ወስደው ካለፉ ተማሪዎች ውስጥ ደግሞ አንዷ ትሩፋት ሆነች፡፡ ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ግርግር የበዛበት ቢሆንም በዚህ መልኩ የዓመቱ ትምህርት ተጠቃሎ ትምህርት ቤት ተዘጋ፡፡ ተማሪው ሁሉ ወደ የቤተሰቡ ተበታተነ፡፡

******

«በእሰቸኳይ ነይ ትልሻለች ፀሐይ» አለች ተልካ የመጣችው ትንሽ ልጅ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል። ሰማዩን በነጩ ይዞ «ችፍ..ችፍ» የሚለው የሐምሌ ዝናብ አበስብሿታል። ባዶ እግሯ በጭቃ ላቁጧል። አዘነችላት ትሩፋት።

«ምን የሚያጣድፍ ነገር መጣ በዚህ በዝናብና በጭቃ የላከችሽ?»

«'ቶሎ ነይ' በያት ብቻ ነው ያለችኝ» አለች አሁንም ከላይ ከላይ እየተነፈሰች። በተናገረች ቁጥር እንደ ሲጋራ ጭስ ትንፋሿ ትጉለል-- ትጉለል ይላል፡፡

«አባቴ 'ራሴን አመመኝ' ብሎ አቤት ተኝቷል። ድንገት ተሽሎት ከወጣ እመጣለሁ ያለዚያ ግን አልችልም ብላለች በያት» ልጅቱ መልዕክቱን ይዛ እንደ ወፍ በረረች። የትሩፋትና የፀሐይ ቤት ብዙ የተራራቀ አይደለም። ለነገሩ የአዲስ ዘመን ሰፈሮች ሁሉ ያን ያክል የተጋነነ ርቀት የላቸውም፡፡ ሁሉም እዛው ጎድጓዳ ገበታ ውስጥ ተከማችተዋል፡፡ ልጅቱ ምንም ያህል ጊዜ ሳትቆይ አሁንም እየሮጠች ተመልሳ መጣች። ከትሩፋት አጠገብ ስትደርስ ጫን ጫን እየተነፈሰች፡፡

«'ሰ...ሰ..ብ..ብ.ር..ቱ ኡህ ! ጉ...ዳ..ይ ነ...ነው. የ..ም...ፈ....ኡህ! የ..ም. ፈ....ልግሽ ባ..ሰቸ...ኳ..ይ ነ..ነይ በጣም ኡህ! እ..ፈ.ልግ.. ኡህ! እፈልግሻለሁ.ብ..ላሻ ኡህ! ብላሻለች»





አለች ልጅቱ እየሳለች፡፡ እያቃሰተች፡፡ የሞት ሞቷን ነበር ቃላቶቹን በሲቃ ያወጣቻቸው፡፡ ደክሟም ብሏታል፡፡ ደግሞ ለመልሱ መቸኮሏ። ዐይኗን ትሩፋት ላይ እያቁለጨለጨች ተቁነጠነጠች።

«እሺ. መጣሁ በያት፡፡» አለች ትሩፋት ድጋሚ እንዳትልካት እየተመኘች፡፡ በዚህ የሐምሌ ዝናባማ ጭፍና ቀን ፀሐይ ሰምን ይህን ያህል ባጣዳፊ እንዳስፈለገቻት ግራ ገባት፡፡

«ታማ መሆን አለበት፡፡ ወይ ደግሞ አንድ ከባድ ጉዳይ ገጥሟታል፡፡ እንዲያ ባይሆን ኖሮ በሄኗ እያየ ሕጻን ልጅ በዚህ ዝናብና ብርድ ቀን ሁለት ጊዜ አትልከም ነበር» አለች ለራሷ፡፡ ለአባቷ ምን መላ ነግራቸው እንደምትሄድ ማሰብ ጀመረች፡፡ እንኳን በቅዳሜው በእዘቦት ቀን እንኳ እግራቸውን ቢያሰሯቸው አቤት የማይቀመጡት ሰውዬ ከነጋ ከቤት አልወጡም። ትሩፋት ደግሞ ጥሎባት መላ መመሰል አይሆንላትም።

«ባበዩ ፀሐይ ፈልጋኝ ነበር» ብላ ፊት ለፊታቸው ቆመች። መጠጥ ባደፈረሰው ጉሽርጥ በሄናቸው ገርመም አደረጓት።ፊታቸው በመጠጥ ባይበላልዝና ዐይኖቻቸው ደፍርሰው ጉሽርጥ ባይመስሉ ኖሮ ዐይን-ስውር በዳበሳ አይሰያቸውም እስኪባልላቸው- ድረስ አባትና ልጅ ይመሳሰላሉ። ያሁኑን እያድርገውና የአዲስ ዘመን ሰው በቅላታቸው «ሌላው ሙሴፋና» እያለ ይጠራቸው ነበር፡፡ ከግሪካዊው ፈረንጅ ሙሴፋና ጋር እያመሳሰለ። ምን ያደርጋል-- በመጠጥ የበላለዘ ፊትና የደፈረሰ ጉሽርጥ ዐይን ይዘው ቀርተዋል። ዛሬ ዛሬ ራሳቸውን የሚያዩት በትሩፋት ውስጥ ነው። ስዚህም ይመስላል የእሷ ነገር አያሆንላቸውም። «ትሩፋት ትሙት» ካሉ የፈሰሰ ውሃ አያቃኑም፡፡

«አሁን ማ ይሙት ሁልጊዜ እኔን እያስፈቅድሽ የምትሄጅ አትመስይም!» አሏት ዐይናቸውን ከወዲያ ወዲህ እያንከራተቱ። እሳቸውም ቢሆን ሰው ወግተው ማየት አይውዱም። ይህን ሰው ወግቶ አለማየት ትሩፋት ከአባቷ የወረሰችው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ዝም ብላ ቆመች፡፡

«ምን አቆመሽ?» አሏት ቁጣ ባልሆነ ቁጣ፡፡ ተፈቀደላት ማለት ነው። እየተጣደፈች ወጥታ ሄደች። መንገዱን ሁሉ እንዲህ ሱሪ ባንገት እስኪሆን ድረስ የተፈለገችበት ጉዳይ ምን ሲሆን እንደሚችል እያሰላሰለች ነበር። ከነፀሐይ ቤት ስትገባ ግን ያየችውን ማመን አቃታት። ሁሌ እንደምታደርገው የተከፈተ አፏን በእጇ አፍን አድርጋ ያዘች ። ዐይኗ ፈጠጠ፡፡ ስትገረም፣ ስትደነግጥ ወይ ስትናደድ እንዲሁ ናት ትላልቅ ዐይኖቿ ከአፎታቸው ሡጥተው ሊወድቁ የደረሱ ይመስላሉ።

«ሥቅሩ የት ተገኘህ?» አለችው መደንገጥዋ እያስታወቀባት።

«ምነው የሞትኩ መሰሎሽ ነበር?» አለ ከተቀመጠበት እየተነሳ። በናፍቆትና በሰስት አቅፍ አድርጎ ጉንጭና ጉንጯን እንገላብጦ ሳመ። ትኩስ የልጅነት ትንፋሹ ሞቃት፤ ወተት ወተት ሸተታት።

ፀሐይን ያሳደጓት አክስቷ ናቸው። እግዜር ለልጅ ባያድላቸውም የታናሽ ወንድማቸውን ልጅ አመጡ። «የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ» ብለው:: ተንከባክበው አሳድገው አስተማሯት:: ይኸው ወደ አስራ አንደኛ ከፍል አልፋላቸዋለች። ባላቸው ከሞቱ ወዲህ «ወራሽ ልጅ ነኝ፤ ሀብት ንብረት ይገባኛል» ባይ የማያውቁት የውጭ ልጅ መጥቶባቸው ተካሰው ጎንደር ይመላለሳሉ። ሰሞኑንም ለዚያው ሙግት ሄደዋል:: ሰራተኛ ወጥታባቸው ፀሐይን ብቻዋን ባዶ ቤት ጥለዋት መሄዱ ቢያስጨንቃቸውም የማይቀሩበት የፍርድ ቤት ጎዳይ ሆነባቸው:: ለማንኛውም ጎረቤቶቻቸውን «አደራ አስተዳድሯት ብቸኝነት እንዳይሰማት ፍቀዷት» ብለው ነበር ወደ ጎንደር የተጓዙት።

ፀሐይና ትሩፋት አዲስ ዘመን እስከ ስምንተኛ ከፍል አብረው ተምረዋል:: ደብረታቦር ሲሄዱም አብረው ነው:: ጓደኝነታቸውን ቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ያውቃሉ:: ፀሐይ ወደ ትሩፋት ቤት ስትሄድ ታምራትና ፍቅሩን ድንገት መንገድ ላይ ታገኘቻቸዋለች። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ

«ታምራት በዚህ በዝናብ ወዴት እያመራችሁ ነው?» ስትል ጠየቀቻቸው:: የት እየሄዱ እንደሆነ ግን ጠርጥራለች። የአዲስ ዘመን ልጅ የሆነ ሁሉ ስለፍቅሩና ስለትሩፋት የማያውቅ አልነበረም። ውስጥ ውስጡን ብዙ ታምተዋል።

«ትሩፋትን ልንጠይቅ ነው» አለ ፍቅሩ ቀደም ብሎ:: ቀጠል አደረገና «አንችስ ምነው ዝናቡ እስኪያባራልሽ እቤትሽ አትቆይም ነበር? እኛስ እንግዳ ስለሆን ትሩፋት አስገብታ ታስጠልለናለች ብለን ነው» አለ::

«ኧረ! እባቷ አሟቸው እቤት ናቸው። አንድ በእስቸኳይ የሚመለስ ዕቃ ባለቤቱ ከመውሰዱ በፊት ላሳያት አስፈልጌያት ነበር። እባቷ እቤት በመኖራቸው መውጣት ባለመቻሏ ነው ባዶ ቤት ትቼ ወደ እሷ የምሄደው» አለች ፀሐይ:: እነ ፍቅሩ ከትሩፋት ቤት ቢሄዱ በእባትና ልጅ መካከል ሊፈጠር የሚችለው ጠብ አየታያት::

«እኛም እኮ እሷ ትምጣ አላልነም። እኛ ነን ወደ እሷ የምንሄደው። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ደግሞ የአንቺ መኖርም ጥሩ ነው» እለ ፍቅሩ:: ታምራት ዝም ብሎ ያዳምጣል።

«አባቷ እያሉ እናንተን አስከትየማ በፍጹም አልሄድም! ምን ይሉኛል?» እለች ፀሐይ ባለመሄዷ ቆርጣ:: እከል አደረገችና «እናንተ ግን እቧቷ ቢያዩዋችሁ ሊደርስባት የሚችለውን ችግር እስባችሁታል?» ሁለቱንም አፈራርቃ እየተመለከተች ጠየቀቻቸው::





«ፀሐይ ከባህርዳር ድረስ ሰራዬ ብዬ የመጣሁበት ጉዳይ ነው። የመጣው ይምጣ!-- የሆነው ያሁን እንጂ! ዐይኗን ሳላይ አልመለሰም» አለ ፍቅሩ ፍርጥም ብሎ።

«መቼም አባቷ እያሉ ልትጠይቋት ካሰባችሁ ከፉ ጠብ እንደሚጣሷት እወቁ!» አለች ፀሀይ:: «ወንዶች ሲባሉ ማገናዘብ የሚችል አንጎል አልፈጠረባቸውም እንዴ? እንዲህ ሁለት ሆነው እየተጓተቱ ሲሄዱባት ምን ይደርስባታል እንኳን አይሉም! ምን ዓይነት ደደቦች ናቸው በሀና ማርያም!» ሙልጭ አድርጋ ሰደበቻቸው በውስጧ::

«በሆነው መንገድ ትሩፋትን ማግኘት እፈልጋለሁ:: በፍጹም ሳላገኛት አልመለስም!» አለ ፍቅሩ እሁንም ድምጹን ጠንከር ፊቱን ቅጭም አድርጎ:: ታምራት ግራ ገብቶት ዝም እንዳለ ነው::

«ለትሩፋት የምታስብ ከሆነ እሷን ማግኘት ያለብህ አባቷ ሳያውቁ ነው:: ያለዚያ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ትወድቃለች» አለች ፀሐይ በማስጠንቀቅ::

«እባክሽ ጸሐይ! በምን መንገድ ላገኛት እችላለሁ?» አለ ፍቅሩ ጭንቅ እያለው:: ያ ሁሉ ፉከራው ቀረ::

«በሆነው መንገድ ሁሉ እርጅው እባክሽ ፀሐይ:: ከባህርዳር እዚህ ድረስ ትራንስፖርት አውጥቶ የመጣው እሷን ለማግኘት ብሎ ነው:: ሳያገኛት ቢመለስ እሱም ያሳዝናል» አለ ታምራት ለማግባባት እየሞከረ::

ታምራት ፍቅሩ ለትሩፋት ያለውን ጥልቅ ፍቅር ያውቃል:: በዚህ በልጅነት እድሜው ፍቅር ላይ ወድቆ በትምህርቱ እንዳይሰንፍና አጉል እንዳይሆን በንጹህ የጓደኝነት መንፈስ ደጋግሞ መክሮታል:: ገስጾታል:: ፍቅሩ ግን የያዘ ስለያዘው የሚሰማ አልሆነም:: ታምራት እሁንም የአረፍት ጊዜውን ከቤተሰቦቹ ጋር እንዳያሳልፍ ይኸው ከፍቅሩ ጋር ይንከራተታል::

«እባክሽ! እባክሽ! ፀሐይ! በሀና ማርያም ልለምንሽ! ከትሩፋት ጋር የምገናኝበትን መንገድ እመቻችልኝ:: ሴት መላ እታጣም ስለ እግዚአብሔር ብለሽ መላ በይኝ!» ሲል ለተመለከተው እንጀት ይበላ ነበር ፍቅሩ::

«በቃ! እንዲህ እናድርግ:: እናቴ የለችም። ለጊዜው ብቻየን ነው ያለሁት:: በናንተ ምክንያት እባትና ልጅ ከሚጣሉ ትሩፋትን አስጠራታለሁ:: ኑ ከኔ ቤት እንሂድ:: ያው ለእኔም ቢሆን ጥሩ አይደለም:: ጎረቤቱ አደራ ተብሏል:: እናቴ ስትመጣ የሆነውንም ያልሆነውንም እውርቶ ማሳበቁ አይቀርም:: የትሩፋት እባት በአካል እግኝተዋችሁ ከሚጣሏት ምን አደርጋለሁ?» አለች ፀሐይ ሌላ መላ ስታጣ። ሦስቱም ተያይዘው ወደ ፀሐይ ቤት አመሩ:: ትሩፋት ተጠርታ መጣች::

«የት ከርመህ ነው ፍቅሩ? ሳትሰናበተኝ ከደብረታቦር ምድር ስትጠፋ ዳግም የምንገናኝ አልመሰለኝም ነበር» አለች ትሩፋት ከሰላምታ በኋላ።

«ባህርዳር ነው ያለሁ» አላት፡፡ ያንጊዜ ከሷ ተለይቶ ሊሄድ ሲነሳ ደብረታቦርን በመልቀቅና ባለመልቀቅ መካከል ነፍሱ እንዴት ተጨንቃ እንደ ነበር ማስታወስ ባይፈልግም በዐይነ ሕሊናው እየመጣበት፡፡ ቸሎ ተሰናብቷት የሚለይበት ጠብታ ታህል አቅም አልነበረውም። የት እንደሚሄድ ገና የወሰነው ነገር አልነበረም፡፡ ደብረታቦር ግን መኖር አይችልም፡፡ ዳግም የነዚያን ምስኪን ዘበኞች ምግብ እየተካፈለ እየበላ መኖር ሊቋቋመው የማይችለው ፈተና ሆነበት፡፡ በቃው! የትም ቢሆን መሄድ አለበት፡፡ ይህን ወስኖ ደብረታቦርን ሲለቅ ገና ጎህ አልቀደደም፡፡ የእናቱን ሞት እንደ ተረዳ ልጅ ራሱን በሁለት እጁ ይዞ ብቻውን እያለቀሰ የመሎን ሜዳ ሲያቋርጥ ሁሉ በደመነፍስ ነበር፡፡ ቁስ ጥሩ ተራራ ደርሶ ቁልቁለቱን እየተንደረደረ ሊወርድ እንኳ አልታወቀውም።

«ትምህርትህንስ ቀጥለሃል?» የትሩፋት ጥያቄ ከሄደበት የሐሳብ ጉዞ መለሰው፡፡ መቼም ትሩፋት የትምህርት ነገር አይሆንላትም፡፡ ፊቱን ከፍት ሲለው አየችው።

«አልተማርኩም፡፡ የመመዝገቢያ ጊዜው አልፎ ነበር፡፡» አላት ዐይኑን ፊት ለፊቱ ካለው ኖራ ቅብ ግድግዳ ላይ ሰክቶ።

ፀሐይና ታምራት ደግሞ የራሳቸውን ጨዋታ ይዘዋል፡፡

«ባህርዳር ምን እያደረክ ከረምክ?» አለችው ትሩፋት፡፡

«ቁሪስት አስጎብኚ ሆኜ ነው የከረምኩት።» እርግት ብሎ መለሰላት፡፡ ሲፈጥረው እርጋታው መቼም ለጉድ ነው፡፡

«ጥሩ ነው፡፡ ባለስራ ነህ ማለት ነዋ! ስራህን ትተህ እዚህ ምን የሚያስመጣ ጉዳይ ገጥሞህ ነው?» ደግማ ጠየቀችው። የመጣበትን ጉዳይ ግን እሱ የሚያውቀውን ያህል ታውቀዋለች። ዝም ብሎ በትዝብት ትከ ብሎ ተመለከታት። ዐይኑን ሸሸች። የተለወጠ ነገር የለም። ሲገናኙ እንዲሁ ነው የሚሆነው፡፡

«ልጠይቃችሁ! አብሮ አደግ ጓደኛ አይጠየቅም አሉሽ?!» ጥያቄዋን በጥያቄ ዝግ ብሎ መለሰላት።

«ኧረ እሱስ ይጠየቃል» አለች፡፡ እሷም ዝግ ብላ፡፡ የሆነ ያልሆነውን ሲያወሩ ሰዓቱ ሳይታወቃቸው ነጎደ።





«ጨዋታ ይዘን ሳናውቀው ጊዜው ገፍቶ መሽቷል ለካ። እንዳጋጣሚ አባቴ ደግሞ 'ራሴን አመመኝ' ብሎ እቤት ነው ያለው፡፡ አባቴን ታውቂው የለ ፀሐይ ይቆጣል ልሂድ፡፡ እንዴውም ብዙ ቆየሁ» ብላ ብድግ አለች ትሩፋት።

«እኔም አብሬሽ እሄዳለሁ» ብሎ ፍቅሩ አብሮ ብድግ አለ።

«የት?» አለች በአግራሞት እየተመለከተችው።

«እቤትሽ አይደል የምትሄጅው? ሌላ የት ይሆናል?»

«ምን ልትሆን? ምን ልታደርግ? አባቴ እቤት ነው ያለው እያልኩ እየነገርኩህ አይደል» በቁጣ ዐይኗን እፍጣ ጠየቀችው፡፡

«ሰምቼሻለሁ፡፡» አለ እንደተለመደው ረ--ጋ ብሎ፡፡

«እና! ከአባቴ ጋር ልታቆራርጠኝ ነው ፍላጎትህ?!»

«የእግዜር እንግዳ ነው ይዤሽ የምትሄጅው፡፡ ለምን ይቆጡብሻል?»

«ኧረ እባክህ! እሱ የማያውቀው የወንድ እንግዳ!?» ስትጮህ አልታወቃትም፡፡ ዝም ብሎ ተመለከታት፡፡

«ተከብሮ በኖረበት አገር የመጀመሪያ ሴት ልጁ ወንድ አስከትየ ከገዛ ቤቱ ስሄድለት በደስታ ይቀበላታል ብለህ አስበህ ከሆን የጤንነት አይደለም፡፡» አለችው ደግማ ውስጥ እንጀቷ በንዴት ቅጥል እያለ፡፡

«ከባህርዳር ሰበር የመጣሁት እኮ ናፍቀሽኝ ነው፡፡ አንችስ ብትሆኚ ይህንን አጥተሽው ነው? ገና ከመገናኘታችን 'ልሂድ' ብለሽ ብድግ የምትይው!»

«አባቴ እቤት መኖሩን ነግሬሃለሁ፡፡ ጊዜው ደግሞ መሽቷል፡፡ ይጣላኛል እኮ ነው የምልህ ፍቅሩ» ለስለስ አለች፡፡

«በአንቺ ላይ የሚደርስ ቅጣት ሁሉ በኔም ላይ ይድረስብኝ፡፡ ሞትም ቢሆን! በእኔ ምክንያት አንች ብቻሽን ምን በወጣሽ ትቀጫለሽ ትሩፋት?»

«ምን ማለትህ ነው ፍቅሩ? የቤቱ ባለቤት በሌሉበት በአንድ ቤት ጣራ ስር ሁለት ሁለት ሆነን እስካሁን መቆየታችን ሳያንስ!? ይኸ ራሱ እንኳን ምን ሊያስከትል እንደሚችል አይጠፋህም፡፡ ለፀሐይም አስብላት እንጂ! ያለ እበሳዋ ለእኛ ብላ ችግር ውስጥ እየገባች መሆኑ አይታይህም!? እናቷ ሲመጡ ጎረቤቱ ሁሉ እንኳን ያየውን ያላየውንም ጨማምሮ

ማሳበቁ አይቀርም። እኔም ችግር ውስጥ ነኝ:: ወሬው ከአባቴ ጆሮ መድረሱ አይቀርም:: በዚህ ብቻ እንኳን ከቤታቸው አብረው እንዳያስወጡን ያሰጋል»::

«አውቃለሁ፤ እንኳን በዚች ትንሽ ከተማ ወሬ የትም ቢሆን ተደብቆ አይቀርም» አለ ፍርጥም ብሎ::

«ይህን አያወቅህ ይባስ ብለህ ደግሞ እቤት ድረስ ልትከተለኝ ታስባለህ:: ይሄማ በፍጹም አይሆንም!» ይህን በማሰቡ እንኳ እንደ ያኔው እንደ ቤት ጠረጋው ጊዜ ጆሮ ግንዱ እስኪነድ በጥፊ ብታቃጥለው በወደደች።

ፀሐይና ታምራት ግራ ተጋብተው ሁለቱን እያፈራረቁ ዝም ብለው ይመለከታሉ::

«እንዴውም ማደርያ የለኝም ትሩፋት:: አባትሽ ካዘኑ የአግዜር እንግዳ ያሳድሩ። ቤት የአግዚአብሄር ነው:: ከጨከኑ ደግሞ ሕይወቴን ያጥፏት እንጂ--ዛሬ አብሬሽ ከመሄድ የሚያግደኝ አይኖርም» አለ ይባስ ድርቅ ብሎ።

«እየቀለድክ መሆን አለበት::»

«ቀልጄ አይተሽኝ ታውቂያለሽ ትሩፌ?» እውነትም ፍቅሩ ጠናን ሲቀልድ አይታው አታውቅም።

«ቆይ ግን ምኗ ነህ ተብለህ ብትጠየቅ ምን መልስ አለህ?»

«ምን ችግር አለው? እብሮ አደግ ጓደኛዋ ነኝ ነዋ! መልሱ::»

«እርስዎ ያልዳሩልኝ መርቀው ያልሰጡኝ የልጅዎ ባል ነኝ ብትል አይቀልህም:: ይኸው ነው የቀረህ!»

«ያን ያክል እንኳን ባለጌ አይደለሁም»

«ከዚህ በላይ!» አለችው ግንባሯን ሰቅላ:: ቀጠል አደረገችና «እባቷ ተከብሮ በኖረበት አገር ላይ ማንም ሴት እንዲህ ያለ ቅሌት አድርሳ ታይቶም! ተሰምቶም አይታወቅም! ፍላጎትህ አባቴ ረግሞ ከቤቱ እንዲያባርረኝ ነው አይደል? ትሰማለህ! አሞታታለሁ እንጂ አብረኸኝ አትሄድም! ተከብሮ በኖረበት አገር እባቴን አላዋርድም!!» አለች ትሩፋት በጣም ተናዳ::

«ትሩፋት-- አንቺ ችግሬ አይገባሽም! ገብቶሽም አያውቅም! እንዲገባሽም አትፈልጊም! ዛሬ ልጆች አይደለንም:: ስሜቴን ልትረጅልኝ ይገባ ነበር:: እንቺ ግን ሆን ብለሽ እንዳዝን ታደርጊኛለሽ! ሆን ብለሽ እንድከፋ ትፈልጊያለሽ! ለዛሬ እንኳን ደስ እንዲለኝ ታድያ ትንሽ እንኳ ብትቆይ ምን አለበት?»





ፀሐይ «ምን እናድርግ» በሚል እስተያየት ታምራትን አየችው:: ታምራት «ምን አውቃለሁ» በሚል አይነት ትከሻውን ሰበቀ::

«ኧረ በእናትህ ፍቅሩ! እንዲህ ድርቅ አትበል? በዐይንህ በብረቱ የምታየው አይደል ይኸው መሽቶ::» ብላ ወደ ውጭ በአጇ ጭምር እመለከተችው:: ጨለማው ለዐይን ያዝ አድርጓል::

«ድርቅና መስሎሽ ነው ትሩፋት? የልጅነት--የጧት ከፉ ለከፍት ብትይው አይሻልም ይልቅ! ከባህርዳር እዚህ ድረስ ሲያበር ያመጣኝ ዐይንሽን ለማየት ያለኝ ጉጉት ምን ያህል መሆኑን ብታውቂ እንዲህ ባላልሽኝ ነበር:: ዳሩ እውቀሽ እንድከፋ የምታደርጊው ነው እንጂ ይገባሻል::»

«እስከ እሁን ስንጫወት እምሽተናል:: ከዚህ በላይ መቼም አብረን አናድር::»

«አብረን ማደር ብንችል ደስታዬ ምን ያህል ቃላት ሊገልጸው የማይችል መሆኑን ብታውቂ ደግሞ ባልገረመሽም ነበር:: ለዚሁ አይመስልሽም እቤትሽ ድረስ አብሬሽ ለመሄድ የተነሳሁት:: እንቺ ባለሽበት ጣራ ስር ለማደር» እለ ፍቅሩ::

«አብድ እንኳ እንደዚህ አያደርግም::» አለች ትሩፋት ብሽቅ ብላ::

«አብጀስ እንደ ሆን? ባንቺ ቤት ሁሌ እንዳበድኩ ነው አይደል? ይህንኑ እብደቴንም ለአባትሽ ንገሪ:: ምን አልባት ከቁጣቸው ማምለጫ ዘዴ ይሆንሽ ይሆናል::» ነገረ ስራው አላማራትም ትሩፋት። ታምራትና ፀሐይን «ገላግሉኝ» ዓይነት በዐይኗ ተማጸነቻቸው።

«በቃ! ትንሽ ቆይ ትሩፌ:: ከታምራት ጋር ላዳር ሲሄዱ በዚያው ይሸኙሻል» አለች ፀሐይ:: አስታራቂ ሐሳብ ማቅረቧ ነው::

«ፀሐይ እውነቷን ነው። እኔ ቤት ስንሄድ በዚያው እንሸኝሽና ወደ ቤትሽ ትገቢያለሽ» አለ ታምራት። ትሩፋት ምርጫ እልነበራትም:: የእባቷ ቁጣ ስጋት እየለቀቀባት ያለውዴታዋ ተቀመጠች::

«ይኸ ልጅ ሁሌ እንዲህ እየተፈታተነኝ እስከ መቼ አኖር ይሆን? መጨረሻችን ከቶ ምን ሊሆን ይሆን? እንዴው ምን ባደርግ ይሻለኛል? ከዚህ ልጅ ጋር መገላገያ ዘዴው ምን ይሆን?» የጥያቄ መዓት ራሷን ጠየቀች:: ምንም መልስ ግን አላገኘችም:: ከፍቅሩ ጋር የምትለያይበትን ዘዴ ብታወጣ ብታወርድ ምንም የታያት ነገር አልነበረም:: ተጨነቀች::

ብትቆይም እኮ ዐይን ዐይኗን ከማየት ውጭ የሚሆን ነገር አልነበረም። እጇን ያዝ አድርጎ ያሻሻል። ቀስ እደርጋ ታስለቅቀዋለች። ዐይኗን ዘልቆ ለማየት ይሞክራል:: ዐይኑን

ትሸሻለች። ፀሐይና ታምራት የግላቸውን ወሬ አያወሩ ነፃነታቸውን ለመስጠት ቢሞክሩም የሆነው ይኸው ብቻ ነበር።

ትሩፋት ከአባቷ እየተደበቀች ወደ ፀሐይ ቤት እየሄደች ከፍቅሩ ጋር አንድ ሳምንት አብረው አሳለፉ። በዚህ አንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በፍቅሩ ልብ ውስጥ ፍቅር ከድሮው መቶ እጥፍ አድጎና ድርጅቶ መሰረቱን ጥሎ ግንቡን ገነባ። ወደ ባህርዳር ሲመለስ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትሩፋት በደም ስሩ ገብታ ከደሙ ጋር እየፈሰሰች በሰራ አካላቱ ተሰራጭታ ነበር።





## ጻአዳ አስመራ

የመምህራን ኮርሱን ወስደው ካለፉት ተማሪዎች አንዷ ትሩፋት ሆነች። አስመራ መምህራን ተቋም። የትምህርት ማስረጃዋን እሚልታ ስትወስድ ያኔ እንደ መከሯት ሁሉ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር አቶ አስረስ ትምህርቷን እንዲህ በአጭሩ ቀጭታ እዚህ ኮርስ በመግባቷ ወቅሰዋታል። ባለማወቅ የልጅ ሥራ እንደ ሰራች በመቁጠር ገስጸዋታል። ለወደፊቱም ቢሆን ከፍተኛ ትምህርት ለመማር ፍላጎቱ ካላትና ከተጋች እድሉ እንዳላት አጥብቀው መከረዋታል። መንገድ መንገዱን ጠቁመዋታል።

ትሩፋት ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተሰቧ ተለይታ አርቃ መሄዷ እርግጥ ሆነ። ምንም ቢሆን እንድም ሁነኛ ዘመድ በሌለበት የማታውቀው አገር መሆኑ ሆዷን ማሸበሩ አልቀረም። ነገር ግን መጽናኛ አላት። በእርግጠኝነት እንደ ተመረቀች ወድያውኑ ሥራ ይኖራታል። ታናናሾቿን እየረዳች ለማስተማር ጊዜው እየቀረበ ነው። ይህን ስታስብ ውስጧን ይህ ነው የማትለው ደስታ ይሰማታል።

«ለዚች ልጅ ስንቅ የሚሆን ዳቦቆሎ ነገር አዘጋጅላት እንጂ መቼስ ከሰው አገር ባዶ እጇን አትኼድ ነገር እኔም እዚያው አድርሻት እመጣለሁ ብዬ ቁቤ ገብቼ የመጀመሪያውን እጣ ውስጃለሁ።» አሉ አቶ ማንያዘዋል ፈራ ተባ እያሉ።

«ደሞ እንደ ለመዱት እዳ ውስጥ ሊዘፍቁን ማለት ነው? የቁቤ መጀመርያ መሆን እዳውን ሲገፈግፉ መኖር ነው» አሉ ሚስት ቆጣ ብለው።

«ዛዲያ የደረሰች ልጅ ዝም ብለህ መዳረሻዋን ሳታይ አግድመህ ልቀቃት ነው የምትይኝ!? መንገድ ላይም እዳር አለው እኮ! ኋላ አንድ ነገር ቢገጥማት ፀፀቱን እችለው ይመስልሻል? ይልቅስ የወሰድኩትን የቁቤ ብር እንደሚሆን እንደሚሆን እናደርገዋለን። ከስሞኑ ደሞ ደመወዝ ይጨመራል እየተባለ ስለሆነ እትጨነቂ» አሉ። ሚስት ነገሩ ባይጥማቸውም አልጎምጉመው ዝም አሉ። የደረሰች ሴት ልጅ ብቻዋን በማታውቀው አገር ትሂድ ማለቱ ከብዷቸው።

ትሩፋትና አባቷ ወደ አስመራ ለመሄድ ትኬት የቆረጡት ጎንደር ከተማ ነው። ከተማዋን ለማየት ብትጓጓም እድሉን ግን አላገኘችም። ከባህርዳር የተነሳውን የመጨረሻ እውቶብስ ይዘው የገቡት ከመሸ ነበር። ወደ አስመራ የሚሄደው ዋልያ የሕዝብ ማመላለሻ እውቶብስ በጧት ነው ጎንደር ከተማን የለቀቀው።

ወጣ ገባና ጠመዝማዛ የበዛበት የጎንደር-- አስመራ መንገድ አላስለቻትም። ተፈጥሮን እያደነቀች ከአባቷ ጋር ስትጓዝ። የሊማሊሞ ተራራን ከሩቁ ስትመለከተው ግን እንደ ቀለበት ዞሮ የገጠመ የሚመስለውን ዙሪያ ጥምጥም መንገድ-- መኪናው በሰላም ወጥቶ